# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ሚና፣ በ7ኛ ክፍል መነሻነት

በመላኩ ማናዬ

ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም.

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ሚና፤ በ7ኛ ክፍል መነሻነት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ

መላኩ ማናዬ

የጥናቱ አማካሪ፡- ማንያለው አባተ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሑፍ

ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ስማችንና ፊርማችን ከዚህ በታች የሰፈረው የፈተና ቦርድ አባላት፣ በመላኩ ማናዬ ፣“አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ሚና፣ በ7ኛ ክፍል መነሻነት” በሚል ርዕስ አማርኛን በማስተማር የአርት ማስተር ዲግሪን ለማግኘት በከፊል መሚያነት የተሰራው ይህ ጥናት፣ የዩኒቨርሲቲን የዲግሪ ማሚያ ፅሁፍ ደንብ የሚያሚላና ተቀባይነት ያለው መሆኑን አረጋግናል፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| የቦርድ ሰብሳቢ | ________________________ | __________ | __________ |
| የውጭ ፈታኝ | ________________________ | __________ | __________ |
| የውስጥ ፈታኝ | ________________________ | __________ | __________ |
| የጥናቱ አማካሪ | ________________________ | __________ | __________ |

# ማረጋገጫ

**አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ሚና፣ በሚል ርዕስ በመላኩ ማናዬ ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ጥናት ከዚህ በፊት በማንም አካል ያልተጠና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፣ እንዲሁም የተጠቀምኳቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና ጅማ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡**

**ስም** *መላኩ ማናዬ* **ፊርማ ------------ቀን-------------------**

# ምስጋና

ይህ ጥናት እዚህ ደረጃ እሰከሚደርስ ድረስ ከትልመ ጥናቱ ጀምሮ በመደገፍና በማማከር ላልተለዩኝ አማካሪዬ ዶ/ር ማንያለው አባተ ላቅ ያለ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በሚያስፈልጉኝ ጊዜ ሁሉ በስልክ፣ በኢ-ሜይል እና በአካል ለምጠይቃቸው ጥያቄዎች ሞያዊ ድጋፋቸውን ለግሰውኛል፡፡ ስራዬንም በጥሩ ሁኔታ እንዳከናውን አበረታተውኛል፡፡

እንዲሁም ዶ/ር ስርአቱ ብርሃኑ በስራዬ ሁሉ ከጎኔ በመሆን ለሰጡኝ ሞያዊ እገዛ ታላቅ ምስጋናዬ አቀርባለሁ፡፡

ይህን ጥናት ከጅምሩ እስከ ፍፃሜው ስሰራ ለተባበረኝ ለአፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን (ዋና ር/መ/ር ተስፋዬ ሙሉነህ፣ ም/ር/መ/ር ኃይለገብርኤል አንዱለም እና ም/ር/መ/ር ልጃለም ከበደ) እንዲሁም ለ7ኛ ክፍል ተጠኚ ተማሪዎች ታላቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም በማስተምርበት ጊዜ ተማሪዎችን በማስተባበርም ሆነ ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ በመፈተንና በማስሞላት ላልተለየቺኝ መምህርት ፍሬህይወት ፍቅሬ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተጨማሪም ፈተናውን በመፈተን ለተባበረኝ መምህር አዲስ አዱኛ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና ........ ii
አጠቃሎ ........ vi
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 6
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 8
1.4 የጥናቱ መላምቶች ........ 8
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 9
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 9
1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 10
ምዕራፍ ሁለት ........ 11
ክለሳ ድርሳናት ........ 11
2.1. ፅንሰ ሃሣባዊ ቅኝቶች ........ 11
2.1.1. የስነ-ጽሑፍ ምንነት ........ 11
2.1.2 ስነ-ፅሁፍ በትምህርት ዉስጥ ያለዉ ሚና ........ 13
2.1.3 ስነ-ፅሑፍን በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ........ 14
2.1.3.1 ስነ-ፅሑፍ እዉነተኛ ቋንቋ የሚጠቀም ዋጋ ያለዉ ሥራ መሆኑ ........ 14
2.1.3.2. ስነ-ፅሑፍ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ መሆኑ ........ 15
2.1.3.3. ስነ-ፅሑፍ ግላዊ ተሳትፎን የሚያዳብር መሆኑ ........ 16
2.1.4 ለቋንቋ ተማሪዎች የሚመረጡት የስነ-ፅሁፍ አሃዶች ........ 18
2.1.5 የአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህሪያት ........ 20
2.1.6 አጭር ልቦለድ ቋንቋን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ ........ 21
2.1.7 የምንባብ ምንነት ........ 23
2.1.8 አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ........ 24
2.1.9 የአንብቦ መረዳት ስልቶች ........ 27
2.1.10 የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ........ 28
2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 29
ምዕራፍ ሶስት ........ 34
የአጠናን ዘዴ ........ 34

3.1. የጥናቱ ንድፍ ...... 34
3.2 የጥናቱ አካላይ ...... 34
3.3. የጥናቱ የናሙና አመራረጥ ስልት ...... 34
3.3.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ ...... 34
3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ...... 35
3.3.3. የተማሪዎች አመራረጥ ...... 35
3.4. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ...... 36
3.4.1 ፈተና ...... 36
3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ ...... 37
3.5. የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ...... 38
3.6. የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ስልት ...... 39
3.7. የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት አግባብነት ...... 40
ምዕራፍ አራት ...... 41
የመረጃ ትንተና እና ውጤት ማብራሪያ ...... 41
4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና ...... 42
4.1.1 የቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና ...... 42
4.1.2 የድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤት ትንተና ...... 46
4.1.3 የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና ...... 50
4.1.4 ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና ...... 56
4.1.5. የመላምቶች ማረጋገጫ ...... 78
4.2. የውጤት ማብራሪያ ...... 79
5.1 ማጠቃለያ ...... 82
5.1.1. የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ግኝት ...... 85
5.1.2. የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ግኝት ...... 85
5.1.3 ፍትነታዊ ምርምሩን ለመፈተሽ የቀረቡ መላምቶችና ማጠቃለያ ...... 86
5.2. መደምደሚያ ...... 88
5.3 አስተያየት ...... 88
5.4. የጥናቱ የወደፊት አቅጣጫ ...... 90
ዋቢ ጽሑፎች ...... 91
አባሪዎች ...... 96

# ማውጫ

**ርዕ** **ገፅ**


ሠንጠረዥ 4.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ መረዳት የቅድመ ፈተና ውጤት ........................ 43

ሠንጠረዥ 4.2 የሙከራና ቁጥጥር ቡድን አንብቦ የመረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራዊ ትንተና ........................ 45

ሠንጠረዥ4.3 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ መረዳት የደህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ........................ 47

ሠንጠረዥ 4.4 የሙከራና ቁጥጥር ቡድን አንብቦ የመረዳት የድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራዊ ትንተና ........................ 49

ሠንጠረዥ 4.5 የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት........................ 51

ሠንጠረዥ 4.6የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራ ትንተና ........................ 52

ሠንጠረዥ 4.7 የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት........................ 53

ሠንጠረዥ 4.8 የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራ ትንተና ........................ 54

ሠንጠረዥ4.9 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ትንተና (በአይነታዊ መንገድ)........................ 57

ሠንጠረዥ 4.10 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ........................ 58

ሠንጠረዥ4.11 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ትንተና (በአይነታዊ መንገድ)........................ 62

ሠንጠረዥ 4.12 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ........................ 63

ሠንጠረዥ 4.13 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ........................ 65

ሠንጠረዥ 4.14 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ........................ 65

ሠንጠረዥ 4.15 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ ........................ 67

ሠንጠረዥ 4.16 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ........................ 68

ሠንጠረዥ 4.17 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ........................ 70

ሠንጠረዥ 4.18 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ........................ 70

ሠንጠረዥ 4.19 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ........................ 73

ሠንጠረዥ 4.20 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ........................ 73

ሠንጠረዥ4.21 ገላጭ እስታትስቲክ ........................ 76

ሠንጠረዥ4.22........................ 76

ሠንጠረዥ4.23 ገላጭ እስታትስቲክ ........................ 77

ሠንጠረዥ4.24 ገላጭ እስታትስቲክ ........................ 77

# አጠቃሎ

*የጥናቱ ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና ምን እንደሆነ መመርመር ነው፡፡ የምርምር ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ ለመመለሰም ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ የጥናት ንድፍን የተከተለ ሲሆን የናሙና አመራረጥ ስልቱም አላማ ተኮር ንሞና እና ቀላል የዕጣ ንሞና ስልት ነው፡፡ በመሆኑም ፈተናን እና የጽሑፍ መጠይቅን የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በናሙናነት ከተመረጡት የተጠኚና የቁጥጥር ቡድን የሰባኛ ክፍል ተማሪዎች በቅድመና በድህረ ፈተና አማካይነት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነ መረጃን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ የተገኘውን ውጤት መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን በመጠቀም በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በባዕድ ናሙና የቲ-ቴስት ዋጋ አማካይነት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከጥናቱ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ በመነሳትም አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና አዎንታዊ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና አዎንታዊ ስለሆነ የቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት አጭር ልቦለድን መጠቀም ቢችሉና የሚመለከታቸው አካላትም፣ መምህራን አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው እገዛ ማድረግ ቢችሉ የሚሉ የመፍትሔ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በሀገራችን አንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች አንዱና ቀዳሚው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ነው፡፡ ይህም አንብቦ የመረዳት ትምህርት ህፃናት በትምህርት ቤትም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የሚያግዝ መሰረታዊ ግብ መሆኑን Hallman (2009)ን ሞላልኝ (2011) ጠቅሰው ያብራራሉ፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲባል ደግሞ አንድን በፅሁፍ የቀረበ መልዕክት በሚገባ ተረድቶ ለሚፈለገው ዓላማ ማዋሉን የሚመለከት አቅም መሆኑን ምሁሩ አያይዘው ገልፀዋል፡፡

ማንበብ የመቀበል ክሂል ሲሆን፣ በአንባቢውና በፅሁፉ መካከል የሚደረግ መስተጋብር እንደሆነም Harmer. (2001) ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም አንብቦ መረዳት አንባቢው ከሚያነበው ፅሁፍ ፍሬ ነገሩን መለየት፣ ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት፣ የቃላትን አገባባዊ ፍቺ ማወቅ፣ የፅሁፉን አወቃቀር መለየትና መሰል ክሂሎችን አጠቃሎ እንደሚይዝ ምሁሩ ገልፀዋል፡፡

ከፍ ሲል የቋንቋ ምሁራን ከገለፁት መረጃ መረዳት የሚቻለው አንብቦ መረዳት መረጃን ከተለያዩ ፅሁፎች በቀላሉ የምናገኝበት ወይም የምንቀበልበት ክሂል መሆኑን ነው፡፡ ይህም አንባቢው የፅሁፉን መልዕክት ለመረዳት የሚያከናውነው አእመሯዊ ሂደት ሲሆን፣ የፅሁፉን አጠቃላይ ጭብጥ (መልዕክት) መረዳትን፣ የቃላትን አውዳዊ ትርጉም መገንዘብን፣ የፅሁፉን ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳትንና የፅሁፉን አወቃቀር መለየትንና መሰል የንባብ ተግባራትን ወይም ንዑሳን ክሂሎችን አካቶ እንደሚይዝ ከሙህራኑ ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

አንብቦ መረዳት በአንድ ጊዜ የሚሻሻል ችሎታ አይደለም፡፡ ስለዚህም ከዝቅተኛው የክፍል ደረጃ ጀምሮ በሚቀርብ የንባብ ትምህርት በትኩረት ለህፃናት መሰጠት ይኖርበታል፡፡ የአንብቦ መረዳት ትምህርት (comprehension instruction) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ ውስብስብ የስርዓተ ትምህርት አካል በመሆኑ መምህራን ትኩረት ሰጥተው ተማሪዎችን ማገዝ እንዳለባቸው ሞላልኝ (2011) Wapole & Mckenn (2007)ን ጠቅሰው ይገልፃሉ፡፡

አንብቦ መረዳት ልዩ ልዩ ውስብስብ ንዑሳን ክሂሎችን በውስጡ የሚይዝና በተለይም ህፃናት ትምህርት ቤት በሚቆዩበት ጊዜና በወደፊት ህይወታቸው በሚገባ ሊያሳድጉት የሚገባ ቀዳሚና ዋናው የንባብ ትምህርት ዓላማ ሊሆን ይገባል በማለት Hallman (2009)ን ሞላልኝ (2011) ጠቅሰው ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህም
የትምህርት ባለሞያዎች፣ ርዕሳነ መምህራን፣ ወላጆችና የመንግስት አካላት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ሊደግፉ እንደሚገባ Hallman (2009) ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ምሁራኑ ካቀረቡት መረጃ መረዳት የሚቻለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ጀምሮ ትኩረት በመስጠት እስከ ከፍተኛ ደረጃና ከትምህርት ቤት ውጭ ባለው ህይወታቸው ጭምር በሂደት ሊሰራበት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ወላጆች፣ መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራንና የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በመተባበር ለተማሪዎቹ እገዛ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ይሄውም ቤተ-መፅሀፍትን በመገንባትና በማደራጀት እና የሚነበቡ ልዩ ልዩ መፅሀፎችን በሚሟላት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ያስረዳናል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ገዜ የህፃናትን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር መምህራን በርካታ የንባብ ማስተማሪያ ስልቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ከሚቀርቡ ልዩ ልዩ የንባብ ማስተማሪያ ምንባቦችና መርሀ ትምህርቶች በተጨማሪ የተለያዩ ሳቢና ማራኪ የስነ ፅሁፍ ስራዎችን ክፍል ውስጥ በማቅረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሊያሳድጉ ይገባል፡፡ ስለዚህም የቋንቋ ትምህርት በስነ ፅሁፋዊ ስራዎች (ግጥም፣ አጭር ልቦለዶች፣ ተውኔት፣ ወዘተ.) ታግዞ ቢቀርብ በተለይም የህፃናትን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ሚናው/አስተዋፅኦ ላቅ ያለ እንደሆነ Ur (1998) ገልፀዋል፡፡

የስነ ፅሁፍ ስራዎችን ለቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያነት የምንጠቀመው በዋናነት የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታና ልዩ ልዩ የክሂል ዘርፎችን ለማሳደግ እንጂ ተማሪዎችን የስነ ፅሁፍዊ ስራዎች አድናቂዎች አለያም የስነ-ፅሁፍ ባለሞያዎች ለማድረግና ደራሲ ለማፍራት አይደለም በማለት Shorte et al (2018)ን ሞላልኝ (2011) ጠቅሶ ያስረዳል፡፡

ንባብ ለማስተማር በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምቹ አውድ መፍጠር ይገባል፡፡ በተለይም የአንደኛ ደረጃ ትምህት ቤት መምህራን በስነ ፅሁፍ የታገዘ ትምህርት ለተማሪዎቻቸው

መስጠት ይገባቸዎል፡፡ ምክንያቱም አንብቦ መረዳት ችሎታቸው በተገቢው መንገድ መዳበር እንዳለበትና አስፈላጊ እንደሆነ በማመን በክፍል ውስጥ በስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች የታገዘ የመማር አውድ (prnit-nch environment) መፍጠር እንዳለባቸው Popp (2005) ገልፀዋል፡፡ ስለዚህም ከሁሉም የህፃናት ስነፅሁፋዊ ዘውጎች ማለትም ግጥሞችን፣ ታሪካዊ ልቦዶችን፣ አጫጭር ልቦለዶችንና አፈ ታሪኮችን የመሳሰሉትን በማካተት ማቅረብ እንዳለባቸው Popp (2005) Short et al. (2018)ን ሞላልኝ (2011) ጠቅሰው ገልፀዋል፡፡

ከፍ ሲል ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ምንባብን ሲያስተምሩ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት የሚቀሰቅሱ ሳቢና ማራኪ የማስተማሪያ ፅሁፎችን መጠቀም ያለባቸው መሆኑን ሲሆን፣ ከነዚህ የስነ-ፅሁፍ ዘውጎች ውስጥም አጭር ልቦለድ ይገኝበታል፡፡

ስነ-ፅሑፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ተግባር መዋል የጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግሪክና ሮም ውስጥ ነበር። በወቅቱ ስነ-ፅሑፍ ለሰዋስው ትርጉም ማስተማሪያነት እየተጠቀሙበት እንደ ነበርና በ1980 ዎቹ አካባቢ ጀምሮ በተጠናከረ መልኩ ስነ-ፅሑፍ የቋንቋን ትምህርት በክፍል ውስጥ ለማስተማር ያለውን ጥቅም የሚያሳዩ የተለያዩ ጥናቶች መታየት ጀመሩ። ከነዚህም ውስጥ Colie and Slatter(1987)፣ Johnson (1981) እና Widdoson (1983) ተጠቃሽ መሆናቸውን Matrix (2015) ይገልፃሉ። በመሆኑም ቋንቋን በስነ ፅሑፍ ማስተማር የተጀመረበትን ጊዜ ስንመለከት ዕድሜው ቆየት ያለ መሆኑን ያመለክታል።

ስነ-ፅሑፍ የሰው ልጅ በገሃዱ ዓለም ውስጥ የሚፈፀመውን የህይወት ውጣውረድ ወይም ገጠመኝ ደስታ ሀዘኑን፣ ስቃይ መከራውን፣ ዕድገተት ውድቀቱን፣ ወዘተ. መልሶ ለማህበረሰቡ የሚቀርብበት የፈጠራ ስራ ነው። ይህም የፈጠራ ስራ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በንቃትና በደስታ እንዲከታተሉ መነሳሳትን ይፈጥራል። ስነ-ፅሑፍ ሰዎች ስለራሳቸውና ስለህይወታቸው የሚሰማቸውን፣ የሚመኙትንና የሚያልሙትን በአጠቃላይ አስተሳሰባቸውን በቋንቋ አማካኝነት የሚገልፁበት ኪነ-ጥበብ ነው። የፈጠራ ስራ በመሆኑም ሳቢ ነው። ሳቢነቱ ደግሞ ስሜትን ይነካል፣ ይማርካል እንዲሁም ደስታን ይፈጥራል በማለት ዘሪሁን (1996) ገልፀዋሉ። ይህም ስነ-ፅሑፍ የአገላለፅ ስልቱ ውብና ማራኪ በመሆኑ እያዝናና እና እያዋዛ እውቀትን ያስጨብጣል።

እንዲሁም በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ደስተኛ ሆነው ትምህርቱን እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሳደግ ያለው ጠቀሜታ ከፍ ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ስነ-ፅሑፍ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በርካታ ክስተቶችና ሁነቶችን መሠረት አድርጎ የሚፃፍ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው በማለት በድሉ (1996) ይገልጻሉ። ይህ ገለፃም ስነ-ፅሑፍ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለውና በገሃዱ ዓለም ላይ የሚከሰቱ የህይወት ውጣ ውረዶችን ማሳያ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎችን ከተለያዩ የህይወት ልምዶች ጋር እንዲተዋወቁ እድል ይሰጣቸዋል። ይህም የደስታ ስሜትን ስለሚፈጥርላቸው ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎትና ጉጉት እንዲጨምርላቸው እገዛ ያደርጋል። ስነ-ፅሑፍ የሰው ልጅ በውስጡ የሚመላለሰውን ሀሳብ ሊለካ፣ ሊመዝነና ሊጨበጥ የማይችለውን ረቂቅ ጉዳይ በቋንቋ አማካኝነት የሚገለፅበት መንገድ ነው። ለዚህም ነው ‹‹ስነ-ፅሑፍ በንግግር ውስጥ ያለ ቋንቋ ነው›› በማለት (Mcky፣ 1982) የሚገልጹት። ይህ ደግሞ ስነ-ፅሑፍ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር ያለው ትስስር የላቀ መሆኑን ማሳያ ነው ። ይህ ደግሞ የደራሲን ስራ አንብቦ ለመረዳት ያለው ጥቅም ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ፈቃደ (1988) የስነ-ፅሑፍን ምንነት ሲገልፅ "ስነ-ፅሑፍ ነገሮችን በቀላሉ፣ ውብና ሚስጥራዊ በሆነ ቋንቋ ይገልፃሉ። አያይዘውም በስነ-ፅሑፍ የቀረበ ፍሬ ሀሳብ በቀላሉ የሚረዱት አይደለም። ያምራል፣ ምን ማለት ፈልጎ ነው ያሰኛል። ይህም ሁኔታ ተደራሲው የሀሳቡን ምንነት ለመረዳት፣ ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርግ ያስገድደዋል።" በማለት ያብራራሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ስነ-ፅሑፍ ሳቢና ማራኪ የመሆኑን ያህል፣ የስነ-ፅሑፍን ሀሳብ ለመገንዘብ ጥረትንና መመራመርን የሚጠይቅ፣ የአእምሮ ንቃተ ህሊናን ይበልጥ አንባቢዎች እንዲያሰሩት የሚያስገድድና አዝናኝ በመሆኑ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው ነው።

በእዚህ መሠረት ከስነ-ፅሑፍ ዘውጎች ውስጥ አንዱ ልቦለድ ሲሆን አጭር እና ረጅም ልቦለድ ተብሎ ይከፈላል። ሁለቱም የልቦለድ አይነቶች አላባውያንን በመያዛቸው ቢያመሳስላቸውም በአላባውያኑ መጠንና በገፅ ስፋታቸው ላይ የጎላ ልዩነት አላቸው። አጭር ልቦለድ እንደ ስሙ መጠኑ ጠባብ የሆነ፣ ጥቂት ገፀባህርያትን፣ ጠባብ መቼትን ይዞ ከአስር ሺህ ባልበለጠ ቃላት ያነሳውን አንድ የትኩረት ነጥብ ሰብሰብ ባለ ሁኔታ በጥድፊያ ለመቋጨት የሚንደረደር የልቦለድ አይነት ነው (ዘሪሁን፣ 1996)፡፡

ስለዚህም አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ እና ተነሳሽነት ለማሳደግ ሳቢ እና ማራኪ እንዲሁም በጥቂት ጊዜ የሚያልቅ፣ በመሆኑ አስተዋፅኦው ላቅ ያለ እንደሚሆን መረዳት ይቻላል።

አጭር ልቦለድ ቋንቋን ለማስተማርም ተመራጭ ነው። ሆኖም መምህራን በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ መሠረት ቴክስቶችን ወይም ማስተማሪያ ፅሑፎችን መምረጥ አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን ቴክስቱን ማንበብ ለተማሪዎቹ ከባድ ስራ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም ለማስተማሪያነት የሚመረጡ የአጫጭር ልቦለድ ቴክስቶች /ፅሑፎች የተማሪውን ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ የእውቀት ዳራ፣ የባህል ዳራ እና የቋንቋ ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። ይህም የንባብ ትምህርቱን ውጤታማ ያደርገዋል (Hismnoglu፣ 2005)።

በተያያዘ መንገድ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የንባብ ችሎታቸውን ለማሳደግ የተለያዩ ምንባቦች ሊቀርቡላቸው ይችላል። የተማሪውን የንባብ ችሎታ በተሻለ መንገድ ለማሳደግ ደግሞ አጭር ልቦለድን መጠቀም ተገቢ ነው። ይህም የንባብ ፍላጎታቸውን ያነሳሳል። ምክንያቱም በአጭር ልቦለድ ውስጥ ያሉት ታሪኮች አጓጊና ማራኪ ስለሆኑ ተማሪዎች ምንባቡን በጉጉት እንዲያነቡትና ቀጥሎ ያለውን ታሪክ ለማወቅ ሲሉ ምንባቡን እንዲጨርሱት ያበረታታቸዋል። በተጨማሪም የተማሪውን ጭንቀት ይቀንሳል፤ የማንበብ ተግባርን ቀለል ያደርጋል፤ ዘና ብለው እንዲያነቡ ያግዛል፤ የእርስ በእርስ ግንኙታቸውንም ያሳድጋል ማለትም ስላነበቡት ታሪክ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ ምላሽ እንዲሰጡ እና እርካታን እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል (Kohan and Pourkalhor፣ 2013)፡፡

በአጠቃላይ አጭር ልቦለዶች የአንባቢን ስሜት የሚገዙ በመሆናቸው የተማሪውን ልብ በማንጠልጠል ቀጣዩን ለማወቅ በጉጉት እንዲያነቡ፣ ባነበቡት ታሪክ ላይ ተመስርተው እንዲጠይቁ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲነጋገሩ፣ እንዲከራከሩ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያስችላቸዋል፤ ቀለል ባለ መንገድ የንባብ ችሎታቸውን ያዳብራል፤ የተማሪውን ጭንቀት በመቀነስ ዘና ብለው እንዲማሩ ያበረታታል፤ ስለ ገሃዱ አለም የተለያዩ እውቀቶችን እንዲያካብቱ፥ የተለያዩ ምሁራን ሲገልጹ ይስተዋላሉ። ስለሆነም እነዚህን የስነ-ፅሑፍ ስራዎች ለማስተማሪያነት በምንመርጥበት ጊዜ ዓላማችን ግብ እንዲደርስ የተማሪዎችን የእውቀት ዳራ፣ የእድሜ ሁኔታ፣ የባህል ዳራ እና የክፍል ደረጃቸውን በሚመጥን መልኩ እየተዘጋጀ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ቢውል የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሳደግ ያለው

ሚና ምን እንደሆነ በዚህ ጥናት በዝርዝር ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተገቢው መንገድ እንዲሻሻልና ተማሪዎች በንባብ ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ እገዛና ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ Taylor, Pearson.Clark & Walpole (2002) እንደገለፁት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ትምህርት ቤቶች በሚፈልጉት መንገድ የዳበረ አለመሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በኢትዮጵያ ደረጃም ቢሆን የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የንባብ ክሂል በጣም ዝቅተኛ መሆኑን በ EGRA (2010) ተገልጿል፡፡ የተማሪዎች የንባብ ክሂል ካላደገ ደግሞ በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ ይህ ደግሞ በወደፊት ህይወታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህም ለተማሪዎች የሚቀርብ የንባብ ትምህርት ይህንን ችግር በመቀነስ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡

አጥኚው በተገለጸው የጥናት ርዕስ እንዲያጠና ያነሳሱት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመርያው ምክንያት በቋንቋ ምሁራኖች መካከል የሚሰጡ ወጥ ያልሆነ አተያይ ሲሆን፤ይህም የቋንቋን ትምህርት በስነ-ፅሑፍ አማካኝነት ማቅረብ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል በማለት Macy (1982) ይገልፃሉ፡፡ እንደ ምሁሩ እምነት ቋንቋን በስነ-ፅሑፍ ማስተማር የቋንቋ ትምህርት እንዲበላሽና የቋንቋ ተማሪዎችን ግራ በማጋባት ውጤታማ በሆነ መልኩ በቋንቋው መጠቀም እንዳይችሉና የቋንቋ ክሂላቸው እንዳያድግ ያደርጋቸዋል ሲሉ፤

በሌላ በኩል ደግሞ የቋንቋ ትምህርትን በአጭር ልቦለድ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ያሳድጋል፤ የመማር ፍላጎታቸውንም ያነሳሳል፤ ስነ-ፅሑፍ የሚቀርብበት ቋንቋ ሳቢ ስለሆነ መልዕክት በቀላሉ ወደ ውስጣችን እንዲሰርፅ ያግዛል፤ ነገሮችን በልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ተንትኖ የመረዳት አቅምን ያጎለብታል፤ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ ያሳድጋል ፣ አንባቢን ከፅሁፉ ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረው የሚያስችል መሆኑን Colli and Slatter (1987)፣ Vural (2013) እና Kohan and Pourkalhor (2013) ያስረዳሉ፡፡ ይህም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው እገዛ የላቀ ነው በማለት አያይዘው ይገልፃሉ፡፡

እንዲሁም ስነ-ፅሑፍ ትምህርታዊ ጉዳዮች የሚንፀባረቁበት በመሆኑ የተማሪዎችን የዕውቀት አድማስ ያሰፋል፣ የሰዎችን የህይወት ልምድ እንዲቀስሙ እድል ይፈጥራል፣ እንዲሁም በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚያስችል ጥሩ

የሆነ መለማመጃዎችን ያስገኛል በማለት Berhanu (2009) ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም ስነ-ፅሑፍ ቋንቋን ለማጎልበት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ አንባቢው የንባብ ልምዱ እንዲዳብር እንዲሁም ሀሳቡን አስፋፍቶ የመግለፅ ልምድ እንዲኖረውና የንባብ ክሂል እውቀትን ለማሳደግ የሚያስችሉ መሆናቸውን ሲገልፁ፤ በድሉ ( 1996) ደግሞስነፅ-ሑፍ በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ውይይት ተማሪዎችን ስለሚስብ የተሳታፊዎቻቸውን ደረጃ ከፍ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች አጫጭር ታሪኮችንና ግጥሞችን ሲያነቡ የመናገርና የማንበብ ክሂላቸው ይዳብራል፡፡ በተለይም ስነ-ፅሑፍ በሳቢ ቋንቋ ስለሚቀርብ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውንም ሆነ ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር በሚከናወኑ ልምምዶች ላይ ለመሳተፍ ውጫዊ ግፊት አይፈልጉም፡፡ ስነ-ፅሑፍ ማንበብ፣ ስነፅ-ሑፍ መናገር፣ ስነፅ-ሑፍ መፃፍ ፣ ስነ-ፅሑፍ ማዳመጥ ይፈልጋሉ፡፡ የሚል አስተሳሰብ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በመስኩ ምሁራን መካከል ያለው ወጥ ያልሆነ አተያይ ለዚህ ጥናት የመጀመሪያው የጥናቱ መንስኤ ሲሆን፣ ከዚህም አንፃር ይህ ጥናት በምሁራኑ መካከል ያለውን የአተያይ ተቃርኖ የማረጋገጥ ፍላጎት ይዞ የተነሳ ነው፡፡ ስለዚህም አጥኚው አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የማንባብ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ሚና ምንድን ነው የሚለውን ለማወቅ በዚህ የጥናት ርእስ ላይ እንዲያጠና ያነሳሳው ምክንያት ሆኗል።

ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ የአጥኚው የሥራ ተሞክሮ ነው፡፡ ይህም ሲባል አጥኚው  ለአስራ ሁለት ዓመታት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያስተምርበት ወቅት ያስተዋለው በተማሪዎች ዘንድ የአንብቦ መረዳት ችግር መኖሩን ነው። በተለይም አብዛኛው ተማሪ በሚያነቡበት ጊዜ ቃላትን በመግደፍ፣ቃላትና ሐረጋትን በመቆራረጥ፣ በመንተባተብ፣ በጣት እየጠቆሙ ማንበብ፣ አዝጋሚ በሆነ ፍጥነት የሚያነቡ መሆናቸው፣ ተነስቶ ለማንበብ ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን፣ ፍቃደኛ ከሆኑት ውስጥም የሚነበበውን ፅሑፍ ይዘው ዝም ብለው መቆማቸውን፣  አንዳንዴም መስመሮችን መዝለላቸውን፣ መመልከቱ እንዲሁም በክፍል ስራ ወቅት የአንብቦ መረዳት መልመጃ ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ ያለመመለስና ለሚመልሷቸውም ጥያቄዎች ምክንያታዊ ያለመሆንና የተብራራ መልስ ለመስጠት ሲቸገሩ ማስተዋሉ ነው። ሌላው በአጋማሽና በማጠቃለያ ፈተናዎች ወቅት ለሚቀርቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በተሰጣቸው ሰዓት ያለመጨረስና መልሶችንም ተረድተው ያለመስራት ሁኔታን በተደጋጋሚ ማስተዋሉ ሲሆን፣ በተጨማሪም ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና

ፈተናዎች ትኩረት ያለመስጠትና የግንዛቤ አቅማቸው ዝቅተኛ መሆኑን አጥኚው አስተውሏል፡፡ በዚህም የተነሳ አጥኚው ምን አይነት ይዘት ብጠቀም ነው የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ሊጎለብት የሚችለው? የሚልው በአዕምሮው ሁሌም የሚመጣበት ጥያቄ በመሆኑ ጥናቱን ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

1. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር ተማሪዎች የቃላት አውዳዊ ፍቺን (ትርጓሜ) እንዲለዩ የሚያስችል መሆኑን ይፈትሻል፤
2. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች ዝርዝር ሃሳቦችን (መረጃዎችን) መለየት እንዲችሉ ማድረጉን ይመረምራል፤
3. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች የዕሁፉን አጠቃላይ መልዕክት መግለፅ መቻላቸውን ይመረምራል፤

## 1.4 የጥናቱ መላምቶች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ችሎታ ለማሳደግ ያለውን ሚና (አስተዋፅኦ) መመርመር ሲሆን፤ ጥናቱ የሚከተሉትን መላምቶች አስቀምጧል፡፡

ሀ. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የአንብቦ መረዳት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች በተለመደው መንገድ ከሚማሩ ተማሪዎች የበለጠ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ይኖራቸዋል (H1:μ1>μ2)

ለ. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የአንብቦ መረዳት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች በተለመደው መንገድ ከሚማሩ ተማሪዎች ያነሰ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ይኖራቸዋል (H1:μ1<μ2)

ሐ. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የአንብቦ መረዳት ክሂልን በሚማሩና በተለመደው መንገድ በሚማሩ ተማሪዎች መካከል ምንም አይነት የአንብቦ መረዳት ልዩነት አይኖርም (H1:μ1=μ2)

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ስነ-ጽሑፍን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የሚቀርበዉን ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ ከፍተኛ ዕገዛ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም "አጭር ልቦለድ" ተጠቅሞ ማስተማር በመማር ማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ምን ፋይዳ እንዳለዉ በሙከራ በማረጋገጥ በመማር ማስተማር ትግበራ ዉስጥ የሚኖረዉን ድርሻ በማየት በዚህ ጥናት ዉስጥ በዓላማ ላይ የተጠቀሱ ዝርዝር ጉዳዮች አዎንታዊ ግብ የሚያመላክቱ ከሆነ ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና ለቋንቋ መጽሐፍት አዘጋጅ ባለሙያዎችና ለተመራማሪዎች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር የተማሪችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማሳደግ ሊጠቅም ይችላል

2. አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለውን ፋይዳ ለመምህራን ሊጠቁም ይችላል፡፡

3. የቋንቋ መምህራን የተማሪው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለይተው በማወቅ ተመሳሳይ ጥናት እንዲያካሂዱ ሊረዳቸው ይችላል

4. ጥናቱ በሚያስገኘው ውጤት መነሻነት የቋንቋ መምህራን የንባብ ትምህርት በሚያዘጋጁበት ጊዜ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከማሳደግ አንፃር እንዲያዘጋጁ ያግዛቸው ይሆናል

5. ለቋንቋ ባለሙያዎች፡- በቋንቋ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ እንዲመታ የተማሪዎችን የእውቀት ዳራ፣ የእድሜ ሁኔታ፣ የባህል ዳራ እና የክፍል ደረጃቸውን የሚመጥን የስነ-ጽሑፍ ሥራዎችን ለማካተት፣ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ምን እንደሆነ በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

6. ወደ ፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናት ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች እንደመነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት አድርጎ የተነሳው በአጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ሚና በመመርመር ላይ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ጥናቱ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ በተማሪዎች የማንበብ ክሂል ችሎታ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የተነሳ ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን የንግግር፣ የማዳመጥ እና የመጻፍ ክሂል ችሎታ እና ተነሳሽነት ምን እንደሆነ በጥናቱ አልተካተትም፡፡ ያልተካተትበት ምክንያት ደግሞ የጥናቱ ርእስ በአንብቦ መረዳት ላይ የተወሰነ ስለሆነ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ጥናቱ ተግባራዊ የተደረገው በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ በሚገኙ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን ነው፡፡

በመሆኑም ከሰባተኛ ክፍል ውጭ የሉ ተማሪዎች በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ ያልተካተቱበት ምክንያትም ጥናቱ ሙከራዊ ስለሆነ የቁጥሩ መብዛትና የክፍል መለያየት በጥናቱ ባህርይ ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል ከማለት የተነሳ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ የሚካሄደው በአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በሰባተኛ ክፍል ላይ ነው። ጥናቱ በዚህ ቦታ ላይ ብቻ የመወሰኑ ዋናው ጉዳይ ሁሉንም የክፍል ደረጃዎች አጠቃሎ ማጥናት ጠቀሜታው የጎላ ቢሆንም ካለው የገንዘብ፣ የጊዜና የሰው ኃይል አቅም እጥረት ምክንያት ነው፡፡ በእዚህም ጥናቱ በአንዱ የክፍል ደረጃ ላይ ብቻ እንዲከናወን መደረጉ እንደክፍተት ተወስዷል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1. ፅንሰ ሃሣባዊ ቅኝቶች

#### 2.1.1. የስነ-ጽሑፍ ምንነት

ስነ-ጽሑፍ ምንድን ነዉ? ለሚለዉ ጥያቄ ቀላል ምላሽ ለመስጠት ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም ስነ-ጽሑፍ በሰዉ ልጅ ታሪክ ለብዙ ዘመናት ፀንቶ የቆየ የኪነ-ጥበብ መስክ በመሆኑ፣ ዘርፉን አስመልክቶ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ምርምሮች የተካሄዱ በመሆኑ ስነ-ጽሑፍን አሰመልክቶ የተሰጡ ብያኔዎች፣ የተለያዩ አንዳንዴም፣ የተራራቁ በመሆኑ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ የስነ-ጽሑፍን ምንነት ቁርጥ ባለ መንገድ መግለጽ ባይቻልም ተደጋግሞ የሚነሱት ዋና ዋናዎችን መሠረት በማድረግ Lazar፣ (1993) እና ዘሪሁን (1992) በሦስት ምድብ መድቧቸዋል፡፡ ይህም ስነ-ጽሑፍ የሚባለዉ የተፃፈ ነገር ሁሉ ነዉ፡፡ በዚህ እሳቤ መሠረት በጽሑፍ የሰፈረ ነገር ሁሉ ነዉ፤ በጽሑፍ የሰፈረ ነገር መቼም ይፃፍ በምንም ዓይነት ጉዳይ ላይ ይፃፍ፣ በማንም ተጽፎ ይገኝ፣ ስነ-ጽሑፍ ተብሎ ይጠራል፡፡ በመሆኑም የጥንት ድንጋይ ላይ ጽሑፎች፤ የመቃብር ላይ ጽሑፎችና ቅዱሳት መጽሐፍት ወዘተ የመሳሰሉት በስነ-ጽሑፍ ጎራ ይመደባሉ፡፡

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳዉ የተፃፈ ነገር ሁሉ ሲል ማንኛውንም የፅሁፍ ዓይነትና በማንኛውም ነገር ላይ የተፃፈን ነገር የሚያጠቃልል መሆኑን ነዉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በታላላቅ ሰዎች የተጻፉ መጽሐፍት ናቸዉ የሚለዉ ብያኔ ደግሞ ስነ-ጽሑፍ የተጻፈ ነገር ሙሉ ሳይሆን በዓለማችን ላይ የራሳቸዉን የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፣ ዘመንና ቦታ ሳይገድባቸዉ ለመዝለቅ የቻሉ ልቦለዶችም ሆኑ ኢ-ልቦለድ ሥራዎች ናቸዉ፡፡ ይህ ብያኔ መሠረት ያደረገዉ ቅዱሳት መጽሐፍትን እና ለአሁኑ ዘመን መሠረት በመሆን የሚያገለግሉ የምርምር ሥራዎች በምሳሌነት ያቀርባሉ፡፡ በሦስተኛ ምድብ የቀረበዉ ደግሞ ስነ-ጽሑፍ የሚባሉ የፈጠራ ሥራዎች ብቻ ናቸዉ፡፡ አንድ ስነ-ጽሑፍ ስነ-ጽሑፍ ለመባል ተጽፎ መገኘቱ ብቻ ሳይሆን ከደራሲዉ ምናብ መንጭቶ የአንባቢዉን አዕምሮ ማነቃቃትና መንፈስን ማበረታታት ሲችል ነዉ፡፡ ስነ-ጽሑፍ የሚባለዉ ለዚህ በምሳሌነት የሚጠቀሱት የስነ-ጽሑፍ ዘርፎች ስነ-ቃል፣ ስነ-ግጥም፣ ተዉኔት፣ ልቦለድ የመሳሰሉትን ሲያነሱ ይህ መሠረታዊ ሃሳብ ደግሞ አንድ ስነ-ጽሑፍ ስነ-ጽሑፍ ለመባል የፈጠራ ሥራ ፅሑፍ (Crative Writing) ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡ ስነ-ጽሑፍ የተወሰነ ዕዉቀት ለማስተላለፍ፣ እንዲህ አድርግ አታድርግ እያለ ለማዘዝ፣

አዋጅ ለማስነገሪያ የሚያገለግል መሣሪያ ሳይሆን አዕምሮን ለማነቃቃት መንፈስን ለማነሳሳት የሚፃፍ የፈጠራ ዉጤት ነዉ፡፡

በስነ-ጽሑፍ የሚነገረዉ በእዉኑ ዓለም የሆነ የተደረገና የተሰራ ብቻ ሳይሆን ሊደረግና ሊሰማ የሚችል የደራሲዉ የምናብ ዉጤት ነዉ፡፡ በመሆኑም ስነ-ጽሑፍ ጋዜጣዊ ዘገባ፣ ታሪክ ወይም በአንድ በትክክል የተፈፀመ ድርጊት እንዳለ ፈጦ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ይልቁንም በልዩ ልዩ ቦታዎች በተለያዩ ጊዜያትና ሰዎች ከተፈፀሙ ድርግቶች ተነሰቶ ደራሲዉ የህይወት ልምዱን በምናቡ በፈጠራቸዉ ገፀ-ባህርያት አማካይነት የሚያንፀባርቅበት የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነዉ፡፡ ይህንን ሁኔታ አሰመልክተዉ መላክነህ (1990፣9-10) እንደሚከተለዉ ያስረዳሉ፡፡

> ስነ-ጽሑፍ የሰዉን ልጅ ጉዳዩ ያደረገ፣ ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊ ነገሮችን ለማግባባት የሚያገለግል የምናባዊና የፈጠራ ሥራ ነዉ፡፡ ልቦለዳዊነቱም ምናባዊነቱም ትርጉማዊነቱም፣ የአገላለፅ ስልቱና ስሜት ሰጪነቱ መለያዉ ናቸዉ፡፡ እንደታሪክ ፀሐፍት በትክክል የተደረገዉን ምክንያት የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ በትክክል የተደረጉ ወይም የሆኑ ነገሮችን የመቅረጽና የማደራጀት ነፃነት አለዉ፡፡ ከሚኖርበት ዘመን አርቆ ይከሰት ይሆናል፣ ይሆን ይሆናል ብሎ በልቡ ያሰበዉን በቋንቋ ወይም የተነበየዉን መጻፍ ይችላል፡፡

ስነ-ጽሑፍ እዉነተኛ ግብዓት የሆነ፣ ባህልና በቋንቋ የበለፀገ፣ ቋንቋ ለማስተማር ተገቢነት አጓጊነት ያለዉ፣ በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚያሣድግ እንዲሁም ከስነ-ጽሑፍ ጋር ጥብቅ የሆነ ትስስር እንዲኖረዉ የሚያስችል መሆኑን Collie and Slatter (1987) ይገልፃሉ፡፡ Richards and Yalden (2014) Hotway et.a l(2002)ን በመጥቀስ ስነ-ጽሑፍ ተማሪዎች ቋንቋን ከእዉዱ እንዲገነዘቡ እንዲሁም የቋንቋን የተለያየ አጠቃቀም እንዲያዉቁ በዕለት ከዕለት ህይወታቸዉ ዉስጥ ያለዉን ማህበረሰብ ማህበራዊ ጉዳይ እንደ ስዕል የሚያሣይ በመሆኑ የቋንቋዉን ተፈጥሯዊ አኳኃን በመጠበቅና ተገቢ በሆነ መልኩ ለመግለጽ የሚያስችል ነው፡፡ በአጠቃላይ ስነ-ጽሑፍ በቋንቋ አማካይነት ለመግለጽ የተፈለገዉን ሃሳብ ግልጽና የተሟላ እንዲሁም ስዕላዊ በሆነ መልኩ ለአድማጭ ወይንም ለአንባቢ የሚቀርብበት መንገድ ነው፡

### 2.1.2 ስነ-ፅሁፍ በትምህርት ዉስጥ ያለዉ ሚና

ስነ-ፅሁፍ የዓለማችን ልዩ ልዩ ገፅታዎችን ለማሳየትና ለሚፈጠሩ ችግሮች መልስ ለማግኘት ድርሻዉ የላቀ ነዉ፡፡ በአንድ ሀገር የትምህርት ስርዓት ዉስጥም ስነ-ፅሁፍ መካተቱ የተማረዉን ኃይል ለማብዛትና ሀገሪቱን ለማሳደግ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለዉ Brumfit,CJ. And R.A.Carter (1986) ይገልፃሉ፡፡ ስነ-ፅሁፍ በትምህርት ዉስጥ ያለዉን ጥቅምም እንደሚከተለዉ አያይዘው ያብራራሉ፡፡

**1. ክሂልን ለማዳበር**

ስነ-ፅሁፍ በትምህርት ዉስጥ መካተቱ ተማሪዎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በቀላሉ ለማዳበር ያስችላቸዋል፡፡ በተለይም የማንበብ ክሂልን በከፍተኛ ደረጃ የሚያዳብር ሲሆን የማዳመጥ፣ የመናገርና የመፃፍ ክሂልን ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ እንዲያዳብሩ ያግዛል፡፡ ተማሪዎች አጫጭር ልቦለዶችን፣ ግጥሞችንና ተዉኔቶችን ሲያነቡ ሳቢ በመሆናቸዉ ቀልብና ስሜታቸዉን በመግዛት የመናገርና የማንበብ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፡፡

**2. ዕዉቀትን ለማካበት**

ስነ-ፅሁፍ የተለያዩ እዉቀቶችንና ባህሎችን የያዘ ነዉ፡፡ እንዲሁም በሰዉ ልጅ ልዩ ልዩ የህይወት ገጠመኝና አጠቃላይ ተፈጥሮ ላይ የሚያተኩር ነዉ፡፡ ስለዚህም አንድ ሰዉ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን (ድርሰቶችን) አነበበ ማለት በተለያዩ የእዉቀት መስኮች በለፀገ ማለት ነዉ፡፡

**3. የአእምሮ ዕድገትን ለማምጣት**

ትምህርት ከክሂልና እዉቀት ባሻገር ከእያንዳንዱ ተማሪ ስብዕና፣ ችሎታ፣ ችግርና እድገት ጋር የተዛመደ ነዉ፡፡ የሰዉ ልጅ የአእምሮ ክፍል ዕድገት ዉስንነት ሊታይበት ይችላል፡፡ ስለሆነም የሰዉ ልጅ የተሟላ ስብዕና እና እድገት እንዲኖረዉ ደግሞ የአእምሮ ክፍሎች ቅንጅታዊ እድገት መኖር የግድ ይላል፡፡ በትምህርት የሚያድጉ የአእምሮ ክፍሎች ስሜታዊና አካላዊ (Sensory Motar) የዕዉቀት (Intellectual) መንፈሳዊ (Affective or Felling) ማህበራዊ (Social) እና ሐይማኖታዊ (Religon) ናቸዉ፡፡ እነዚህ የአእምሮ ክፍሎች በተመሳሳይ ደረጃ ለማሳደግ የሚረዱ መረጃዎችን በማቅረብ ረገድ ስነ-ፅሁፍ ከየትኛዉም የትምህርት ዓይነት የላቀ ጠቀሜታ አለዉ በማለት በድሉ (1996) Ajzen (1988)ን በመጥቀስ ይገልፃሉ፡፡

### 4. የባህሪ ለዉጥ ለማምጣት

አንድ ሰዉ በተገቢ መንገድ ተምሯል የሚባለዉ የቀለም ትምህርቱ ዕዉቀት በህይወቱ አስተምረዉ የሚያልፉ ልዩ ልዩ ሁነቶችን፣ ዕዉቀቶችን ከባህሪ ለዉጥ ጋር ተጣምሮ ሲኖረዉ ነዉ፡፡ ነገር ግን ዕዉቀት ያለባህሪ ለዉጥ አዋቂ ሊያስብል አይችልም፡፡ ያካበተዉ ክሂልና ዕዉቀት የደረሰበት የአእምሮ ዕድገት የግለሰቡን የአሰራር ባህሪ መለወጥ አለበት፡፡ "ግለሰቡ ክሂሉን፣ እዉቀቱንና የአእምሮ ብስለቱን ካገኘ በኋላ ከቀድሞዉ የአሰራር ባህሪው ካልተቀየረ ሶስቱም እንዳሉ አይቆጠሩም፡፡ ቢኖሩም የሉም"፡፡ ስነ-ፅሁፍ በትምህርት ዉስጥ መካተቱ ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ ይቀይራቸዋል ማለት ሳይሆን በርካታ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ያነበበ "ጥሩ" ምንም ያላነበበ ወይም ጥቂት ያነበበ" መጥፎ" የአሰራር ባህሪ ለዉጥ ይታይባቸዋል ማለት ነዉ በማለት በድሉ (1996) ይገልፃሉ፡፡

### 2.1.3 ስነ-ፅሑፍን በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ያለዉ ጠቀሜታ

ቀደም ሲል የስነ-ፅሁፍ አጀማመርን፤ በስርዓተ ትምህርት ሊካተት የቻለበትን ሂደት አስመልክቶ የምሁራንን ሃሳብ በማስደገፍ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በማስከተል ስነ-ፅሁፍ ለቋንቋ ትምህርት ያለዉን አስፈላጊነት (አስተዋፅኦ) እንቃኛለን፡፡

#### 2.1.3.1 ስነ-ፅሑፍ እዉነተኛ ቋንቋ የሚጠቀም ዋጋ ያለዉ ሥራ መሆኑ

አብዛኛዎቹ የቋንቋ ማስተማሪያ መፅሐፍት ለየክፍል ደረጃዉ በሚመጥኑ ሁኔታ የተዘጋጁ ምንባቦችን ያቀፉ ናቸዉ፡፡ የሚዘጋጁ ምንባቦችም የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ዕድሜና የቋንቋ ችሎታ ከግንዛቤ ያስገቡ መሆን አለባቸዉ፡፡ ምንባቦቹም በሁለት መንገድ የሚዘጋጁ ሲሆን እነሱም፡- የተፃፉትን ለተፈለገዉ ደረጃ እንዲመጥኑ አድርጎ እንደገና መፃፍ እና የተማሪዎቹን ደረጃ ያገናዘበ አዲስ ፅሁፍ ማዘጋጀት ናቸዉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የቋንቋ ተፈጥሯዊ ባህሪ ይገድባል፡፡ መቼም ሰዎች በቋንቋ ሲግባቡ መሰረታዊ ጉዳዩ የሚተላለፈዉ መልዕክት እንደሆነ ግልፅ ነዉ (በድሉ፣ 1996) በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መሠረት የተፃፉትን ለተፈለገዉ ደረጃ እንዲመጥኑ አድርጎ እንደገና በመፃፍም ሆነ የተማሪዎችን ደረጃ ያገናዘበ አዲስ ፅሁፍ ማዘጋጀት ሆን ተብሎ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጁ ምንባቦች ከፅሁፉ መልዕክት በበለጠ በቃላት መረጣና ዓረፍተ ነገር መረጣ ላይ ያተኩራሉ፡፡ በእዉነተኛ ተግባቦታዊ አዉድ ቋንቋ መልዕክት ለማስተላለፍ ሲዉል በእነዚህ ምንባቦች ዉስጥ ግን

በተወሰነ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ቃላትና ሰዋሰዉን ለማስተማር ይዉላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚዘጋጁ ፅሁፎች የቋንቋዉን ተናጋሪ እዉነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም አያሳዩም የሚባለዉ፡፡ ስለሆነም ስነ-ፅሁፍ የሚዘጋጀዉ ተዝናኖትን ለመፍጠር ስሜትን በሚያዝ መንገድ የሚቀርብ ነዉ፡፡ ይህም በተደራሲዉ ዘንድ ምናባዊ ደስታን ለማግኘት ደራሲዉ በተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ተደራሲያንን በምናብ ፈጠራዉ የሚያገኝበት ሂደት ነዉ፡፡ በዚህ ሂደት "ደራሲዉ የሚፅፈዉ ህይወትን ነዉ ህይወት ደግሞ በድርጊት ብቻ ሳይሆን በቋንቋ አጠቃቀም ይንፀባረቃል፡፡ እዉነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም የአንድን ህብረተሰብ ሃሳብ ከባህሉ ጋር አመሳጥሮ ያቀርባል፡፡" በማለት በድሉ (1996) ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም ስነ-ፅሁፍ ቋንቋን የበለጠ ለመረዳት የሚያስችል የተማሪዉን ዉስጣዊ ስሜት በመቀስቀስና በማነሳሳት ሰፊ ንባብ እንዲያነቡ ያደርጋል፡፡ ተግባቦትንም ያሳድጋል በማለት ስነ-ፅሁፍ በቋንቋ ትምህርቱ ዉስጥ ያለዉን ሚና በተመለከተ Hall (2005) ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ዝርዝር ሀሳቦች የምንገነዘበዉ ስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ እዉነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ያለዉ ማስተማሪያ መሳሪያ መሆኑን ነዉ፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን ስነ-ልቦና በመግዛት የቋንቋ ትምህርቱን በተገቢዉ መንገድ ማከናወን እንዲችሉ ደስታን በመፍጠር ተግባቦታቸዉንም እንደሚያሳድግ ነዉ፡፡

### 2.1.3.2. ስነ-ፅሑፍ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ መሆኑ

ቋንቋ የሰዉ ልጅ ባህላዊ እሴቶች ይገለፁበታል፤ የማህረበረሰቡን ስሜትና ሐሳብ፣ አለባበስና አመጋገብ፣ ጀግንነትና ፍርሀት፣ ደስታና ሀዘን፣ ወዘተ ያሳያል፡፡ ይህም ለአንባቢዉ ስነ-ፅሁፍ ስለተፃፈበት ህብረተሰብ ተጨባጭ የሆነ ምስል ይፈጥርለታል፡፡ ስለአንድ ማህበረሰብ ያለፈ ታሪክ ማንበብ በወቅቱ እንዴት ይኖሩ እንደነበርና የደረሱባቸዉን የስነ-ፅሁፍ ዕድገትና ስልጣኔ እንድናዉቅ ያደርገናል፡፡ ወግና ባህላቸዉንም ያሳዉቀናል፡፡ ይህም ቋንቋ ለመማር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል (Zen፣ 2012)፡፡ የሰዉ ልጅ በልቦለድ፣ በአጭር ልቦለድ፣ በግጥም፣ በድራማ አማካኝነት በእዉነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ባህሉን ይገልፃል፡፡ ስለሆነም ባህል በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ መካተቱ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ከአፍ ፊት ተማሪዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነትን እንዲፈጥሩ ያስችላል (በድሉ፣ 1996)፡፡ አያይዘውም "ስነ-ፅሁፍ የአንድን የህብረተሰብ ክፍል የተወሰነ መልክ ወይም ግንኙነት ብቻ ለይቶ አያቀርብም፡፡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ጉዳዮች ዉስጥ

የሚኖራቸዉን ግንኙነት ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ አንባቢዉን ከተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞች ጋር እንዲተዋወቅ ያደርገዋል፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከቀረበዉ ገለፃ መረዳት የሚቻለዉ የሰዉ ልጆች ባህል በቋንቋ ይገለፃል፣የተለያዩ ህብረተሰቦችን ባህል ለመግለፅ ደግሞ ሰዎች አጫጭር ታሪኮችን፣ልቦለዶችን፣ግጥሞችንና ድራማን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ የህዝቦች ባህል የተንፀባረቀባቸዉ የስነ-ፅሁፍ ስራዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርብበት ጊዜ ለተማሪዎች የባህል እዉቀትን ያስገኛሉ፣የመረዳት ችሎታቸዉም ይሰፋል፡፡ ስለ ሚያነቡት ማህበረሰብም የቀደመ የአኗኗር ዘይቤ፣የስልጣኔ ደረጃ፣የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ የቃላት አጠቃቀም እንዲያዉቁ ይረዳል፡፡ በዚህ ሂደት የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችና የሀሳብ አገላለፆችን፣ትርጓሜ አሰጣጥን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል (Lii፣ 2011)፡፡

በአጠቃላይ ከቀረቡት ገለፃዎች መገንዘብ የሚቻለዉ በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር ተመራጭ ነዉ፡፡ የስነ-ፅሁፍ ስራን ተማሪዉ የሚያደንቀዉ በገፀ-ባህሪያቶች አማካኝነት የሚተላለፈዉን ታሪክ ነዉ፡፡ ይህ ታሪክ ደግሞ የገሀዱ ዓለም እዉነት ሲሆን በዋናነት ባህልን ነዉ የሚገልፀዉ፡፡ ምክንያቱም ባህል የህዝቡን ሁነቶች ይይዛልና ይሄም የህዝቡን የቋንቋ አጠቃቀም፣ ወግ ልማዳቸዉን፣ ደስታና ሀዘን፣ የዕዉቀት ደረጃን፣ የስልጣኔ ሁኔታን ወዘተ ያካትታል፡፡ እንዲሁም ለቋንቋ ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ፅሁፍ አንብቦ ለመረዳት በዉስጡ ያሉትን የቋንቋ አጠቃቀሞች በቀለለ መንገድ ለመረዳት ስነ-ፅሁፍ ይረዳቸዋል፡፡

### 2.1.3.3. ስነ-ፅሑፍ ግላዊ ተሳትፎን የሚያዳብር መሆኑ

ስነ-ፅሑፍ የተማሪዎችን ዉስጣዊ ፍላጎት በመቀስ ቀስ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎአቸዉ ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡ "ስነ-ፅሑፍ ከሰዉ ህይወት ተቀድቶ፣ በሰዉ ተዘጋጅቶ መልሶ ለሰዉ የሚቀርብ ነዉ" (ዘሪሁን፣ 1992)፡፡ በመሆኑም የሚያጠነጥነዉ ስለ ሰዉ ልጅ ህይወት ወይም ገጠመኝ ስለሆነ ሁሉንም ሰዉ ለማስተማር ያገለግላል፡፡ ሰዎች ስላነበቡት ነገር ትርጉም ሊመራመሩ፣ አስተያየትና ሀሳብ ሲሰጡ፣ ሲወያዩ የማመዛዘን፣ የተግባቦት፣ የመከራከር ነገሮችን የመረዳት ችሎታቸዉ ይጨምራል የአስተሳሰብ አድማሳቸዉም ይሰፋል በማለት (Lazar፣ 1993) የስነ-ፅሑፍን ጠቀሜታ ይገልጻሉ፡፡ አያይዘውም ስነ-ፅሁፍ በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ የተሻለ የሚያደርገዉ ሌላዉ ነጥብ ተማሪዎች እራሳቸዉን የክዋኔዉ ተሳታፊ አድርገዉ እንዲያስቡ ማድረጉ ነዉ፡፡ ለቋንቋ ትምህርት የሚቀርብ ይዘት በህግና ስርዓት የታሰረ ነዉ፡፡ ስለዚህም የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎቹ

በብዛት ትኩረታቸዉ አገባብና ሰዋሰዋዊ ህግ ላይ ነዉ፡፡ ስነ-ፅሁፍ ግን ከዚህ በተለየ መንገድ ተማሪዎች በቋንቋዉ መግባባት እንዲችሉ ማድረግ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ሁኔታም ተማሪዎች አጭር ልለድን፣
ተዉኔትን፣ ግጥምን ወዘተ በሚያነቡበት ጊዜ የታሪኩ ተሳታፊ የመሆን ድባብን ይፈጥራሉ፤ ታሪኩንም ከቀደመ ዕዉቀታቸዉ ጋር በማዛመድ ይረዱታል፡፡ ይህም የግል ተሳትፏቸዉን ያዳብራሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ቋንቋን ለማስተማር ስነ-ፅሁፍን መጠቀም በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ይኸዉም የተሻለ የቋንቋ አጠቃቀም ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል፣ የፈጠራ ችሎታችንን ያሳድጋል፣ ትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ እንዲኖረን ያደርጋል (Callie & Slater፣ 1987፤ Ramsaren፣ 1983)፡፡ እንዲሁም የምናብ አድማስን ያሰፋል፣ የፈጠራ ችሎታቸዉንም ለማሻሻል ወሳኝ ነዉ፡፡ ዉስጣዊ ስሜትንና የተማሪዉን የትምህርት ግንዛቤ ያሳድጋል (Lazar፣ 1993)፡፡ ንባብ የቋንቋ ተማሪ የቃላት ዕዉቀትን፣ ትርጉምንና የቃላት አጠቃቀምን እንዲያዉቅ ስለሚረዳዉ አስቀድሞ ከሚያዉቃዉ ቃላት በተጨማሪ ከስነ-ፅሁፍ ያገኛቸዉንም በመጠቀም ራሱን ያስደስትበታል (Brumfin and Carter፣ 1986)፡፡ ተማሪዎች በብዛት የቃላት ዕዉቀታቸዉን የሚያዳብሩት በሰፊ ንባብ ነዉ፡፡ የተማሪዉ የቃላት ብቃት ማደግ የንባብ ችሎታቸዉን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ (Krashen፣ 1989፤ Coody፣ 1997፤) ነው፡፡

ስነ-ፅሁፍ ለማስተማሪያነት ጠቃሚ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች እንዲጠይቁ፣ እንዲተረጉሙ፣ ተራክቦ እንዲፈጥሩ እና እንዲሄሱ (እንዲያሄሱ) ያስችላቸዋል፡፡ እንዲሁም የቋንቋ ብቃታቸዉን ብቻ ሳይሆን የሌላዉን ማህበረሰብ ወግና ባህል ለማስተማር ይረዳል (Elliot፣1990)፡፡ አያይዘውም ደግሞ ስነ-ፅሁፍ ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ በከፍተኛ ደረጃ ከራሳቸዉ ጋር እንዲያሰርፁትና እንዲያዋህዱት ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ጠቃሚ ነዉ ይላሉ፡፡ በሌላ ጎን ደግሞ ስነ-ፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ የመጠቀም ዓላማ ተማሪዎችን በክፍል ዉስጥ ያላቸዉን ግንኙነት በማዳበር የግንኙነት ችሎታቸዉን እንዲያሻሽሉ በአእምሮአቸዉ ዉስጥ ዘላቂ ተፅዕኖ መፍጠር ነዉ (Koutsompou፣ 2015)፡፡ በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር የተለያዩ ጥቅሞች አሉት እነዚህም የማህበረሰቡን ወግና ባህል ያሳዉቃል፣ በዓለማችን ላይ ያሉትን ዕዉቀቶች እንድንረዳ /እንድናዉቅ/ ያስችላል፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ያሳድጋል እንዲሁም በትምህርታቸዉ ንቁ ተሳታፊ

እንዲሆኑ ያበረታታል (Collie & Slater፣ 2005)፡፡

### 2.1.4 ለቋንቋ ተማሪዎች የሚመረጡት የስነ-ፅሁፍ አሃዶች

የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ለማስተማር በምንመርጥበት ጊዜ ሶስት ዋና ዋና ተግባራትን ማጤን አለብን እነሱም የምናስተምረዉ ትምህርት፣ የተማሪዎቹ ሁኔታና ከገአሃዱ ዓለም ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች ናቸዉ (Lazar፣ 1993)፡፡

**1. ስነ-ፅሑፋዊ ስራዉ ከቋንቋ ትምህርት ዓላማ ጋር የተዛመደ መሆን**

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎችና ሁለቱን የዕዉቀት ዘርፎች ማጎልበት ነዉ፡፡ ከሁለቱ የዕዉቀት ዘርፎች አንዱ ደግሞ ስነ-ፅሁፍ ነዉ፡፡ በመሆኑም ስነ-ፅሁፍን ለቋንቋ ትምህርት ስናዉለዉ መምረጥ የሚገባን ከቋንቋዉ ትምህርት ዓላማ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሲሆን በመርሃ ትምህርቱ የታቀፉትን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ያደርስልናል (Lazar፣1993)፤ እንዲሁም (Gehosen፣2002) ስነ-ፅሑፍ የቋንቋ ትምህርትን ያሳምራል፣ በአገባቡም የቃላት ትምህርትን ማስተማር ያስችላል፤ በአጠቃላይ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ጥሩ አማራጭ ነው ፡፡

## 2. ስነ-ፅሁፋዊ ስራው ከተማሪዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑ

ለማስተማሪያነት የሚመረጠዉ ስነ-ፅሁፍ ተማሪዎችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ የሚመረጠዉ ስነ-ፅሁፍ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማሻሻል እስከሆነ ድረስ ዓላማዉን መሰረት አድርገን መምረጥ ይገባናል፡፡ ስለዚህም ተከታዮቹን ዝርዝር ጉዳዮች ከግንዛቤ ማስገባት አለብን (Lazar፣ 1993)፡፡

**ሀ. የተማሪዎችን ዕድሜ ያገናዘበ ሥራ መምረጥ**

ሰዎች ዕድሜያቸዉ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ፍላጎታቸዉና ስሜታቸዉ እየተቀያየረና እያደገ የሚሄድ ስለሆነ ጎን ለጎንም የአስተሳሰብ አድማሳቸዉ እየሰፋ ሊመጣ ይችላል፡፡ ከዚህም የተነሳ ለህፃናት የሚዘጋጀዉ ስነ-ፅሁፋዊ ስራ ለአዋቂዎች የማያስደስት፣ ለወጣቶች የሚማርክ ደግሞ ለጎልማሶች የማይጥም ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም ለልጆች በዕድሜያቸዉ ልክ የሚመጥኑ ተረቶችና ቀለል ያሉ ስራዎች ሊመረጡ ሲችሉ፣ ለአዋቂዎች ደግሞ በደረጃቸዉ ልክ ሊያመራምሩና ሊረዱት የሚችሉትን ስነ-ፅሁፋዊ ስራ መምረጥ (Lazar፣ 1993)፡፡

**ለ. የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ያገናዘበ ሥራ መምረጥ**

ተማሪዎች በሚኖሩባቸዉ ማህበረሰቦች ዉስጥ በርካታ ባህሎች አሉ፡፡ ስለሆነም በአንዱ ባህል ተቀባይነት ያለዉ ጉዳይ በሌላዉ ማህበረሰብ የተወገዘ ይሆናል፤ ለአንዱ ነዉር

የሆነዉ ለሌላዉ ችግር የሌለዉና ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በአገራችንም በርካታ ባህሎችን የሚከተሉ ተማሪዎችን በአንድ ትምህርት ቤት ዉስጥ ማስተማሩ የተለመደ ነዉ፡፡ Lazar (1993) እና በድሉ (1996) እንደሚገልፁት የተማሪዎች ባህላዊ ዳራና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ግምት የቀረበዉን የስነ-ፅሁፍ ስራ ለመረዳት ወይም ላለመረዳት የሚያስችል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የተለያዩ ባህላዊ ዳራ ያላቸዉን ተማሪዎች በአንድ ክፍል ዉስጥ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታም ይኖራል፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ መምህሩ የሚመርጠዉ ስነ-ፅሁፋዊ ስራን በጥንቃቄ ሊያየዉና ሊያጤነዉ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የተማሪዉን የባህል ዳራ ያገናዘበ ስራ ስለሆነ የሚመርጠዉ፣ መምህሩ ስነ-ፅሁፉን ሲመርጥ የተማሪዎችን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ አንዱን ከሌላዉ የማያበላልጥ መሆን አለበት። Gehosen (2002) ደግሞ የሚመረጠው ስነ-ፅሁፍ ዓለማቀፋዊ ይዘት ያላቸውን ጭብጦች የሚያነሳ መሆን አለበት በማለት ይገልፃል፡፡

**ሐ. የተማሪዎችን የቋንቋ ሁኔታ ያገናዘበ ሥራ መምረጥ**

ለተማሪዎች የምንመርጠዉ ስነ-ፅሁፋዊ ስራ በጣም የከበደ ወይም በጣም የቀለለ መሆን አይገባዉም፡፡ የሚመረጠዉ አሃድ የተማሪዉን ዕድሜና ዕዉቀት ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ ከዚህ በፊት ያነበቡት የስነ-ፅሁፍ ስራ መጠንና የተማሪዎቹ የማንበብ ፍላጎት የምንመርጠዉን አሃድ ጥልቀትና ስፋት ይወስነዋል (Lazar፣1993)፡፡ በድሉ (1996) እንዳብራሩትም ለቋንቋ ትምህርት የተመረጠ የስነ-ፅሁፍ ስራ የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃ ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

**መ. ሳቢ ስራ**

ለማስተማሪያነት የሚቀርበዉ የስነ-ፅሁፍ ስራ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚያሳድግ መሆን አለበት፡፡ የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ደግሞ ከሚመረጠዉ ስራ ሳቢ መሆን ወይም አለመሆን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለዉ፡፡ ስለዚህም የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት ገዝቶ የያዘ ስራ ሳቢ ስለሆነ የተማሪዉን ግላዊ ተሳትፎ ከፍ ያደርገዋል (በድሉ፣ 1996) እና (ዘሪሁን 1996)፡፡

**ሠ. ስነ-ፅሑፋዊ ሥራዉን በተመለከተ ያላቸዉ ዳራዊ ዕዉቀት**

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዉ እንዴት ተፃፈ? ለምን ተፃፈ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ከቻልንና ቀድመን ለተማሪዎቻችን ካሳወቅን ተማሪዎቹ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዉን የመረዳት ብቃታቸዉና ለማንበብ ያላቸዉ ፍላጎት ይጨምራል፡፡ ይህም ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይረዳል፡፡ ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ዳራና የቋንቋ ብቃታቸዉ ጥሩ

የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንድን ስራ ስንመርጥ ማየት ያለብን የቋንቋውን ደረጃ ብቻ ሳይሆን የስነ-ፅሁፍ ጥራቱንም ጭምር መሆን ይገባዋል (Lazar፣ 1993)፣ በድሉ(1996)፡፡

## ረ. ከስነ-ፅሑፍ ሥራዉ ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች

Lazar (1993) እንደገለፁት ለቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያነት ስነ-ፅሁፋዊ ስራን ስንመርጥ ሌሎች ከግምት ዉስጥ ሊገቡ የሚገባቸዉ ጉዳዮች የስነ-ፅሁፉ በበቂ ሁኔታ መገኘት፣ ስረዉ ለአጠቃቀም የሚመች መሆንና ከቋንቋ ትምህርቱ መርሃ ትምህርት ጋር ያለዉ የተቀራራቢነት ደረጃ የሚሉት ናቸዉ፡፡ ዘመንፈስ (1991) Wiliam (1986)ን ጠቅሰዉ እንደገለፁት ለቋንቋ ትምህርት የሚያገለግሉ አሃዶች በሚመረጡበት ጊዜ ቅድሚያ መስጠት ያለበት አሃዶቹ ለቋንቋ ትምህርት በሚሰጡት ፋይዳ ላይ እንጂ በምንባቦቹ ይዘት ባይሆን ይመረጣል፡፡ አክለዉም በየክፍል ደረጃዉ የሚቀርቡት አሃዶች

ተቀዳሚ ዓላማ ተማሪዎች የአሃዶቹን ይዘት ተረድተዉ በመተግበር ላይ ሳይሆን በስርዓተ ትምህርቱ ዉስጥ ላሰፈረዉ ዓላማ ማሳኪያ እንዲዉሉ ለማድረግ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት ሃሳብ የምንረዳዉ የስነ-ፅሁፍ ስራን ለማስተማሪያነት በምናዉልበት /በምንመርጥርበት/ ጊዜ ስራዎቹ ሳቢ መሆን እንዳለባቸዉ ሲሆን ይሄም ተማሪዉ በደስታና በንቃት ስራዉን እንዲያነብ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም አንድን የስነ-ፅሁፍ አሃድ ስንመርጥ የተማሪዎችን ዕድሜ ከግንዛቤ ዉስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤ ማለትም ለወጣቱ ምን ያስፈልገዋል ለልጆችስ የትኛዉ ስራን ብንመርጥ አዋጪ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴዉን አከናዉናለሁ፣ የተማሪዉ የቋንቋ ሁኔታስ ምን ያህል ነዉ? የትኞቹን ቃላት አጠቃቀምን መረዳት ይችላሉ፤ የትኛዉስ ይከብዳቸዋል (መረዳት አይችሉትም) የሚሉትን ከግንዛቤ ዉስጥ ማስገባት የመምህራኑ ተቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት፡፡ ባጠቃላይ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ተጠቅመን በተማሪዎች ላይ የተፈለገዉን ለዉጥ ለማምጣት ከላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦችና ተግባራት ተከትለን በጥንቃቄ መምረጥ እንዳለብን ነዉ፡፡

### 2.1.5 የአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህሪያት

የአጭር ልቦለድ ዘዉግ ከ19ኛዉ ክፍለ ዘመን በፊት እንደተለየ ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡ ይህ የጥበብ ዘዉግ አለም አቀፋዊና ከመጀመሪያዎቹ የሰዉ ልጆች እስከ ዘመናዊ ሰዉ ድረስ ስለቀጣዮቹ ትዉልዶችም የሚያወሳ ነበር፤ ከትረካ ይልቅ ስሜት መፍጠር ላይ

ማተኮሩ አጭር ልቦለድ ከሌሎቹ ዘዉጎች የተለየና ጠቃሚ ያደርገዋል፡፡ ሰዎች በህይወታቸዉ ለተለያየ ዓላማ አጫጭር ታሪኮችን በሰፊዉ ያነባሉ፡፡ ለምሳሌ፡-ተረት ተረት፣ አጫጭር ልቦለዶች እና በመፅሐፉ ዉስጥ የተደበቀ የዘመናት ጥበብ ግንዛቤን ለማዳበር ህዝቡን በልዩ ልዩ ዘይቤና የትረካ ቴክኒኮች ማዝናናትና ማስተማር ነዉ፡፡ ኤድጋርአለንፖ ስለአጭር ልቦለድ ፍቺ ሲገልፁ "በአንድ ግማሽ ሰዓት ወይም ሁለት ሰዓት ተቀምጦ የሚነበብ ትረካ እና በተወሰነ ነጠላ ዉጤት የተገደበ ነዉ" ሲል Abrham (1970) ይገልፃሉ፡፡

አጭር ልቦለድ በገሃዱ ዓለም ላይ የሚፈጠሩና ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳዮችን በዕለት ተዕለት ህይወታችን ዉስጥ የሚስተዋሉ ሁነቶችን ባህላዊ እሴቶችን የሚያቀርብ ኪነ-ጥበብ ነዉ፡፡ ይህም ምናባዊነት የሚስተዋልበት፣ አንድን ድርጊት አጉልቶና አግዝፎ የሚያሳይ ታሪክ ያለዉና በጥቂት

ገፀ-ባህሪያት ትስስር ነጠላ ዉጤትን የሚያስተላልፍ፣ ነጠላ መቼት ያለዉ፣ ግልፅ በሆነ ገለፃ የሚቀርብ መሆኑን Lazar (2009) እና Abrhams (1970) ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ አጭር ልቦለድ ፈጣን የሆነ፣ በድርጊቶች የተሞላ ገጠመኞችን የያዘና አንድ ብቸኛ የትኩረት ነጥብን በማንሳት እሱን ለመቋጨት የሚንደረደር አጓጊና ሳቢ የልቦለድ ዓይነት ነው (ዘሪሁን፣ 1992)፡፡ አጭር ልቦለድ ነጠላ ዉጤት ዋነኛ ባህሪዉ የሆነ የአንባቢያንን አእምሮ ገዝቶ የሚይዝ ያልተወሳሰበ እና በተሻለ መንገድ የፅሁፉን መልዕክት ለመረዳት የሚያስችል ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ ጥድፊያ ሲሆን ያነሳዉን ታሪክ ብዙም ሳያወሳስብ የታሪኩን ፍሰት በጠበቀ መንገድ አብዛኛዉ የልቦለድ አላባን ነጠላ በሆነ አቀራረብ የሚያቀርብና የሚያጓጓ አንባቢያን ሳይሰለቹ በደስታ እንዲያነቡት የሚያደርግ ነዉ፡፡ የመጨረሻዉ የአጭር ልቦለድ ባህሪ ቁጥብነት ነዉ፡፡ ይህም ከሌሎቹ አላባዉያን ጋር በመቀናጀት በተወሰኑ ቃላት ያነሳዉን ታሪክ አንባቢያን እንዲረዱት የሚያስችልና ሳይሰለቹ በጉጉት እንዲያነቡት የሚያስችል ነው፡፡ የቃላቱ መጠን ከአስራ አምስት ሺህ የማይበልጥ እንደሆነና በገፀባህሪያቱ አማካኝነት የማህበረሰቡን አኗኗርና አካባቢ ለመረዳት የሚያስችል ነዉ (ዘሪሁን፣ 1992)፡፡

### 2.1.6 አጭር ልቦለድ ቋንቋን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

አጭር ልቦለድም ቋንቋን ለማስተማር በጣም ጠቃሚ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ነጠላ ዉጤትን፣ አንድ ሴራን፣ ጥቂት ገፀ-ባህሪያት ስላሉትና ስለሚስቡ የመማር ፍላጎትን ያነሳሳል፣ የማንበብ ፍላጎታቸዉንም ይጨምራል፡፡ ይህ ሂደትም የንባብ ችሎታቸዉ

እንዲሻሻል ያደርጋል (Saka፣ 2014፤ Pardede፣ 2011፤ Vural፣ 2013)፡፡ አጭር ልቦለድ ቋንቋን ለማስተማር ከሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘዉጎች ተስማሚና ተመራጭ መሆናቸዉን Collie and Slater (1987) ይገልፃሉ፡፡ አጭር ልቦለድ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ተመራጭ ያደረገዉ አጭር ልቦለዶች ርዝመታቸዉ አጭር ስለሆነ ተማሪዉ በአንድ ወይም በሁለት ክፍለ ጊዜ የሚያጠናቅቁት (የሚሸፍኑት) መሆኑ፣ ተማሪዎች በራሳቸዉ ተነሳሽነት እንዲያነቡትና እንዲረዱት የሚያስችል መሆኑና ዉስብስብ ያለመሆኑ፣ አጭር ልቦለዶች በዉስጣቸዉ የተለያዩ አማራጮችን በመያዛቸዉ አንባቢዎች የፈለጉትን መርጠዉ እንዲያነቡ መቻላቸዉ እና እንዲሁም በሁሉም የዕድሜ ክልል የዕዉቀት ደረጃ መነበብ የሚችል መሆኑ እንደሆነም አያይዘው ይገልጻሉ፡፡

የፅሑፉ አጭር መሆን ለተማሪዎቹ ጠቃሚ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የታላሚዉን ቋንቋ ፅሁፍ ማንበብ፣ መረዳት እና መጨረስ እንደሚችሉ ስለሚመለከቱ (ስለሚገነዘቡ) ስኬትና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማቸዉ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም Hill (1994) እንደገለጹት ጽሑፍን ለመምረጥ ሌሎች ሶስት መሰረታዊ መመዘኛዎችን ይጠቁማል፡፡ እነዚህም የተማሪዎችን ፍላጎትና

ችሎታ፣ የፅሁፍ ቋንቋ እና የአፃፃፍ ደረጃ እና ለፅሑፉ እዉነተኛ አድናቆት የሚያስፈልገዉ (የሚያስገኝ) መረጃን የያዘ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህን መመዘኛዎች የማጤን አስፈላጊነት የሚጠናዉ አጭር ልቦለድ የቃላትና የዓረፍተ ነገር አወቃቀሩ ለተማሪዎቹ ደረጃ ተስማሚ መሆን እንዳለበት በመገንዘብ ነዉ (Hill፣ 1994)፡፡ አክለዉም Ur (1996) ሲገልፁ የሚመረጠዉ አጭር ልቦለድ የተማሪዎችን ደረጃ ያማከለ መሆን አለበት፡፡ ጎበዞችን ብቻ ከግምት ዉስጥ ያስገባ መረጣ መከናወን የለበትም፡፡ የሚመረጠዉ ፅሁፍ ዝቅተኛ የቋንቋ ችሎታ ያላቸዉንም ታሳቢ በማድረግ ቀለል ያለና ሳቢ ታሪኮችን መጠቀም ተገቢ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረበው ሀሳብ የሚያስረዳው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡት አጭር ልቦለዶች የተማሪዎችን የዕዉቀት፣ የዕድሜና የቋንቋ ችሎታ ከግምት ዉስጥ ያስገባ የአረፍተ ነገሮች እና የቃላት አጠቃቀምም ግልፅና አጭጫር መሆን እንዳለበት ነዉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ አጭር ልቦለዱን እንዲያነቡ በታሪኩ ዉስጥ የሚኖሩት ቃላት ጥንታዊ ያልሆኑ፣ ግራ የሚያጋቡና ጉራማይሌ ያልሆኑ መሆን እንዳለባቸዉ ነው፡፡

### 2.1.7 የምንባብ ምንነት

ንባብ ፀሐፊዉ በሌለበት በአንባቢዉ እና በፀሐፊዉ መካከል የሚካሄድ ተራክቦ ሲሆን ይህንንም ተራክቦ ለማከናወን ሁለት መንገዶችን መከተል አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከነዚህም የመጀመሪያዉ ንባብ ትርጉም መገመት እንዲችል የላይ-ታች (Top-Down) ሂደትና ይህንን ለማረጋገጥ የታች-ላይ (Bottom-Up) ሂደት መጠቀምን የሚጠይቅ አእምሮአዊ ተግባር ነዉ፡፡ ስለዚህም የፅሁፉን ሀሳብ ለመረዳት ሁለቱም ሂደቶች ተጣምረዉ የሚካሄዱ ናቸዉ (Berardo፣ 2006)፡፡

በተጨማሪም ማንበብ ደስታን የሚፈጥር፣ ጥልቅና ግላዊ ክንዉንና ጥረትን የሚጠይቅ ነዉ (Alderson፣ 2000)፡፡ ይህ ትርጉም ደግሞ የሚነበበዉ ፅሁፉ የአንባቢዉ የቀደመ ዕዉቀት፣ ቃላትን የማፍለቅ ብቃት፣ ካለዉ መረጃ ጋር ማገናዘብና ሃሳቦችን የማዛመድ ዉጤት ነዉ በማለት የላይኛዉን ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

በሌላ በኩል Noman (2013) እንደገለፁት የማንበብ ክሂል አንብቦ መረዳት አልያም ጮክ ብሎ ማንበብ ነዉ፡፡ ጮክ ብሎ ማንበብ ደግሞ የሚያተኩረዉ ፊደላትን መለየት ላይ እና ከሚወክሉት ድምፅ ጋር ማዛመድ ላይ ነዉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ ንባብ ለጀማሪዎችና ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ አንባቢዎች የቃላትና የዓረፍተ ነገሮች አነባበብ መለማመጃነት የሚዉል እንጂ ትርጉማቸዉን መረዳት ላይ የሚያተኩር አይደለም፡፡ በአንፃሩ የአንብቦ መረዳት ግን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን አጥርቶ ከማንበብ የዘለለ ነዉ፡፡ አንባቢዉ መስተጋብር ፈጥሮ ለመረዳት የሚሞክርበት ዉስብስብ ሂደት እንደሆነ ገልፀዉ ንባብ መረጃ መቀበያ መስተጋብራዊ ክሂል ስለሆነ ከረጅምም ከአጫጭር አሃድ ልዩ ልዩ መረጃዎችን እናገኝበታለን፡፡ የዚህ ዓይነቱ ተግባቦት የሚከናወነዉም በአንባቢዉ አእምሮ ዉስጥ ነዉ፡፡

Berardo (2006) Nutal (1996)ን ጠቅሶ ማንበብ በዉስጡ የፍቺ እሳቤን ከአንዱ አእምሮ ወደ ሌላኛዉ የትርጉም ሽግግርን፣ ከፀሐፊዉ ወደ አንባቢዉ የመልዕክት ሽግግርን፣ ፍቺ የማግኘት ሁኔታንና በማንበብ ሂደት ፀሐፊዉ፣ አንባቢዉና የሚነበበዉ ፅሁፍ ያላቸዉ ግንኙት የሚሉት ማዕከላዊ ነጥቦች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የምንባብ ምንነት መገንዘብ የሚቻለዉ ምንባብ ፀሐፊዉ በሌለበት አንባቢዉና ፅሁፉ የሚገናኙበት ሂደት መሆኑና የፀሐፊዉን ሀሳብ ለመረዳት አእምሮአዊ ተግባርን የሚጠይቅ መሆኑን ነዉ፡፡ አንብቦ መረዳት በማንኛዉም የትምህርት ዘርፍ ዉጤታማ ሆኖ ለመቀጠል መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን፣ በህይወት

ዉስጥ የተለያዩ መረጃዎችን በስፋትና በጥልቀት ለመገንዘብ፣ የተለያዩ ምርምሮችን ለማካሄድና የኑሮን አቅጣጫ ለመተለም አንብቦ መረዳት አብይ ትምህርታዊ ተግባር መሆኑን ነዉ፡፡ እንዲሁም ጮክ ብሎ ማንበብ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችና ጀማሪዎች ቃላትን ለመለየትና ድምፆችን ከተወከሉበት ሃሳብ ጋር ለማዛመድ የሚጠቅም ሲሆን አንብቦ መረዳት ግን አንባቢዉ ከፅሁፉ ጋር መስተጋብር ፈጥሮ ለመረዳት የሚሞክርበት ዉስብስብ ሂደት መሆኑን ነዉ፡፡

## 2.1.8 አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ

የንባብ ትምህርት ተማሪውን ውጤታማና ራሱን የቻለ አንባቢ እንዲሆን ለማድረግ በሚያግዝበት መንገድና የንባብ ስልቶችን በሚያዳብርበት መልክ መቅረብ አለበት፡፡ ውጤታማ ንባብ የስነ ልቦናዊ ስነ-ልሳንን የንባብ ጽንሰ ሐሳብ መሰረት ማድረግ አለበት፡፡ ንባብ የስነ-ልቦናዊ ስነ ልሳን የመተንበይ ሂደት ነው፡፡ የንባብ ሂደትም በቋንቋና በእሳቤ መካከልያለ የመገመት፣ የመምረጥ፣ የመመዘን፣ የማዋሐድና የመተርጎም ዑደታዊ ሂደት ነው በማለት Mei-Yun (1997፡180) ያብራራሉ፡፡

ይህን የስነ-ልቦናዊ ስነ-ልሳን የንባብ ግንዛቤ መሰረት በማድረግ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ለማድረግ እንደሚቻል ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ጥሩ አንባቢ ለንባብ ከቀረበለት ጽሁፍ በመነሳት የጽሁፉን ይዘት የመገመት፣በንባብ ሂደት ያገኘውን ሐሳብ የመመዘንና ከግምቱ ጋር በማዋሃድ የምንባቡን አጠቃላይ ፍሬ ሐሳብ የመረዳት ባሕርይ ስላለው ግንዛቤውን መሰረት ማድረግ ለትምህርት አቀራረብ የጥሩ አንባቢን ባሕርይ ለማላበስ ያስችላል፡፡

የውጤታማ ንባብ ዓላማ ጥሩ አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የማንበብ ስልቶችና ንዑሳን ክሂሎችን መጠቀም የሚችል ውጤታማ አንባቢ ተማሪ ለማፍራት ስለሆነ Mei-Yun (1997) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያግዝ የትምህርት አቀራረብ ባሕርያት ማለትም በምክንያት ማንበብ፣የመገመት ስልትን መጠቀም፣ዳራዊ እውቀትን ለግንዛቤ ማከልና በንዑሳን ክሂሎች የመጠቀም ችሎታን መርህ ሊያደርግ ይገባዋል፡፡ ስለዚህም ተማሪዎችን ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ ለማገዝ የትምህርቱን አቀራረብ በመስተጋብራዊ የንባብ ግንዛቤ ላይ መመስረት የተሻለ ነው፡፡

ለዚህም ተገቢ የሆነ የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪውን ማሳተፍ ይገባል (Johnson 1982)፡፡ ይህን የንባብ ግንዛቤ መሰረት አድርጎ የሚቀርብ አንብቦ የመረዳት ትምህርት የሚያተኩረው ግንዛቤ ለማዳበር በሚደረግ የንባብ ሂደት ላይ እንጂ ምን

ያህል እንደተገነዘቡ በማወቅ በውጤት ላይ ማተኮር አይደለም (Greenwood 1981:53):: ለመረዳት የሚደረግ የንባብ ሂደት የሚጠይቀውን የንባብ ስልት ለማዳበር የሚያግዝ ወቅታዊ የሆነና ተቀባይነት ያለው የትምህርት አቀራረብ የቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

### ሀ. ቅድመ ንባብ(Pre-Reading)

የቅድመ ንባብ አቀራረብ ተማሪዎች አንድ የቀረበን ጽሑፍ ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የሚከናወኑትን ተግባራት የሚያትት ሲሆን ይህም ሁለት አበይት ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡- ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ምክንያት በመግለጽ የማንበብ ፍላጎታቸውን ማነሳሳት እና ስለ ምንባቡ ይዘት መነሻ ሐሳብ/ፍንጭ እንዲኖራቸው ማስቻል ናቸው (Getachew 1996:13):: በዚህ ቅድመ ንባብ ወቅት ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበት ዓላማ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ ይህም ምንባቡን ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንደሚገባቸው ለመወሰን ያግዛቸዋል፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስለ ምንባቡ ይዘተ ነገርና ምንነት መጠነኛ ግንዛቤና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ጽሑፉን ወደማንበብ ከመሸጋገራቸው በፊት ከርዕሱ በመነሳት ሐሳብ እንዲሰነዝሩ በማነሳሳት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ወዘተ. ይከናወናል፡፡

በቅድመ ንባብ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ሌላው ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ፍችዎች እንዲረዱ ማድረግ እንደሆነ ምሁራን (ለምሳሌ Nuttal 1982:157) ይጠቁማሉ፡፡ ምንባቡን አንብቦ ለመረዳት እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አዳዲስ ቃላት ፍችዎች ለተማሪዎች በዚህ የቅድመ ንባብ ወቅት ቢቀርቡላቸው ምንባቡን አንብበው ለመረዳ ያግዛቸዋል፡፡

በሌላም በኩል የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎች ተማሪዎች ምን እንደሚያነቡ ማስተዋወቂያና ለቀጣዩ ደረጃ (የንባብ ጊዜ) ተግባራትን ማስተዋወቂያ ነው McDonugh and Shaw (2003:95) ፡፡

በአጠቃላይ የቅድመ ንባብ ዋና ዓላማ ከዋናው የንባብ ሂደት በፊት የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት የክፍል ደረጃውንና እድሜያቸውን ከግምት ያስገቡ የንባብ ትምህርት ይዘቶችን በመጠቀም ተማሪዎቹ እንዲሳተፉና ለዕለቱ ትምህርት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ማገዝ ነው፡፡ የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎችና ጥያቄዎች ዋና

ትኩረት ግን ልጆቹ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሩ ሁኔታ እንዲረዱና ፍላጎታቸው እንዲነቃቃ ለማድረግ ነው፡፡

**ለ. የንባብ ጊዜ (While-Reading)**

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ጽሑፉን የሚያነቡበት የንባብ ሒደቱ ዋነኛ አካል ነው፡፡ ይህ ባለ ሶስት ደረጃ የንባብ ትምህርት ተማሪ ተኮር (Student-Centered) በመሆኑ አብዛኞቹ ተግባራት የሚከናወኑት በተማሪዎቹ ነው፡፡ የመምህሩ ሚናም ለተማሪዎቹ እርዳታ በመስጠት የማንበብ ሂደቱን ማፋጠን ነው (Getachew 1996፡15)፡፡

ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ምንባቡን ማንበብ ያለባቸው በፀጥታ ነው ወይስ ድምፅን ከፍ በማድረግ የሚለው ጥያቄ በተለያዩ ምሁራን ይነሳል፡፡ ብዙዎቹ ምሁራን (Greeenwood 1981:81-82፣ Lewis 1985፣ Nuttal 1982) እንደሚሉት፣ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርበውን ምንባብ በፀጥታ ቢያነቡ ይመረጣል፤ ምሁራኑ እንደሚሉት ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ምናልባት ድምፅን ከፍ አድርጎ የሚያነበው ተማሪ የአነባበብ ስልት ጥሩ ካልሆነ ሌሎቹ ተማሪዎችም ይህን ጥሩ ያልሆነ ያነባበብ ስልት ልምዱን ሊቀስሙ ይችላሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር ተማሪዎች በክፍ ውስጥ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ "አሁን ምን እሳሳት ይሆን?" እያሉ ይጨነቃሉ፡፡ ይህም ስጋት የሚያነቡትን ምንባብ መረዳታቸውን ሊቀንሰው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ እርባናቢስ ነው፤ሙሉ በሙሉም መዘንጋት አለበት ማለት እንዳልሆነ ከላይ የተጠቀሱት ፀሐፍት ይጠቁማሉ፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ አልፎ አልፎ በተለይም የተማሪውን የአነባበብ ስልት ለመገምገም ሲባል ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**ሐ. ድህረ ንባብ (post-Reading)**

በዚህ ወቅት ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ የበለጠ እንዲገነዘቡት የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡በዚህ ደረጃ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ ስለተገነዘበው ምንባብ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማቅረብና በተማሪዎች እንዲመለሱና ውይይትም እንዲካሄድባቸው ማድረግ ዋነኛው ዓላማ ነው፡፡

የእነዚህ ጥያቄዎች ዋና ትኩረትና ዓላማም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው (Nuttall 1982፣ Greenwood 1981:83) ስለሆነም ንባብን በማስተማሩ ሂደት አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ ለተማሪዎች የሚቀርቡት ጥያቄዎች አንብቦ መረዳትን የሚያዳብሩ እንዲሆኑ በጥንቃቄ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

በድኅረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ባነበቡት ጽሑፍ ላይ በጥልቀት ሊወያዩና ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡ Celce-Murcia (1991፡204) በድኅረ ንባብ ደረጃ በእለቱ ለንባብ የቀረበው ጽሑፍና ዋና ዋና ሐሳቦች የሚከለሱበት ክፍል ነው፡፡ እንደዚሁም በጊዜ ንባብ ደረጃ ከቀረበው ትምህርት ተነስተው የተወሰኑ አዳዲስና ተያያዥነት ያላቸውን ቁም ነገሮች በማካተት በክፍል ውስጥና እቤታቸው ሰፋ ያለ ልምምድ የሚያከናውኑበት ደረጃ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ክፍል ተማሪዎቹ ካነበቡት ምንባብ የተገነዘቡትን በራሳቸው አገላለጽ ለጓደኞቻቸው የሚያቀርቡበትና እርስ በርሳቸው እየተጋገዙ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ነው፡፡

እንዲሁም የድኅረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በየግላቸው የተሰጣቸውን ጽሁፍ በዝምታ ካነበቡ በኋላ በተናጥል፣በጥንድ/በቡድን ሆነው ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማነቃቃት ይቻላል፡፡ጥያቄዎችን በህብረት ወይም በቡድን መሥራቱ ደግሞ የበለጠ ጥሩ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ አካሄድ እያንዳንዱ ተማሪ የመለሰውን መልስ ለምን እንደመረጠው የማስረዳት እድል ይሠጠዋል፡፡ ይህ እድል በመኖሩም ተማሪው በሕብረት ስለሚወያይ አንድ ምንባብ አንብቦ ምን ያህል እንደተረዳ ጥያቄዎቹን በሚሰራበት ወቅትም የት ላይ፣ እንዴት እንደተሳሳተ ሊያውቅ ይችላል (Nuttall 2000)::

### 2.1.9 የአንብቦ መረዳት ስልቶች

የተለያዩ የንባብ ስልቶች ያሉ ሲሆን አንባቢዉም እንደ ፍላጎቱና እንደ ዓላማዉ አንዱን ተጠቅሞ ማንበብ ይኖርበታል፡፡ እነዚህም የንባብ ስልቶች አራት ሲሆኑ እነሱም፡- የገረፍታ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብ፣ ሰፊ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ ናቸዉ፡፡ የገረፍታ ንባብበ አጠቃላይ የተፃፈዉን ፅሁፍ ሐሳብ ለማግኘት የሚነበብ ስልት ነዉ፡፡ ይህ ስልት የአንቀፁን ኃይለ ቃል ለመረዳት የምንጠቀምበት መሆኑን Inyang (2009) ይገልፃሉ፡፡ ሁለተኛው ስልት ደግሞ የአሰሳ ንባብ ሲሆን ከአንድ ፅሁፍ ዉስጥ የተወሰነ መረጃን ፈልጎ ለማግኘት ሲባል በፍጥነት የምናከናዉነዉ ስልት ነዉ፡፡ በዚህ ስልት ለማግኘት የምንፈልጋቸዉ መረጃዎች ስም፣ ቁጥር እና ዓመተ ምህረትን ከፅሁፉ ዉስጥ ለመለየት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ሶስተኛዉ የአንብቦ መረዳት ዘዴ ደግሞ ሰፊ ንባብ የሚባለዉ ሲሆን በቦታ እና በጊዜ ሳይወሰን አንባቢዉ ለመዝናናትና ከተለያዩ ሀሳቦች ለማረፍ ሲል የሚገለገልበት ስልት ነዉ፡፡ የሚነበበዉ ፅሁፍ ሰፊ በመሆኑ የፅሁፉን አጠቃላይ መልዕክት ለመገንዘብ የአንባቢዉን ንቁ ተሳትፎ ይፈልጋል የመጨረሻዉ ስልት ጥልቅ ንባብ ሲሆን ፅሁፉን በጥልቀት ለመገንዘብ ሲባል የሚከናወን ነዉ፡፡

ይህ የንባብ ስልት በጊዜና በቦታ የተገደበ ሆኖ ስፋት ግን የለዉም፡፡ በንባብ ሂደትም እርጋታና ጥንቃቄ እና አስተዉሎትን የሚጠይቅ የንባብ ዓይነት ነዉ፡፡ በጥልቅ ንባብ ጊዜ በፅሁፉ ዉስጥ በግልፅ የሰፈሩ መረጃዎች ላይ ከማተኮር አንስቶ በግልፅ ላልሰፈሩ ሀሳቦችም ትርጉም በመስጠት ለመረዳት የሚሞክርበት ስልት ነዉ (Inyang፡ 2009)፡፡ እንዲሁም አንባቢዉ ከሚያገኘዉ ጥቅም አንፃር ደግሞ የንባብ ደረጃዎች ላይላይ፣ታህታይ እና አልቦ (ዜሮ) ንባብ ማለት የሚከፍሉ አሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠልም እነዚህን የንባብ ደረጃዎች እናያለን፡፡ ላዕላይ ንባብ አንባቢዉ ፍጥነቱን ተጠቅሞ የፅሁፉን አጠቃላይ ሀሳብ ለመረዳትና ለመጨረስ በትኩረት የሚያከናዉነዉ ነዉ፡፡ ታህታይ የንባብ ደረጃ ደግሞ አንባቢዉ ዋናዉን መልዕክት ለመረዳት በትኩረት የሚያነበዉ እና በፅሁፉ ከተገለፁ ጉዳዮች በተጨማሪ ያሉ ነገሮችን መመልከት ዝምድናቸዉን ለመመርመር የምንገለገልበት ነዉ፡፡ የመጨረሻዉ አልቦ (ዜሮ) የንባብ ደረጃ ሲሆን ይህ ንባብ ፅሁፉን በፍጥነት አንብቦ ለመጨረስ ሲባል የምናከናዉነዉ መሆኑን Carter & lang (2011) እና ማረዉ (1998) ይገልፃሉ፡፡

### 2.1.10 የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች

የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን በተመለከተ ወጥነት ያለው አከፋፈል ባይታይም የምሁራኑን አተያይ ቀጥለን ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡ የጥናቱ ዋና ትኩረትም አንብቦ መረዳት፣ ከዛም ውስጥ ንዑሳኑ ላይ አበክሮ ስለሚመለከት ነው፡፡ እንደ Langan(2003) እና Grellet(1981) ገለፃ ፍሰቱን የጠበቀ/ቅደም ተከተሉን የያዘ የንባብ ክሂል ሂደት በጣም መሰረታዊና ለአንብቦ መረዳት ወሳኝ ድርሻ ያለው ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ ንዑሳን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የምንብቡን ግልፅ መልዕክት መረዳት(Literal comprehension)፣ በምንባቡ ውስጥ በቀጥታ የተገለፀውን መልዕክት አንብቦ የሚነሱ ጥያቄዎችን መመለስን ያመለክታል፡፡ በሌላ አገላለፅ የምንባቡን ግልፅ መልዕክት መረዳት፣ መልዕክቱን ከሚጠይቁ ጥያቄዎች ጋር ማዛመድና ማብራራትን ይጠቁማል፡፡ እነሱም፦ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መረዳትን፣ ዋና መልዕክቱን/ሃሳቡን መገንዘብ መቻል፣ ዝርዝር ሃሳቦችን/ደጋፊሃሳቦችን መለየት መቻል፣ ዋናሃሳቡን/መአከላዊ ሃሳቡን መረዳት (Critcal level of Comprehension)፣ ተዛማጅ ወይም ሃሳባዊ ሂደቱን መረዳት፣ የማጠናከሪያ፣ የንፅፅር፣ የምክንያትና ውጤት መዋቅሮችን መረዳት ሲሆኑ፣ ሌሎችም ቁልፍ የአንብቦ መረዳት ክሂላት አሉ፡፡ እነሱም፦ ሃቅንና የግል አስተያየትን መለየት፣ በጥልቀት መመርመር፣ አንድምታውን መፈተሽ፣ የፀሀፊውን አላማና ስሜት መረዳት፣ ሂስ ማድረግ መቻል ናቸው፡፡

አንብቦ መረዳት ችሎታ ሲባል ደግሞ አንድን በፅሁፍ የቀረበ መልዕክትን በሚገባ ተረድቶ ለሚፈለገው አላማ ማዋልን የሚመለከት አቅም ነው፡፡ ማንበብ የመቀበል ክሂል (Receptive skill) ሲሆን፣ በአንባቢውና በፅሁፉ መካከል የሚደረግ መስተጋብር እንደሆነ Harmer (2010 ) ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም አንብቦ መረዳት አንባቢው ከሚያነበው ፅሁፍ ፍሬ ነገሩን መለየት፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት፣ የቃላት አገባባዊ ፍቺዎችን ማወቅ፣ የፅሁፉን አወቃቀር መለየትና መሰል ክሂሎችን አጠቃሎ እንደሚይዝ ምሁራኑ ይገልፃሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው የምሁራን አስተያየት አንብቦ መረዳት መረጃን ከልዩ ልዩ ፅሁፋዊ አሃዶች በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል አቅም እንደሆነም መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም አንብቦ መረዳት አንባቢው የፅሁፉን መልዕክት ለመረዳት የሚያከናውነው አእምሯዊ ሂደት ሲሆን፣ የፅሁፉን አጠቃላይ ጭብጥ መረዳትን፣ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መገንዘብን፣ የፅሁፉን አወቃቀር መለየትንና መሰል የንባብ ተግባራትን ወይም ንዑሳን ክሂሎችን አካቶ እንደሚይዝ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ካላቸው ጥናቶች ውስጥ ማግኘት የተቻለው በመንግስቱ (2008)፣ በመሰረት (2013)፣ በአለምነሽ (2014)፣ በየማሪያምወርቅ (2013)፣ በአንድነት (2010) እና በእቴነሽ (2010) የተጠኑት ጥናቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በምን እንደሚለያዩና እንደሚመሳሰሉ እንደሚከተለው በዝርዝር ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

የመጀመሪያው መንግስቱ በ2008 ዓ.ም የተጠናው ጥናት በጅማ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ አማርኛን ማስተማር ለማስተር መርሃ ግብር ለማሟያነት የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስም ‹‹ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና›› የሚል ነው፡፡ ይህ ጥናት በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2008 ዓ.ም በሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ሲሆን ዋና ዓላማውም በአጭር ልቦለድ ቋንቋ ማስተማር አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ሆኖ

በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖች አማካይነት ተግባራዊ የተደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ግኝትም የሚያሳየው በአጭር ልቦለድ አማካይነት ቋንቋን መማርና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ግንኙነት እንዳለ መረዳት ተችላል፡፡ ስለሆነም ቋንቋን በተለመደው መንገድ ከተማሩት ይልቅ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ አማካይነት የተማሩት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ተሻሽሎ እንደታየ ነው፡፡

የመንግሰቱ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ልዩነት ስንመለከት የመንግስቱ ጥናት በ2008 ዓ.ም የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በ2015 ዓ.ም የተጠና ነው፡፡ ሌላው የመንግስቱ ጥናት በፓዊ ወረዳ በቀጠና ሁለት መንደር ሁለት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከናወነ ነው፡፡ በተጨማሪም የመንግስቱ ጥናት ዋና ዓላማውም በአጭር ልቦለድ ቋንቋ ማስተማር አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ በሚል፣ በማንበብ ክሂል ላይ ያተኮረ ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ደግሞ የ7ኛ ክፍል አፍ-ፈት ተማሪዎችን በአጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር በመሆኑ ማለትም በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ (ክሂል) ላይ ትኩረት በማድረግ የተጠና ነው፡፡ የመንግስቱ ጥናት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠነ ነው፡፡ የመንግስቱ ጥናት በኢ-ፊፈት ተማሪዎች ላይ የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በአፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ የተጠና ነው፡፡ የመንግስቱ ጥናትና ይህ ጥናት ያላቸውን አንድነት ስንመለከት ደግሞ ሁለቱም ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ ላይ የተጠኑ መሆኑ፤ በማንበብ ክሂል እና በአጭር ልቦለድ ላይ የተመሰረቱ መሆኑና ተመሳሳይ የሆነ የአጠናን ዘዴን የተከተሉ በመሆናቸው ነው፡፡

በእዚህ መሠረት የመንግስቱ ጥናት አፈፊት ተማሪዎች እና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ያልተመለከተ በመሆኑ ይህ ጥናት ይህን ክፍተት ለመሙላት እንዲጠና ተደርጓል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ መሰረት (2013) በግጥም አማካኝነት የማንበብ ክሂልን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና ፍተሻ (በቀርሳ ወረዳ ለምለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) የሚለው

ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ በጥናቱ ተግባራዊ የተደረገው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ፈተና እና የጽፍ መጠይቅ ነው። ዋና ዓላማውም በግጥም አማካኝነት የማንበብ ክሂልን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ሆኖ በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖች አማካይነት ተግባራዊ የተደረገ ነው፡፡

የመሰረት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ልዩነት ስንመለከት የመሰረት ጥናት በ2013 ዓ.ም የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በ2015 ዓ.ም የተጠና ነው፡፡ ሌላው የመሰረት ጥናት በቀርሳ ወረዳ ለምለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከናወነ ነው፡፡ በተጨማሪም የመሰረት ጥናት ዋና ዓላማውም በግጥም አማካኝነት የማንበብ ክሂልን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና መፈተሽ በመሆኑ ማለትም በማንበብ ክሂል ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ(ሶስት ንዑሳን አላማዎችን አካቶ) ደግሞ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር በመሆኑ፣ ማለትም በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ ትኩረት በማድረግ የተጠና ነው፡፡ የመሰረት ጥናት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠነ ነው፡፡ የመሰረት ጥናትና ይህ ጥናት ያላቸውን አንድነት ስንመለከት ደግሞ ሁለቱም ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ ላይ የተጠኑ መሆኑ፣ በማንበብ ክሂል ላይ የተመሰረቱ መሆኑና ተመሳሳይ የሆነ የአጠናን ዘዴን የተከተሉ በመሆናቸው ነው፡፡ በእዚህ መሠረት የመሰረት ጥናት አጭር ልቦለድን እና  አፊ ፊት ተማሪዎችን ያልተመለከተ በመሆኑ ይህ ጥናት ይህን ክፍተት ለመሙላት እንዲጠና ተደርጓል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ አለምነሽ (2014) ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማጎልበት ላይ ያለው አስተዋፅኦ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሊኖዋ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ሙከራዊ ጥናት) የሚለው ጥናትና

ተጠቃሽ ነው፡፡ በጥናቱ ተግባራዊ የተደረገው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ፈተና እና የጽፍ መጠይቅ ነው። ዋና ዓላማውም ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማጎልበት ላይ ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው፡፡

ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ሆኖ በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖች አማካይነት ተግባራዊ የተደረገ ነው፡፡

የአለምነሽ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ልዩነት ስንመለከት የአለምነሽ ጥናት በ2014 ዓ.ም የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በ2015 ዓ.ም የተጠና ነው፡፡ ሌላው የአለምነሽ ጥናት በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሊኖኖ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከናወነ ነው፡፡ በተጨማሪም የአለምነሽ ጥናት ዋና ዓላማውም ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማጎልበት ላይ ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ሲሆን፣ ማለትም በማንበብ ክሂል ላይ ያተኮረ ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ደግሞ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር በመሆኑ በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ ትኩረት በማድረግ የተጠና ነው፡፡ የአለምነሽ ጥናት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠና ነው፡፡

የአለምነሽ ጥናትና ይህ ጥናት ያላቸውን አንድነት ስንመለከት ደግሞ ሁለቱም ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ ላይ የተጠኑ መሆኑ፣ በማንበብ ክሂል ላይ የተመሰረቱ መሆኑና ተመሳሳይ የሆነ የአጠናን ዘዴን የተከተሉ በመሆናቸው ነው፡፡ በእዚህ መሠረት የአለምነሽ ጥናት አጭር ልቦለድን እና አፍ ፈት ተማሪዎችን ያልተመለከተ በመሆኑ ይህ ጥናት ይህን ክፍተት ለመሙላት እንዲጠና ተደርጓል፡፡

በአራተኛ ደረጃ ደግሞ የማሪያምወርቅ (2013) በኢትዮ ሚሊኒዬም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች የመደገፍ ብልሀቶች የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለው ሚና በሚል ርዕስ የተካሄደው ጥናትና ተጠቃሽ ነው፡፡ በጥናቱ ተግባራዊ የተደረገው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ፈተና እና የጽፍ መጠይቅ ነው። ዋና ዓላማውም ተማሪዎች የመደገፍ ብልሀቶች የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለው ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ሆኖ በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖች አማካይነት ተግባራዊ የተደረገ ነው፡፡

የማሪያምወርቅ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለውን ልዩነት ስንመለከት የማሪያምወርቅ ጥናት በ2013 ዓ.ም የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በ2015 ዓ.ም የተጠና ነው፡፡
ሌላው የማሪያምወርቅ ጥናት በኢ.ትዮ ሚሊኒዬም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስድሰተኛ ክፍል ተማሪዎች የተካሄደ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ደግሞ በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከናወነ ነው፡፡
የማሪያምወርቅ ጥናት እና ይህ ጥናት ያላቸውን አንድነት ስንመለከት ደግሞ ሁለቱም ጥናቶች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተጠኑ መሆኑ፣ በአማርኛ ቋንቋ ላይ የተጠኑ መሆኑ፤ በማንበብ ክሂል ላይ የተመሰረቱ መሆኑና ተመሳሳይ የሆነ የአጠናን ዘዴን የተከተሉ በመሆናቸው ነው፡፡ በእዚህ መሠረት የማሪያምወርቅ ጥናት አጭር ልቦለድን በመጠቀም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከማጎልበት አኳያ ያልተመለከተ በመሆኑ ይህ ጥናት ይህን ክፍተት ለመሙላት እንዲጠና ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም የምርምር ዘዴው ከፊል ፍትነታዊ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም በፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ በቁጥር የሚገለጽ ስለሆነና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው ደግሞ በሰንጠረዥ በመቶኛ በማስቀመጥ በገለፃ የሚገለፅ በመሆኑ ነው፡፡ የጥናት ንድፉም ከፊል ፍትነታዊ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ጥናቱ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን አማካይነት የሚጠና ስለሆነ የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ ፈተና ንድፍን (Two group pre-test and post-test design) ተግባራዊ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር ነፃ ተላውጦ ሲሆን፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጥገኛ ተላውጦ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካባይ

በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አምስት የሰባተኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ በሆነው አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 152 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በአንድ የመማሪያ ክፍል በአማካይ 50 ተማሪዎች በ2015 ዓ.ም በሦሰት ምድብ ተከፍለው ትምህርታቸውን በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ በአምስቱ ትምህርት ቤቱ የሚማሩት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ አካባይ ሲሆኑ አፍሪካ አንድነት ቁጥር-2 ከሚማሩ ከሦስቱ ምድብ ውስጥ ሁለት ምድብ በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርገዋል፡፡

## 3.3. የጥናቱ የናሙና አመራረጥ ስልት

### 3.3.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

በአዲስ አበባ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ ሁለት አምስት የሰባተኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ አምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አመቺ የንሞና ስልትን በመጠቀም አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡ ትምህርት ቤቱ በአመቺ

የንሞና ስልት የተመረጠበት ምክንያትም የተመረጠው ትምህርት ቤት በወረዳው ከሚገኙ ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንፃር ሲታይ አጥኚው የሚሰራበት በመሆኑና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችም ቁጥር ከሌሎቹ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ስለሆኑና ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

### 3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ይህ ጥናት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ በሚገኙ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተጠና ነው፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠው በአመቺ የንሞና ስልት ነው፡፡ በአመቺ የንሞና ስልት የተመረጠበት ምክንያትም ተማሪዎችን እስከ አመቱ መጨረሻ ለጥናቱ ማግኘት ስለሚቻል እና አጥኚው ተማሪዎቹን በፈለገው ጊዜ ማግኘት ስለሚችል ነው፣ በተወሰነ ጊዜ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለመመርመር አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

### 3.3.3. የተማሪዎች አመራረጥ

በአፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 152 ተማሪዎች በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን በአንድ የመማሪያ ክፍልም በአማካይ 50 ተማሪዎች በሶስት ምድብ ተከፍለው ይማራሉ፡፡ ጥናቱ በከፊል ፍትነታዊ የምርምር ንድፍ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ ስለማይቻል፣ የተሳታፊዎችን ቁጥር መወሰን የግድ ሆኗል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ክፍል በኦሮምኛ መርሀ ግብር አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በመሆኛቸው በጥናቱ ተሳታፊ አልተደረጉም፤ ከቀሩት ሁለት ክፍሎች ውስጥ በአላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ከ7ኛ(A) ክፍል 32 ተማሪዎች ከ7ኛ(B) ክፍል 30 ተማሪዎች በድምሩ 62 አማርኛ አፍፌት ተማሪዎች የተገኙ ሲሆን፤ በቅድመ ልምምድ ፈተናው ጊዜ ከ7ኛ(A) ሁለት(2) ተማሪዎች ባለመገኘታቸው በጥናቱ ትንታኔ አልተካተቱም፤ ከሁለቱ ክፍል የቀሩት 60 ተማሪዎች ግን የጥናቱ ተሳታፊ ተደርገዋል፡፡ በዚህ መሠረት የሁለት ምድብ ተማሪዎችን በጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ በቅድሚያ የሁሉንም ምድብ ተማሪዎች የችሎታ ስብጥር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የችሎታ ስብጥርን መሰረት ያላደረገ የምድብ ድልድል በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ስለሚኖረው ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ከትምህርት ቤቱ ርዕስ መምህር ባገኘው የምድብ ድልድል መረጃ መሰረት የተማሪዎቹ

የምድብ ድልድል የውጤት ስብጥራቸውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ፣ ያገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ ቅድመ ልምምድ ፈተና በመፈተን የተገኘው የሁለቱ ክፍል ውጤት ተቀራራቢ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

በዚህ መሰረት ቀላል የዕጣ ንሞናን ስልት በመጠቀም ከሁለቱ ምድብ ውስጥ ሰባተኛ (B)ን የሙከራ ቡድን ሰባተኛ (A)ን ደግሞ የቁጥጥር ቡድን አድርጎ በመምረጥ 60 ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ የጥናቱን ተሳታፊዎች ለመምረጥ አላማ ተኮር ንሞና እና ቀላል የእጣ ንሞን ስልት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ይህ የተደረገበት ምክንያትም አፍፈት ተማሪዎችን ለማግኘት አላማ ተኮር ንሞና ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን፣ በሁለቱ ምድብ የሚገኙት ተማሪዎች ተመሳሳይ የሆነ የውጤት ስብጥር ስላላቸው የቁጥጥር ቡድኑንና የሙከራ ቡድኑን ለመለየት ደግሞ ቀላል የእጣ ንሞና ዘዴን ተከትሏል፤ በጥናቱ የመሳተፍ ዕድላቸው ዕኩል እንዲሆን በማሰብ ነው ይህ የተደረገው፡፡

## 3.4. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት

### 3.4.1 ፈተና

በዚህ ጥናት ፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት ጥናቱ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያተኮረ በመሆኑ፤ ችሎታ ደግሞ የሚለካው በፈተና ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት የጥናቱን ተሳታፊ ተማሪዎች ወቅታዊ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት Haregewain (2008) በሶስተኛ ዲግሪ ጥናታቸው ላይ ተግባራዊ ያደረጉትን የቅድመና የድህረ ፈተና አዘገጃጀት መንገድ እንደመነሻ በመጠቀም የቅድመ ትምህርት ፈተና በአጥኚው ተዘጋጅቶ ለአማካሪና ለሶስት አማርኛ መምህራን በማሳየትና በማስተካከል የሁለቱ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡

የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የተዘጋጀው የቅድመ ትምህርት ጥያቄዎች አራት ክፍል ያለው ሲሆን ጥያቄዎችም የወጡት የክፍል ደረጃውን መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አጠቃላይ ለጥያቄዎቹ የተሰጠው ነጥብ 40 ሲሆን የጥያቄዉ ብዛትም 40 እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ተማሪዎች ከ40 ያገኙት ውጤትም ወደ100 በመቀየር እንዲሰላ ተደርጓል፡፡

የቅድመ ትምህርት ፈተናው ለሁለቱ ክፍል ተማሪዎች ከተሰጠ በኋላ የተገኘው ውጤት

ተቀራራቢ በመሆኑ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑን በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ መለየት ተችሏል። ከዚህ በኋላ ደግሞ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበር የሚያስችሉ የትምህርት ይዘቶችን ለደረጃው ከቀረበው መርሃ ትምህርትና መማርያ መጻሕፍ አኳያ እዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ ይዘቶች በአራት ክፍለ ትምህርት በመክፈል በሳምንት ሶስት ጊዜ፣ ለአራት ተከታታይ ሳምንታት በአጥኚው አማካይነት ተጠኚ ቡድኑን አጭር ልቦለድን በመጠቀም፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለምዷዊው መንገድ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ የመማር ማስተማሩ ሂደት በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ የተማሪዎችን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የድህረ ትምህርት ፈተና ለቁጥጥርና ለተጠኚ ቡድን ተማሪዎች ተሰጥቷል፡፡ የድህረ ፈተና አወጣጡም ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር በተመሳሰለ መልኩ ተዘጋጅቶ ለአማካሪና ለሶስት አማርኛ መምህራን በማሳየትና በማስተካከል ፈተናው ተከናውኗል፡፡ በአጠቃላይ የቅድመ ፈተና ጥያቄዎችን አባሪ ስምንት፣ የድህረ ፈተና ጥያቄዎችን አባሪ ዘጠኝ እንዲሁም ለትምህርት የቀረበውን ይዘት ደግሞ አባሪ አሥር ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ተግባራዊ የተደረገበት ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎቹ የማንበብ ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ሚና/አስተዋፅኦ ለመፈተሽ በአጋዥነት (በደጋፊነት) የተዘጋጀ ነው። ስለዚህም የፅሑፍ መጠይቁ ንዑሳን አላማዎች ላይ በመመርኮዝ የማንበብ ችሎታን የተመለከተ ሲሆን፣ ጥያቄዎቹ በሶስት ክፍሎች በማዛመድ በአጭር ልቦለድ መማር የተማሪዎችን የቃላት አውዳዊ ፍቺ የመስራት፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት እና የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት/ጭብጥ ከመግለፅ አንፃር ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ መንግስቱ (2008) "ቋንቋን በአጭር ለልቦለድ ማስተማር አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና መፈተሽ" በሚለው ጥናታቸው ከተዘጋጁት የፅሑፍ መጠይቅ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግና በአማካሪና በቋንቋ መምህራን በማስገምገም የተዘጋጀ ሲሆን፣ የጥያቄዎቹ ብዛት ሃያ (20) ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ነው። በዚህ መልኩ የተዘጋጀው መጠይቅ በቋንቋ ባለሙያዎች እንዲገመገም ከተደረገ በኋላ በአንዳንድ ጥያቄዎቹ ላይ ለውጥ ተደርጎባቸው ተግባራዊ ተደርጓል። የፅሑፍ መጠይቁ በቅድመ ትምህርት ደረጃ ላይ በሁለቱም ቡድኖች ከተሞላ በኋላ

ምንም የተለየ ግብኣት ሳይጨመርባቸው በድህረ ትምህርት ደረጃ ላይም በሁለቱም ቡድኖች የማንበብ ችሎታን ከማሳደግ አንፃር የፅሑፍ መጠይቁን ሞልተዋል።
በፅሑፍ መጠይቁ ላይ የተካተቱት ጥያቄዎችም ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ቀርበዋል። እነሱም፦ በጣም እስማማለሁ (4)፣ እስማማለሁ (3)፣ አልስማማም (2) እና ፈፅሞ አልስማማም (1) የሚሉት ናቸው። መጠይቆቹ አራት የመልስ መወሰኛ አማራጮች እንዲይዙ የተደረገበት ምክንያት ያለው (2009) እንደገለፁት ወላዋይ መላሾች ለሚጠየቁት ጥያቄ እስማማለሁ ወይም ደግሞ አልስማማም ብለው መልስ መመለስ ስለሚቸግራቸው መወሰን አልችልም የሚል መልስ እንዳይመልሱና የመጠይቁን አስፈላጊነት ካለመረዳት ወይም በግድየለሽነት እርግጠኛ አይደለሁም ወይም አልወሰንኩም የሚል ምርጫ እንዳይመርጡ ለመከላከል ነው። ለበለጠ መረጃ አባሪ አምስትን ይመልከቱ፡፡

## 3.5. የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የጥናቱ ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር ውጤታማ መሆንና አለመሆኑን በመፈተሽ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በጥናቱ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አማካይነት መረጃ ከመሰብሰቡ በፊት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ሊለካ የሚችል የቅድመ ትምህርት ፈተና በአጥኚው ተዘጋጅቶ በአማካሪና ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ችሎታን ከመለካት አኳያ አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረገና የተሰጠውን አስተያየት በማስተካከል የተመረጡት የሁለቱ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፣ ውጤታቸውም ተቀራራቢ በመሆኑ በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ተለይቷል፡፡ እንዲሁም ቅድመ ፈተናውን ከተፈተኑ በኋላ ደግሞ የተማሪዎች ስለ አንብቦ መረዳት ያላቸው ግንዛቤ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ የተዘጋጀውን የቅድመ መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

የቅድመ ፈተናው እና መጠይቁ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ደግሞ የተማሪዎችን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ሊያጎለብቱ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶችን የተጠኚ ቡድኑን አጭር ልቦለድን በመጠቀም፣ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በተለምዷዊው የማስተማርያ መንገድ

በሳምንት ሦስት ጊዜ ለተከታታይ አራት ሳምታት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ የመማር ማስተማሩ ሂደት በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት የሚያስችል የድህረ ትምህርት ፈተና እና የጽሑፍ መጠይቅ በድጋሚ በአጥኚው ተዘጋጅቶ በአማካሪና በሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከመለካት አኳያ አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረገና የተሰጠውን አስተያየት በማስተካከል የቁጥጥርና የተጠኚ ቡድኑ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜም የፈተና አወጣጡም ሆነ አስተራረሙ ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር፣ እንዲሁም የጽሑፍ መጠይቁ አዘገጃጀትም ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቁ ጋር በማመሳሰል ከተማሪዎች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነ መረጃን በድጋሚ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

## 3.6. የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ስልት

በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረገው የመረጃ መተንተኛ ስልት መጠናዊና ገለፃ ነው፡፡ በመጠናዊና በገለፃ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተግባራዊ የሆነበት መሰረታዊ ምክንያትም በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ ሙሉ በሙሉ በቁጥር የሚገለጽ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ዋና ዓላማ ግብ እንዲመታ ለማድረግ አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ምን እንደሆነ በቅደመና በድህረ ፈተና እና የጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት ከቁጥጥርና ከሙከራ ቡድኑ መረጃውን በመሰብሰብ የመረጃው አማካይና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡

በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኑ አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩንና አለመኖሩን ለመፈተሽም የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ከቁጥጥርና ከሙከራ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ፈተና እና የጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰበውን መረጃ አማካይ፣ መደበኛ ልይይትና የቲ-ቴስት ዋጋ ምን እንደሆነ በSPSS Version 20 በማስላት የተገኘውን መረጃ በምዕራፍ አራት ላይ በዝርዝር ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ለትንተናው ያመች ዘንድ ከ40 የተሰጠውን የፈተና ውጤት ወደ መቶ በመቀየር ተተንትኗል፡፡

## 3.7. የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት አግባብነት

የጥናቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት አግባብነትን ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይህም ሲባል የተዘጋጁትን የቅድመና የድህረ ፈተናዎች እና የጽሑፍ መጠይቆችን አግባብነት ለመጠበቅ በማንበብ ክሂል ትምህርት ዙሪያ ላይ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የተሰጡ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ሊለኩ የሚችሉ ፈተናዎች እና የጽሑፍ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡ ፈተናዎች የተዘጋጁት በአጥኚው ስለሆኑ ለአማካሪው በማሳየት እንዲሁም ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከማንበብ ክሂል ትምህርት አኳያ ተገቢነታቸውን እንዲገመግሟቸው በማድረግና የተሰጠውን አስተያየት በማስተካከል የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች እንዲፈተኗቸው ተደርገዋል፡፡

በፈተና አሰጣጡ ወቅት ተማሪዎች እንዳይኮራረጁ በሰፊ ክፍል ውስጥ ነጣጥሎ በማስቀመጥ በሁለት መምህራን አማካይነት እንዲፈተኑ ተደርገዋል፡፡ ለፈተናው የተሰጠው ጊዜም 1፡30 ሰዓት ሲሆን ተማሪዎቹ ፈተናውን ሰርተው እንደጨረሱ የፈተናዎች የመልስ ወረቀት በፈታኞች አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡ እርማቱም እንደጥያቄዎቹ ባህርያት በመምህሮቹ አማካይነት ተካሂዷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና እና ውጤት ማብራሪያ

ይህ ክፍል በዋናነት በምዕራፍ ሶስት፣ በጥናቱ ዘዴ በተጠቆሙ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች በስታትስቲክ ስልት ተተንትኖ የቀረበበትና ከትንተናው የተገኘው ውጤትም በምዕራፍ አንድና ሁለት ስር በቀረቡ የተለያዩ አስተያየቶች በመመርኮዝ ተብራርቶ የቀረበበት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከተማ፣በአራዳ ክፍለ ከተማ፣ በወረዳ ሁለት (02) በሚገኘው አፍሪካ አንድነት ቁጥር-2 የመጀመያ ደረጃ ትምህርት ቤት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ ስለዚህም የጥናቱ ትኩረት አጭር ልቦለዶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያላቸውን አስተዋፅኦና ውጤታማነት በመፈተሽ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ አቅጣጫዎችን ማሳየት ነው፡፡ ለዚህም ጥናቱ ሶስት ዝርዝር አላማዎች ያሉት ሲሆን፣ እነሱም (1) በአጭር ልቦለድ የአንብቦ መረዳት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች የቃላት አውዳዊ ፍቺ የመለየት ችሎታቸው በተለመደው መንገድ ከሚማሩ ተማሪዎች ጉልህ በሆነ መንገድ መሻል አለመሻሉን መፈተሽ፤ (2) አጭር ልቦለድን ተጠቅመው የአንብቦ መረዳት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች ዝርዝር ሃሳቦችን ተረድተው የመለየት ችሎታቸው በተለምዷዊ መልኩ ከሚማሩ ተማሪዎች ጉልህ በሆነ መልኩ መሻሻል አለመሻሻሉን መመርመር እና (3) አጭር ልቦለድን ተጠቅመው የአንብቦ መረዳት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት/ ጭብጥ ተረድቶ የመግለፅ ችሎታቸው በተለምዷዊ መልኩ ከሚማሩ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ መሻል አለመሻሉን መፈተሽ የሚሉ ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የቁጥጥር ቡድኑም ሆነ የሙከራ ቡድኑን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ ቅድመ ልምምድ እና ድህረ ልምምድ ፈተናዎች ተፈትነዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ክፍል ሁለቱም ቡድኖች በፈተናዎቹ ያስመዘገቧቸው ውጤቶች ስታትስቲካዊ በሆነ መንገድ ተተንትነው የቀረቡበት ነው፡፡

ሁለቱም ፈተናዎች በምዕራፍ አንድ በጥናቱ አላማ ስር በተገለፁት ሶስት ዝርዝር አላማዎች መነሻነት በሶስት የጥያቄ ምድቦች የተዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህ ዝርዝር

አላማዎችም፣ አንብቦ ከመረዳት አንፃር የተማሪዎችን የቃላት አውዳዊ ፍቺ መለካት፣ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ መመርመር እና የፅሁፉን ጭብጥ (አጠቃላይ መልዕክት) የመረዳት ችሎታን መመዘን ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያትም ትንተናው የቅድመ ልምመድና የድህረ ልምምድ ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቆችን ከእነዚህ ሶስት ዝርዝር አላማዎች አንፃር በመቃኘት በማባራራት ቀርቧል፡፡

## 4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና

ጥናቱ ትኩረት አድርጎ የተነሳው አጭር ልቦልድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና በመመርመር ላይ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች አማካይነት መረጃዎችን በመሰብሰብ አጭር ልቦልድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ሚና በዝርዝር ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

በዚህ ጊዜም አጭር ልቦልድን በመጠቀም ቋንቋ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሳደግ ያለውን ሚና ለመመርመር በቅደመና በድህረ ፈተና፣ እንዲሁም በቅድመ እና በድህረ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት ከሙከራና ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በቅደመና በድህረ ፈተና፣ አማካይነት ከሙከራና ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ አማካይና መደበኛ ልይይቱ ተስልቷል፡፡ እንዲሁም በቅድመ እና በድህረ የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ በመቶኛ በማስቀመጥ በገለፃ ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ሌላው ደግሞ ልዩነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቲ-ቴስትን መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩንና አለመኖሩን ለመፈተሽ የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በቀመሩ መሰረት የተገኘውን መረጃም እንደሚከተለው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 4.1.1 የቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና

በዚህ ክፍል የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ከልምምድ በፊት የተፈተኗቸው የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት የሚተነተኑ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት ስታስቲካዊ መረጃ ምን እንደሚመስል በተከታዩ

ሰንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል፣ በማስከተልም የሁለቱም ቡድኖች የአንብቦ መረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት አማካይነት ተተንትኖ ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ መረዳት የቅድመ ፈተና ውጤት**

| | ምድብ (Group) | ናሙና (N) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (Std. Deviation) | የመደበኛ ስህተት ልዩነት (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት ፍቺ እውቀት ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት | ሙከራ ቡድኑ | 30 | 40.9583 | 18.04772 | 3.29505 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 43.3750 | 13.05186 | 2.37636 |
| ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታ ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት | ሙከራ ቡደኑ | 30 | 11.4875 | 3.82966 | 0.69920 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 11.000 | 5.03650 | 0.91954 |
| አጠቃላይ ሀሳቦችን የመግለፅ ችሎታ ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት | ሙከራ ቡድኑ | 30 | 10.3333 | 3.81317 | 0.69619 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 8.5833 | 3.51618 | 0.64196 |
| አንብቦ መረዳት ችሎታ ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት(የ3ቱ ንዑሳን አላማዎች ድምር ውጤ) | ሙከራ ቡድኑ | 30 | 62.7708 | 22.10847 | 4.03644 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 62.9583 | 18.15131 | 3.31396 |

ሠንጠረዥ 4.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡደኖቹ በቅድመ ልምምዱ ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ያሳያል፡፡ በፈተናው ውጤት መሰረትም በቅድመ ልምምድ ፈተናው የሙከራ ቡድኑ የቃላት አውዳዊ ፍቺ እውቀት ችሎታ አማካይ ውጤት 40.9583 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 43.3750 ሆኗል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ አማካይ ውጤት 11.4875 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 11.0000 ሆኗል፡፡ እንዲሁም የሙራ ቡድኑ አጠቃላይ ሃሳብን የመረዳት (የመለየት) ችሎታ አማካይ ውጤት 10.3333 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 8.5833 ተመዝግቧል፡፡ በዚህ መሰረትም በቅድመ ልምምዱ ጊዜ የተመዘገበው አማካይ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ (40.9583 እና 43.375) ውጤት አንፃር የቁጥጥር ቡድኑም ሆነ የሙከራ ቡድኑ

ተቀራራቢ የቃላት ፍቺ ዕውቀት ያላቸው ሲሆን፤ዝርዝር ሀሳቦችንም የመለየት ችሎታ አማካይ ውጤታቸው የሙከራ ቡድኑ11.4875 ሲሆን፤የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 11.0000 ሆኗል፣ ይሄም በሁለቱም ቡድኖች ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታ ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብን የመለየት ችሎታቸውም ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል ምክንያቱም አማካይ ውጤታቸው የሙከራ ቡድኑ 10.3333 እና የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 8.5833 በመሆኑ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሁለቱ ቡድኖች በሶስቱ ንዐሳን የጥያቄ ምድቦች ያስመዘገቡት የአንብቦ መረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት የሙከራ ቡድኑ 62.7708 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 62.9583 ነው፡፡ ይህም ሁለቱም ቡድኖች በቅድመ ልምምዱ ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት አኳያ በመካከላቸው የጎላ ልዩነት ያለ አይመስልም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ብቻ የውጤት ተመሳስሏቸውን መግለፅ አስተማማኝ ስለማይሆን፣ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህም በቀጣዩ ሠንጠረዥ የሁለቱን ቡድኖች ቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.2 የሙከራና ቁጥጥር ቡድን አንብቦ የመረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራዊ ትንተና**

| | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | ጉልህነት (2 ጫፍ) | አማካይ ልዩነት | የመደበኛ ስህተት ልዩነት | 95% confidence Interval of Difference | |
| | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| የቃላት ፍቺ እውቀት የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት | ተጠባባቂ | -0.687 | 29 | 0.498 | 19.28108 | 3.52023 | -9.61634 | 4.78301 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | -0.687 | 29 | 0.498 | 19.28108 | 3.52023 | -9.61634 | 4.78301 |
| ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታ ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት | ተጠባባቂ | 0.440 | 29 | 0.663 | 6.06239 | 1.10684 | -1.77623 | 2.75123 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 0.440 | 29 | 0.663 | 6.06239 | 1.10684 | -1.77623 | 2.75123 |
| አጠቃላይ ሀሳቦችን የመግለፅ ችሎታ ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት | ተጠባባቂ | 1.915 | 29 | 0.065 | 5.00646 | 0.91405 | -0.11944 | -3.61944 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 1.915 | 29 | 0.065 | 5.00646 | 0.91405 | -0.11944 | -3.61944 |
| አንብቦ የመረዳት ችሎታ ቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት(የ3ቱ ድምር ውጤት) | ተጠባባቂ | 0.041 | 29 | 0.967 | 24.75916 | 4.52038 | -9.43272 | 9.05772 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 0.041 | 29 | 0.967 | 24.75916 | 4.52038 | -9.43272 | 9.05772 |

ሠንጠረዥ 4.2፣ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነትን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረትም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት የተገኘው ውጤት የቃላት አውዳ ፍች ችሎታ (t= 0.687፣df= 29፣ p= 0.498፣) ፣ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ (t= 0.440፣ df= 29፣ p= 0.663) እና አጠቃላይ መልዕክትን የመረዳትችሎታ (t= 1.915፣ df= 29፣ p= 0.065) ነው፡፡ ይሄም የሚያሳየን ቡለቱ

ቡድኖች መካከል ያለው የቃላት አውዳዊ ፍቺን የመለየት ችሎታ ተቀራራቢ ሲሆን፣ ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታቸውም ልዩነት አይታይበትም፤ እንዲሁም አጠቃላይ መልዕክትን የመለየት ችሎታቸውም ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአንብቦ መረዳት የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት (t= 0.041፣ df= 29፣ p= 0.967) እንደሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡ ምክንያቱም በቲ-ቴስት ስሌት በሚገኙ ውጤቶች መካከል ስታትስቲካዊ ልዩነት እንዳለ የሚታመነው የ‹‹p›› ዋጋ ከ 0.05 ያነሰ እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህም 0.967 ከ0.05 የበለጠ ስለሆነ የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት ጉልህ ባለመሆኑ የቡድኖቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ተቀራራቢ ነው ለማለት ያስችላል፡፡

### 4.1.2 የድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ውጤት ትንተና

በዚህ ንዑስ የትንተና ክፍል የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ከልምምድ በኋላ በተፈተኗቸው የአንብቦ መረዳት ፈተና ያገኙት አማካይ ውጤት ልዩነት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.2 የቀረበው ውጤት በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ አንብቦ የመረዳት የቅድመ ልምምድ አማካይ ውጤት ልዩነት አለመኖሩ/ ያለው ውጤት ተቀራራቢ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በሁለቱ የጥናት ቡድኖች መካከል የጎላ የችሎታ መበላለጥ አለመኖሩን ያሳየ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ ከተረጋገጠ በኋላ ሁለቱ ቡድኖች ለ4 ሳምንት የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ ኢ-ልቦለዳዊ በሆነ ዝርው ምንባባት ተለምዷዊ በሆነ የማስተማሪያ መንገድ ከተማሩ በኋላ የድህረ ልምምድ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ የፈተናው አጠቃላይ ውጤትም በቀጣዩ ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ4.3 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ መረዳት የደህረ ልምምድ ፈተና ውጤት

| | ምድብ (Group) | ናሙና (N) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (Std. Deviation) | የመደበኛ ስህተት ልዩነት (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት ፍቺ እውቀት ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | ሙከራ ቡድኑ | 30 | 49.0000 | 7.05123 | 1.28737 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 36.6667 | 16.15300 | 2.94912 |
| ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | ሙከራ ቡደኑ | 30 | 19.0000 | 3.46861 | 0.63328 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 14.9375 | 5.29402 | 0.96655 |
| አጠቃላይ ሀሳቦችን የመግለፅ ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | ሙከራ ቡድኑ | 30 | 15.1667 | 3.97640 | 0.72599 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 10.9583 | 5.38830 | 0.98376 |
| አንብቦ መረዳት ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት(የ3ቱ ንዑሳን አላማዎች ድምር) | ሙከራ ቡድኑ | 30 | 83.1667 | 10.32726 | 1.88549 |
| | ቁጥጥር ቡድኑ | 30 | 62.5458 | 23.95284 | 4.37317 |

ሠንጠረዥ 4.3፣ የሚያሳየው ሁለቱ ቡድኖች በድህረ ልምምዱ ፈተና ያስመዘገቡትን አማካይ ውጤት፣ መደበኛ ልይይት እና የመደበኛ ስህተት ልዩነት ነው፡፡ በፈተናው ውጤት መሰረትም በድህረ ልምምድ ፈተናው የሙከራ ቡድኑ የቃላት ፍቺ እውቀት ፈተና አማካይ ውጤት 49.0000 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 36.6667 ነው፤ይህም የሙከራ ቡድኑ የቃላት አውዳዊ ፍቺን የመለየት ችሎታቸው ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሌላው የሙከራ ቡድኑ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ የድህረ ልምምድ አማካይ ፈተና ውጤት 19.0000 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ውጤት ደግሞ 14.9375 ሆኗል፤ በዚህም የሙከራ ቡድኑ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታቸው ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ አጠቃላይ መልዕክትን(ሀሳብን) የመግለፅ ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት 15.1667 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 10.9583 ሆኗል፤ ስለዚህም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ አጠቃላይ መልዕክትን የመለየት ችሎታ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡

በአጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሲታይ የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት 83.1667 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 62. 5458 ነው፣ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት የሶስቱ ንዑሳን ዓላማዎች ድምር ውጤትም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ከቅድመ ልምምድ የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት የተሻለ ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ግን የድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ከቅድመ ልምምዱ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ጋር ተቀራራቢ ነው ለማለት ያስችላል፡፡ ይህም ጉልህ ልዩነት ስለማይታይበት፡፡ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የአንብቦ መረዳት አማካይ ውጤት 62.7708 ሲሆን፣ የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ 83.1667 ነው፡፡ ስለሆነም በድህረ ልምምዱ ያሳየው ልዩነትም 20.3959 ብልጫ ነው፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ስንመለከት ደግሞ በቅድመ ልምምድ 62.9583 ሲመዘገብ፣ በድህረ ልምምዱ ደግሞ 62.5458 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በመካከላቸው ያለው ልዩነት 0.4125 ነው፡፡ ይህም በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ያመላክታል፡፡ይሁን እንጂ በድህረ ልምምድ ፈተናዎች የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ አማካይ ውጤት አስመዝግቧል ለማለት ያስችላል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የሁለቱን ቡድኖች አጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ውጤት መደበኛ ልይይት ስንመለከት የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት መደበኛ ልይይቱ 7.05123 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 16.1530 ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመካከላቸው ያለው የመደበኛ ልዩነት ውጤት ስንመለከት የቁጥጥር ቡድኑ ከሙከራ 9.10177 ልዩነት አለው፡፡ቢሆንም በአማካኝ ውጤቱ ብቻ ጉልህ ልዩነት አለ ለማለት አስተማማኝ ስለማይሆን በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህም በቀጣዩ ሰንጠረዥ የሁለቱን ቡድኖች የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### ሠንጠረዥ 4.4 የሙከራና ቁጥጥር ቡድን አንብቦ የመረዳት የድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራዊ ትንተና

| | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | ጉልህነት (2 ጫፍ) | አማካይ ልዩነት | የመደበኛ ስህተት ልዩነት | 95% confidence Interval of Difference | |
| | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| የቃላት ፍቺ እውቀት የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | ተጠባባቂ | 3.702 | 29 | 0.001 | 18.24679 | 3.33139 | 5.51987 | 19.14680 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 3.702 | 29 | 0.001 | 18.24679 | 3.33139 | 5.51987 | 19.14680 |
| ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | ተጠባባቂ | 4.645 | 29 | 0.000 | 4.79018 | 0.87456 | 2.27382 | 5.85118 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 4.645 | 29 | 0.000 | 4.79018 | 0.87456 | 2.27382 | 5.85118 |
| አጠቃላይ ሀሳቦችን የመግለፅ ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | ተጠባባቂ | 4.374 | 29 | 0.000 | 5.27001 | 0.96217 | 2.24048 | 6.17619 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 4.374 | 29 | 0.000 | 5.27001 | 0.96217 | 2.24048 | 6.17619 |
| አንብቦ የመረዳት ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት(የ3ቱ ንዑስ አላማዎች ድምር ውጤት) | ተጠባባቂ | 4.800 | 29 | 0.000 | 23.52941 | 4.29586 | 11.83481 | 29.40686 |
| | ኢ-ተጠባባቂ | 4.800 | 29 | 0.000 | 23.52941 | 4.29586 | 11.83481 | 29.40686 |

ሠንጠረዥ 4.4 የሚያሣየው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ድህረ ልምምድ አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራዊ ልዩነትን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የድህረ ልምምድ ፈተናዎቹ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት የቃላት አውዳዊ ፍቺ እቀት (t= 3.702፣ df= 29፣ p= 0.001)፣ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ (t= 4.645፣ df= 29፣ p= 0.000)፣ አጠቃላይ ሃሳቦችን የመግለፅ ችሎታ (t= 4.374፣ df= 29፣ p= 0.000)፣ አጠቃላይ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት (t= 4.800፣ df= 29፣ p= 0.000)፣ ነው፡፡ ይህ ውጤትም የሚያሳየው

በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መኖሩን ነው፡፡ ምክንያቱም በቲ-ቴስት ስሌት ልዩነት መኖሩ የሚታወቀው ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 ያነሰ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር የሙከራ ቡድኑ የቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ዕውቀት ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ሲሆን፤ ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ልዩነት እንዳለው ያስገነዝበናል፤ እንዲሁም አጠቃላይ ሀሳብን ለይቶ የመግለፅ ችሎታቸውም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ነው፡፡ ስለዚህም አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የቃላት ዐውዳዊ ፍቺን ለማሳደግ፣ የምንባቡን ዝረዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታቸውን ለማዳበር፣ እንዲሁም የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለይቶ የመግለፅ ችሎታቸውን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን መረጀው ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረትም የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድህረ ልምምድ P= 0.000 መሆኑ ከ0.05 መቁረጫ ነጥብ በማነሱ ጉልህ ልዩነት ሊኖረው ችሏል፡፡

#### 4.1.3 የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና

ይህ የትንተና ንዑስ ክፍል የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቶች አማካይ ልዩነት በባዕድ ናሙናቲ-ቴስት ተተንትኖ የሚቀርብበት ነው፡፡ ቀደም ሲል በቀረበው 4.4 ሠንጠረዥ እንደተመለከትነው የሙከራ ቡድኑ በሁሉም ደረጃ ለውጥ አምጥቷል፣ ይህም የሙከራ ቡድኑ አባላት ለ4 ሳምንት ባገኙት አጭር ልቦለዶችን ተጠቅሞ አንብቦ የመረዳት ትምህርት፣ የቃላት አውዳዊ ፍቺን የመለየት ችሎታ፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት እና አንብቦ ተረድቶ መግለፅ ላይ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሸለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የቃላት አውዳዊ ፍቺን የመለየት ችሎታ የተመዘገበ የ‹‹p›› ዋጋ 0.001 ሲሆን፣ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ የ‹‹p›› ዋጋ 0.000 ሆኗል፣ አጠቃላይ አሳቦችን ተረድቶ የመግለፅ ችሎታ ደግሞየ‹‹p›› ዋጋ 0.000 ነው፡፡ይህ ደግሞ ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 ያነሰ በመሆኑ በሶስቱም ንዑሳን ዓላማዎች ላይ ጉልህ/የጎላ ልዩነት ተመዝግቧል፡፡ እንዲሁም አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህን ለማለት ያስቻለንየ‹‹p›› ዋጋ 0.000 በመሆኑና ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 ያነሰ ስለሆነ ጉልህ ልዩነት ታይቷል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በታች የሁለቱን ቡድኖች የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት በባህድ ናሙና ቲ-ቴስት በቅደም ተከተል ይቀርባል፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት

| | | አማካይ (Mean) | ናሙና (N) | መደበኛ ልይይት (Std. Deviation) | መደበኛ ስተት አማካይ (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥንድ-1 | የቃላት ፍቺ ቅድመ ልምምደ | 40.9583 | 30 | 18.04772 | 3.29505 |
| | የቃላት ፍቺ ድህረ ልምምድ | 49.000 | 30 | 7.05123 | 1.28737 |
| ጥንድ-2 | ዝርዝር ሃሳብ መረዳት ቅድመ ልምምድ | 11.4875 | 30 | 3.82966 | 0.69920 |
| | ዝርዝር ሃሳብ መረዳት ድህረ ልምምድ | 19.0000 | 30 | 3.46861 | 0.63328 |
| ጥንድ-3 | አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ቅድመ ልምምደ | 10.3333 | 30 | 3.81317 | 0.69619 |
| | አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ድህረ ልምምድ | 15.1667 | 30 | 3.97640 | 0.72599 |
| ጥንድ-4 (የ3ቱ ንዑሳን አላማዎ ድምር) | አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምድ | 62.7708 | 30 | 22.10847 | 4.03644 |
| | አንብቦ መረዳት ድህረ ልምምደ | 83.1667 | 30 | 10.3276 | 1.88549 |

በሠንጠረዥ 4.5 የቀረበው ስታትስቲካዊ መረጃ የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለዶች ከተማሩ በኋላ የቃላት አውዳዊ ፍቺ የመስራት ችሎታ አማካይ ውጤት 8.0417፣ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ አማካይ ውጤት 7.5125፣ አጠቃላይ መልዕክትን የመግለፅ ችሎታ 4.8334 ሲያድግ፡፡ እንዲሁም አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በ20.3959 አማካይ ውጤት አድጓል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ፈተናው ያስመዘገበው ውጤት ከቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል ያሳየ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ በአማካይ ውጤቱ ብቻ ልዩነት/መሻሻል አለ ብሎ መወሰኑ አስተማማኝ ስለማይሆን ልዩነቱ ምን ያህል ስታትስቲካዊ ጉልህነት እንዳሳየ በዳግም ልኬት ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ትንታኔው ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ 4.6የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራ ትንተና

| | | የጥንድ ልዩነቶች (Paired Differences) | | | | | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (ባለ 2 ጫፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የመደበኛ ስህተት አማካይ | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| ጥንድ-1 | የቃላት ፍቺ ቅድመ ልምምድ የቃላት ፍቺ ድህረ ልምምድ | -8.04167 | 18.37904 | 3.35554 | -14.90451 | -1.17882 | -2.397 | 29 | 0.023 |
| ጥንድ-2 | ዝርዝር ሃሳብ ቅድመ ልምምድ ዝርዝር ሃሳብ ድህረ ልምምድ | -7.51250 | 3.60934 | 0.65897 | -8.86025 | -6.16475 | -11.400 | 29 | 0.000 |
| ጥንድ-3 | አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ቅድመ ልምምድ አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ድህረ ልምምድ | -4.83333 | 4.69700 | 0.85755 | -6.58722 | -3.07945 | -5.636 | 29 | 0.000 |
| ጥንድ-4 (የ3ቱ ንዑሳን አላማዎች ድምር) | አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምደ አንብብ መረዳት ድህረ ልምምድ | -2.03958 | 20.03061 | 3.65707 | -27.87539 | -12.91628 | -5.577 | 29 | 0.000 |

የሙከራ ቡድኑን የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት ለማረጋገጥ በሠንጠረዥ 4.6 የቀረበውን ስንመለከት፣ በሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት ተመዝግቧል፡፡ የአንብቦ መረዳት ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተናዎች ውጤትም፣ የቃላት ፍቺን የመስራት እውቀት (t= -2.397፣ df=29፣p=0.023)፣ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ (t= -11.400፣ df=29፣ p=0.000)፣ አጠቃላይ ሃሳቦችን/ መልዕክትን የመግለፅ ችሎታ (t= -5.636፣ df=29፣ p=0.000)፣ አንብቦ መረዳት ችሎታ (t= -5.577፣ df=29፣ p=0.000) በመሆኑም በሁሉም ደረጃ ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ ምክንያቱም ከቃላት ፍቺ እውቀት፣ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ፣ አጠቃላይ መልዕክትን የመግለፅችሎታ እና አንብቦ መረዳት እንደ ቅደም ተከተላቸው የ‹‹p›› ዋጋ (0.023፣ 0.000፣ 0.000 እና 0.000) በመሆኑና ይህም ውጤት ከተቀመጠው የጉልህነት መቁረጫ ነጥብ ከ0.05 ያነሱ/ያልበለጡ ስለሆኑ ነው፡፡ በዚህም ውጤት መሰረት የሙከራ ቡድኑ አባላት አንብቦ መረዳትን በአጭር

ልቦለድ ከተማሩ በኋላ ከቀድሞ ብቃታቸው በሶስቱም ንዑሳን ዓላማዎች በተሻለ መልኩ አንብቦ መረዳት መቻላቸውን ያመለክታል፡፡ ከሙከራ ቡድኑ ባሻገር የቁጥጥር ቡድኑም ከ4ሳምንት ትምህርት በኋላ በተሰጣቸው የድኅረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ልምምዱ ፈተና አማካይ ውጤት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል ያሳየ አይመስልም፡፡ በመሆኑም በቅድመ ልምምዱና በድህረ ልምምዱ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ስታትስቲካዊ ጉልህነት ምን ያህል እንደሆነ በቀጣዩ ሰንጠረዥ እንመለከታለን፡፡

### ሠንጠረዥ 4.7 የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት

| | | አማካይ (Mean) | ናሙና (N) | መደበኛ ልይይት (Std. Deviation) | መደበኛ ስተት አማካይ (Std. Error Mean) |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥንድ-1 | የቃላት ፍቺ ቅድመ ልምምደ | 43.3750 | 30 | 13.01586 | 2.37636 |
| | የቃላት ፍቺ ድህረ ልምምድ | 36.6667 | 30 | 16.15300 | 2.94912 |
| ጥንድ-2 | ዝርዝር ሃሳብ መረዳት ቅድመ ልምምድ | 11.0000 | 30 | 5.03650 | 0.91954 |
| | ዝርዝር ሃሳብ መረዳት ድህረ ልምምድ | 14.9375 | 30 | 5.29402 | 0.96655 |
| ጥንድ-3 | አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ቅድመ ልምምደ | 8.5833 | 30 | 3.51618 | 0.64196 |
| | አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ድህረ ልምምድ | 10.9583 | 30 | 5.38830 | 0.98376 |
| ጥንድ-4 (የንዑሳን አላማዎች ደምር) | አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምድ | 62.9583 | 30 | 18.15131 | 3.31396 |
| | አንብቦ መረዳት ድህረ ልምምደ | 62.5458 | 30 | 23.95284 | 4.37317 |

ሠንጠረዥ 4.7 ላይ እንደምንመለከተው የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት የቃላት ፍቺ ችሎታ ድህረ ልምምድ 43.3750፣ ወደ 36.6667 ዝቅ ሲል ልዩነቱም (6.7083)፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መረዳት/መለየት ከ11.0000 ወደ 14.9375 (3.9375) ከፍ ሲል፣አጠቃላይ ሀሳቦችን/መልዕክትን የመግለፅ ችሎታ ከ8.5833 ወደ 10.9583 (2.375) ከፍ ሲል፣ በተቃራኒው አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ውጤት

ከ62.9583 ወደ 62.5458 (0.4125) ዝቅ ብሏል፡፡ በዚህ መሰረት ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየትና አጠቃላይ መልዕክትን /ሃሳቦችን የመግለፅ ችሎታ ላይ ጉልህ የውጤት ልዩነት ያሳየ ሲሆን፣ ነገር ግን የቃላት አውዳዊ ፍቺ መለየትና አጠቃላይ አንብቦ መረዳት ላይ ግን የድህረ ልምምዱ ውጤት ከቅድመ ልምምድ ውጤት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ይመስላል፡፡ ሆኖም በአማካይ ውጤታቸው ብቻ ጉልህ ልዩነት አለ ወይም የለም ብሎ ለማለት አስተማማኝ ስለማይሆን በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህም በቀጣዩ ሠንጠረዥ የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ንፅፅራዊ ትንተናን እንመለከታለን፡፡

**ሠንጠረዥ 4.8 የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት የቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት ንፅፅራ ትንተና**

| | | የጥንድ ልዩነቶች (Paired Differences) | | | | | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት (ባለ 2 ጫፍ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የመደበኛ ስህተት አማካይ | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| ጥንድ-1 | የቃላት ፍቺ ቅድመ ልምምድ የቃላት ፍቺ ድህረ ልምምድ | 6.70833 | 11.78326 | 2.15132 | 230839 | 11.10827 | 3.118 | 29 | 0.004 |
| ጥንድ-2 | ዝርዝር ሃሳብ ቅድመ ልምምድ ዝርዝር ሃሳብ ድህረ ልምምድ | -3.93750 | 6.77762 | 1.23742 | -6.46831 | -1.40669 | -3.182 | 29 | 0.003 |
| ጥንድ-3 | አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ቅድመ ልምምድ አጠቃላይ ሃሳብ መግለፅ ድህረ ልምምድ | -2.37500 | 5.07593 | 0.92673 | -4.27038 | -0.47962 | -2.563 | 29 | 0.016 |
| ጥንድ-4 (የ3ቱ ንዑሳን አላማዎች ድምር ውጤት) | አንብቦ መረዳት ቅድመ ልምምደ አንብብ መረዳት ድህረ ልምምድ | -41250 | 17.35401 | 3.16839 | -6.06760 | 6.89260 | 0.130 | 29 | 0.897 |

የቁጥጥር ቡድኑ ለ4 ሳምንት በተለመደው መንገድ ከተማሩ በኋላ የድህረ ልምምድ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በፈተናው ያገኙት ውጤትም ከቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤታቸው ጋር ተነፃፅሯል፡፡

በሠንጠረዥ 4.8 እንደሚያመለክተው የቃላት አውዳዊ ፍቺ እውቀት (t=3.118፣ df=29፣ p=0.000)፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት (t= -3.182፣ df=29፣ p=0.003)፣ አጠቃላይ መልዕክትን/ሃሳቦችን መግለፅ (t= -2563፣ df=29፣ p=0.016) ሲሆን፣ የሶስቱም ንዑሳን አላማዎች አንብቦ መረዳት ድምር ውጤት (t=0.130፣ df=29፣ p=0.897) ነው፡፡ይህም የሚያመለክተው በሶስቱ ንዑሳን አላማዎች መካከል ጉልህ ዩነት የቃላት ፍቺ፣ ዝርዝር ሃሳብ መለየትና መልዕክት መረዳት በቅደም ተከተል የጉልህነት ውጤት (0.004፣ 0.003፣ 0.016) ሲሆን ይሄም ከጉልህነት መለያ ነጥብ ከ0.05 ያነሰ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ዝቅተኛ የጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ አጠቃላይ አንብቦ መረዳት ላይ ያለው የጉልህ ልዩነት 0.897 ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ከጉልህነት መለያ ነጥብ ከ0.05 የበለጠ ስለሆነ ልዩነት የለውም ወደሚለው ያመለክታል፡፡ ስለዚህም በውጤቱ መሰረት ጉልህ ልዩነት የለም የሚል ይሆናል፡፡

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት የድህረ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤት በጥንድ ስንመለከተው ስታትስቲካዊ ጉልህነት ያለው ሲሆን፤ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤትን በጥንድ ስነሰመለከተው ግን ስታትስቲካዊ ጉልህነት አይስተዋልበትም/የለውም፡፡ በድህረ ልምምዱ ያስመዘገቡት የ‹‹p›› ዋጋ የቃላት አውዳዊ ፍቺ እውቀት 0.001፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት 0.000፣ አጠቃላይ ሃሳብን መግለፅ/አንብቦ መረዳት 0.000፣ እና አጠቃላይ አንብቦ መረዳት 0.000 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

በዚህ መሰረትም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ድህረ ልምምድ አማካይ ውጤት ስታትስቲካዊ ጉልህ ልዩነት ያሳየ ነው ማለት ያስችላል፡፡ ነገር ግን የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት የ‹‹p›› ዋጋ የቃላት አውዳዊ ፍቺ እውቀት 0.498፣ ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታ 0.663፣ አንብቦ መረዳት/አጠቃላይ ሃሳብን መግለፅ 0.065፣ እና አጠቃላይ አንብቦ መረዳት ችሎታ 0.967 ሆኗል፡፡ ከዚህ ውጤት አኳያምየሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ቅድመ ልምምድ ፈተና አማካይ ውጤትን በጥንድ ስንመለከት ግን ስታትስቲካዊ ጉልህነት አይስተዋልበትም (የለውም ማለት) እንችላለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ቅድመ ልምምድ እና ድህረ ልምምድ ተናጥላዊ ውጤት ስናነፃፅር በሰንጠረዥ 4.6 እና 4.8 ያለው የ‹‹p››ውጤት

እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ልምምድ የቃላት አውዳዊ ፍቺ እውቀት 0.023፣ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት 0.000፣ አጠቃላይ መልዕክትን መግለፅ/አንብቦ መረዳት 0.000 እና አጠቃላይ አንብቦ መረዳት 0.000 ሆኗል፡፡ ይህም ከመቁረጫ ነጥቡ ከ0.05 ያነሰ ስለሆነ ጉልህነት ታይቶበታል ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ያስመዘገበው ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ልምምድ ካስመዘገበው ውጤት የተሻለ ልዩነት አሳይቷል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ልምምድ ተናጠላዊ ውጤት ሠንጠረዥ 4.8 እንደሚያመለክተው የ‹‹p›› ዋጋ የቃላት አውዳዊ ፍቺ እውቀት 0.004፣ ዝርዝር ሃሳብን መለየት 0.003፣ አንብብ መረዳት/አጠቃላይ ሀሳብን መግፅ 0.016 ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረትም ጉልህ ልዩነት አለ ለማለት ያስችላል፡፡ ምክንያቱም በሶስቱም ንዑሳን ርእሶች የተመዘገበው ስታትስቲካዊ ጉልህነት ከ0.05 ያነሰ በመሆኑ፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ አንብቦ መረዳትን ስንመለከት ውጤቱ 0.897 ሆኗል፡፡ ይሄ ደግሞ ከመቁረጫ ነጥቡ ከ0.05 የበለጠ በመሆኑ ጉልህ ልዩነት የለውም ማለት ያስችላል፡፡

### 4.1.4 ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና

### ሀ. በአይነታዊ ትንተና

በዚህ ክፍል ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ እግብ ለማድረስ ከተማሪዎች የተገኙትን የፅሁፍ መጠይቅ መልስ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም የፅሁፍ መጠይቁ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ንዑሳን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ በሶስት ክፍሎች በመክፈል እንደጥያቄዎቹ ቅርበት ለመመደብ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ሁኔታም በክፍል አንድ የምንባብን ሀሳብ (መልዕክትን) መረዳትን መሰረት ያደረገ 6 ዝግ ጥያቄዎች የያዘ ሲሆን፣ በክፍል ሁለት ደግሞ የቃላትን ፍቺ መሰረት ያደረጉ 3 ዝግ ጥያቄዎች እና በሶስተኛው ክፍል ደግሞ ዝርዝር ሃሳቦችን የመረዳት ችሎታን መሰረት ያደረጉ 3 ዝግ ጥያቄዎችን ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት ከተማሪዎች የተገኙትን የፅሁፍ መጠይቅ መልስ አረፍተ ነገሮቹ እንደያዙት የሀሳብ ቅርበት ከክፍል አንድ እስከ ክፍል ሶስት እንደሚከተለው በገለፃ መንገድ ተተንትነዋል፡፡

**ክፍል አንድ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች**

4.አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች በምንባቡ ሊተላለፍ የፈለገውን መልዕክት የመገንዘብ አቅማቸው እንዲጎለብት ያስችላል፡፡

5.አጭር ልቦለድ ቀጣይነት ያለው የአንባቢነት የህይወት ልምድ እንዲኖረን ያስችላል፡፡

7.በአጭርልቦለድ መማር የአንብቦ መረዳት ክሂልን ያዳብራል፡፡

13.አጭር ልቦለድ ተማሪዎች ስለሌሎች በህል እንዲያውቁ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

14.አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የምንባቡን ሃሳብ ፍሰት ጠብቀው የመረዳት አቅማቸው እንዲጎለብት ያስችላል፡፡

16.አጭር ልቦለድ ማንበብ በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመግለፅ አቅምን ያዳብራል፡፡

## ሠንጠረዥ4.9 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ትንተና (በአይነታዊ መንገድ)

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | 4 | 3 | 2 | 1 | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 4 እና 3 | 2 እና 1 |
| 4 | በቁጥር | 10 | 18 | 2 | - | 28 | 2 |
| | በመቶኛ | 33.3% | 60% | 6.6% | - | 93.3% | 6.6% |
| 5 | በቁጥር | 9 | 17 | 3 | 1 | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 30% | 56.6% | 10% | 3.3% | 86.6% | 13.3% |
| 7 | በቁጥር | 17 | 11 | 2 | - | 28 | 2 |
| | በመቶኛ | 56.6% | 36.6% | 6.6% | - | 93.3% | 6.6% |
| 13 | በቁጥር | 11 | 13 | 4 | 2 | 24 | 6 |
| | መቶኛ | 36.6% | 43.3% | 13.3% | 6.6% | 80% | 20% |
| 14 | በቁጥር | 11 | 10 | 8 | 1 | 21 | 9 |
| | በመቶኛ | 36.6% | 33.3% | 26.6% | 3.3% | 70% | 30% |
| 16 | በቁጥር | 8 | 18 | 4 | - | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 26.6% | 60% | 13.3% | - | 86.6% | 13.3% |
| አማካይ | በመቶኛ | 36.62% | 48.3% | 12.73% | 2.2% | 84.97% | 14.96% |

ሠንጠረዥ 4.10 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | 4 | 3 | 2 | 1 | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 4 እና 3 | 2 እና 1 |
| 4 | በቁጥር | 20 | 10 | - | - | 30 | - |
| | በመቶኛ | 66.6% | 33.3% | - | - | 100% | - |
| 5 | በቁጥር | 13 | 12 | 5 | - | 25 | 5 |
| | በመቶኛ | 43.3% | 40% | 16.6% | - | 83.3% | 16.6% |
| 7 | በቁጥር | 12 | 16 | 2 | - | 28 | 2 |
| | በመቶኛ | 40% | 53.3% | 6.6% | - | 93.3% | 6.6% |
| 13 | በቁጥር | 11 | 13 | 4 | 2 | 24 | 6 |
| | መቶኛ | 36.6% | 43.3% | 13.3% | 6.6% | 80% | 20% |
| 14 | በቁጥር | 10 | 16 | 3 | 1 | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 33.3% | 53.3% | 10% | 3.3% | 86.6% | 13.3% |
| 16 | በቁጥር | 14 | 11 | 4 | 1 | 25 | 5 |
| | በመቶኛ | 46.6% | 36.6% | 13.3% | 3.3% | 83.3% | 16.6% |
| አማካይ | በመቶኛ | 44.4% | 43.3% | 9.97% | 2.2% | 87.75% | 12.18% |

በሠንጠረዥ 4.9 እና 4.10 የቀረበው ጥያቄ 4 የሚያመለክተው አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመገንዘብ አቅማቸው እንዲጎለብት ከማስቻል አንፃር ያለውን ጥቅም የሚገልፁበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 28 እና በመቶኛ 93.3% ሲሆኑ፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) ብለው የመለሱ ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 2 እና በመቶኛ 6.6% ናቸው፡፡

በሠንጠረዥ 4.10 የቀረበው ጥያቄ 4 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የሰጠው ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) ብለው የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 30 እና በመቶኛ ደግሞ 100% ነው፡፡ እንዲሁም አልስማማም(2) እና

ፈፅሞ አልስማማም(1) የሚል ምላሽ የሰጠ ተማሪ ደግሞ ምንም የለም፡፡

ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑም ሆነ የሙከራ ቡድኑ አጭር ልቦለድ በምንባብ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመገንዘብ አቅምን ያሳድጋል የሚለው ሃሳብ ላይ ግንዛቤ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

በሠንጠረዥ 4.9 እና 4.10 የቀረበውን ጥያቄ 5፣ ስንመለከት አጭር ልቦለድ ቀጣይነት ያለው የአንባቢነት የህይወት ልምድ እንዲኖር ያስችላል የሚለውን ሃሳብ ተማሪዎች መልስ የሚሰጡበት ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የተሰጡትን ምላሾች ስንመለከት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ምላሽ በቁጥር 26 እና በመቶኛ 86.6% ነው፡፡ እንዲሁም አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) ማለት ደግሞ የሰጡት ምላሽ በቁጥር 4 እና በመቶኛ ደግሞ 13.3% ነው፡፡

በተጨማሪም በሠንጠረዥ 4.10 ለጥያቄ 5፣ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ጊዜ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 25 እና በመቶኛ 83.3% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የመለሱት ደግሞ በቁጥር 5 እና በመቶኛ 16.6% ነው፡፡

ከላይ ከቀረው መረጃ መረዳት የሚቻለው በሁለቱም ምድብ ያሉ ተማሪዎች አጭር ልቦለድ ማንበብ ቀጣይነት ያለው የአንባቢነት ልምድን የሚያጎለብት መሆኑን ግንዛቤ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ 4.9 እና 4.10 የቀረበው ጥያቄ 7፣ የሚገለፀው በአጭር ልቦለድ መማር የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሳደግ አንፃር ያለውን ሚና/ አስተዋፅኦ የሚገልፁበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቁጥጥር ቡድኑ የሰጠው ቅድመ ልምምድ ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 28 እና በመቶኛ 93.3% ነው፡፡ እንዲሁም አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት ደግሞ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በቁጥር 2 እና በመቶኛ 6.6% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.10 ደግሞ ለጥያቄ ቁጥር 7፣ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 28 እና በመቶኛ 93.3% ሲሆን፤ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት የሰጡት መልስ በቁጥር 2 እና በመቶኛ 6.6% ነው፡፡

ከላይ በሁለቱ ሰንጠረዦች የቀረበው ጥያቄ ቁጥር 7፣ መረጃ የሚያመለክተው በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ አጭር ልቦለድ ቀጣይነት ያለው የአንባቢነት የህይወት ልምድ የሚያዳብር መሆኑን ግንዛቤ እንዳላቸው ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.9 የቀረበው ጥያቄ 13፣ የሚገልፀው አጭር ልቦለድ ተማሪዎች ስለሌሎች ባህል እንዲያውቁ ፍንጭ ይሰጣል የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ምላሽ የሚሰጡበት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 24 እና በመቶኛ 80% ሲሆን፤ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የተሰጠ መልስ ደግሞ በቁጥር 6 እና በመቶኛ 20% ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4.10 ለቀረበው ጥያቄ 13፣ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስን ስንመለከት በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 26 እና በመቶኛ 86.6% ሲሆን፤ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የተሰጠ ምላሽ ደግሞ በቁጥር 4 እና በመቶኛ 13.3% ነው፡፡

ከላየ በጥያቄ ቁጥር 13፣ ከቀረው መረጃ መረዳት የሚቻለው በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ምላሽ አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች ስለሌሎች ባህል እንዲያውቁ አስተዋፅኦ ያደርጋል የሚል መረጃ/ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳየናል፡፡

በሠንጠረዥ 4.9 የቀረበው ጥያቄ 14፣ የሚገልፀው አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የምንባቡን ሃሳብ ፍሰት ጠብቀው የመረዳት አቅማቸው እንዲጎለብት ከማስቻል አንፃር ያላቸውን ሃሳብ የሚገልፁበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ በጣም እስማማለሁ (4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የተሰጠ ምላሽ በቁጥር 21 እና በመቶኛ 70 ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት ደግሞ የሰጠ ምላሽ ብዛት በቁጥር 9 እና በመቶኛ ደግሞ 30% ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በሠንጠረዥ 4.10 የቀረበው ጥያቄ ቁጥር 14፣ መሠረት በማድረግ የሙከራ ቡድኑ የሰጠው ቅድመ ልምምድ ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 26 እና በመቶኛ 86.6% ነው፤ እንዲሁም አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት የተሰጠ መልስ ደግሞ በቁጥር 4 እና በመቶኛ ደግሞ 13.3% ነው፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ 4.9 እና 4.10 ለጥያቄ ቁጥር 14፣ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ የሰጠው መልስ ከቁጥጥር ቡድኑ አንፃር ሲታይ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የተመለሰው በመቶኛ 86.6% ነው፡፡ ስለዚህም የሙከራ ቡድኑ በ16.6% የተሻለ ብልጫ ከቁጥጥር ቡድኑ ምላሽ መስጠቱን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱም ቡድኖች ከግማሽ በላይ በመመለሳቸው አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የምንባቡን ሃሳብ ፍሰት ጠብቆ የመረዳት አቅምን የሚያሳድግ መሆኑን መረጃ እንዳላቸው ያስገነዝበናል፡፡

በሠንጠረዥ 4.9 እና 4.10 የቀረበው ጥያቄ 16፣ የሚያመለክተው አጭር ልቦለድ ማንበብ በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመግለፅ አቅምን ከማሳደግ አኳያ ምላሽ የሚሰጡበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 26 እና በመቶኛ 86.6% ነው፡፡ እንዲሁም አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት ደግሞ ቁጥር 4 እና በመቶኛ 13.3% ነው፡፡

በተያያዘ ሁኔታ ደግሞ በሰንጠረዥ 4.10 ለቀረበው ጥያቄ 16፣ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 25 እና መቶኛ 83.3% ሲሆን፤ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት ደግሞ የተሰጠ መልስ በቁጥር 5 እና በመቶኛ 16.6% ነው፡

ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት የሚቻለው የቁጥጥሩም ሆነ የሙከራ ቡድኑ አጭር ልቦለድ ማንበብ በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመግለፅ አቅምን እንደሚያሳድግ ምላሻቸው ያሳየናል፡፡

**ሠንጠረዥ4.11 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ትንተና (በአይነታዊ መንገድ)**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | 4 | 3 | 2 | 1 | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 4 እና 3 | 2 እና 1 |
| 4 | በቁጥር | 11 | 17 | 2 | - | 28 | 2 |
| | በመቶኛ | 36.6% | 56.6% | 6.6% | - | 93.3% | 6.6% |
| 5 | በቁጥር | 10 | 16 | 3 | 1 | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 33.3% | 53.3% | 10% | 3.3% | 86.6% | 13.3% |
| 7 | በቁጥር | 16 | 10 | 3 | 1 | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 53.3% | 33.3% | 10% | 3.3% | 86.6% | 13.3% |
| 13 | በቁጥር | 11 | 11 | 5 | 3 | 22 | 8 |
| | መቶኛ | 36.6% | 36.6% | 16.6% | 10% | 73.3% | 26.6% |
| 14 | በቁጥር | 10 | 12 | 7 | 1 | 22 | 8 |
| | በመቶኛ | 33.3% | 40% | 23.3% | 3.3% | 73.3% | 26.6% |
| 16 | በቁጥር | 11 | 13 | 6 | - | 24 | 6 |
| | በመቶኛ | 36.6% | 43.3% | 20% | - | 80% | 20% |
| አማካይ | መቶኛ | 38.28% | 43.85% | 14.42% | 3.32% | 82.18% | 17.73% |

**ሠንጠረዥ 4.12 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | 4 | 3 | 2 | 1 | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 4 እና 3 | 2 እና 1 |
| 4 | በቁጥር | 20 | 8 | 2 | - | 28 | 2 |
| | በመቶኛ | 66.6% | 26.6% | 6.6% | - | 93.3% | 6.6% |
| 5 | በቁጥር | 14 | 9 | 5 | 2 | 23 | 7 |
| | በመቶኛ | 46.6% | 30% | 16.6% | 6.6% | 76.6% | 23.3% |
| 7 | በቁጥር | 11 | 15 | 3 | 1 | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 36.6% | 50% | 10% | 3.3% | 86.6% | 13.3% |
| 13 | በቁጥር | 14 | 10 | 5 | 1 | 24 | 6 |
| | መቶኛ | 46.6% | 33.3% | 16.6% | 3.3% | 80% | 20% |
| 14 | በቁጥር | 12 | 10 | 5 | 3 | 22 | 8 |
| | በመቶኛ | 40% | 33.3% | 16.6% | 10% | 73.3% | 26.6% |
| 16 | በቁጥር | 12 | 14 | 4 | - | 26 | 4 |
| | በመቶኛ | 40% | 46.6% | 13.3% | - | 86.6% | 13.3% |
| አማካይ | በመቶኛ | 46.07% | 36.63% | 13.28% | 3.87% | 82.73% | 17.18% |

ሠንጠረዥ 4.11 እና 4.12፣ ላይ የቀረበውን ውጤት ስንመለከት በተራ ቁጥር 4፡ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ በቅድመ ልምምድ ወቅት በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ የተሰጡት ምላሾች እና በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የተሰጠው ምላሽ በአብዛኛው ተመሳሳይ ውጤት ያለው ሲሆን፣ የጎላ ልዩነትም አይታይበትም፡፡ እንዲሁም በድህረ ልምምድ ወቅት በቁጥጥር ቡድኑ ለጥያቄ 5፣ የተሰጠ ምላሽ ደግሞ 76.6% በመቶ ነው፡፡ ይሄም የቁጥጥር ቡድኑ 10% በመቶ አብላጫ ውጤት እንዳለውና ከሙከራ ቡድኑ መሻሉን ያሳያል፡፡

በሌላው በኩል ደግሞ በሠንጠረዥ 4.11 እና 4.12፣ የቀረበውን ውጤት ስንመለከት በጥያቄ ተራ ቁጥር 7 እና 14 ለቀረቡት ጥያቄዎች በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የተሰጡት መልሶች ምንም አይነት ልዩነት የለውም ወይም

ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይሄውም በመቶኛ ስንመለከተው ለጥያቄ ቁጥር 7፣ የቁጥጥር ቡድኑ የሰጠው ምላሽ በጣም እስማማለሁእና እስማማለሁ በማለት 86.6% በመቶ ሲሆን፤ የሙከራ ቡድኑ የሰጠው መልስም 86.6% በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም በጥያቄ ተራ ቁጥር 14፣ የቁጥጥር ቡድኑ የሰጠው ድህረ ልምምድ መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ 73.3% በመቶ ሲሆን፤ የሙከራ ቡድኑም በተመሳሳይ መልኩ የሰጠው ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ 73.3% በመቶ ነው፡፡ ይሄም በአንፃራዊነት የሁለቱም ምድቦች ውጤት ሲታይ ምንም አይነት ልዩነት አይታይበትም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሠንጠረዥ 4.11 እና 4.12፣ በጥያቄ ቁጥር13፣ ላይ ያለውን ስንመለከት በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የተሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት 73.3% በመቶ ሲሆን፤ በሙከራ ቡድኑ ደግሞ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የተሰጠ መልስ 80% በመቶ ነው፡፡ የሂም ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አንፃር ሲታይ 6.7% በመቶ የሙከራ ቡድኑ ውጤት ብልጫ ያሳያል፡፡ ይህ በመሆኑም በድህረ ልምምድ ወቅት የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች ስለሌሎች ባህል እንዲያውቁ ፍንጭ እንደሚሰጥ ግንዛቤ እንዳገኙ ነው፡፡

እንዲሁም በሠንጠረዥ 4.11 እና 4.12፣ በጥያቄ 16፣ ላይ የቀረበውን ጥያቄ ስንመለከት በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የተሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት 80% በመቶ ሲሆን፤ በሙከራ ቡድኑ የተሰጠው መልስ ደግሞ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት 86.6% በመቶ ነው፡፡ ይህ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ጋር ያለው ልዩነት 6.6% በመቶ ሲሆን፤ ይሄም የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ ማንበብ በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመግለፅ አቅምን እንደሚያሳድግ ግንዛቤ ማግኘታቸውን ያመለክታል፡፡

**በክፍል ሁለት ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች**

2. አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ዕውቀትን ያሳድጋል፡፡
12.አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ትርጉም የማብራራት ችሎታን ለማሳደግ ያስችላል፡፡
20. አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ የመስራት ዕውቀታቸውእንዲጎለብት ያስችላል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.13 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 2 | በቁጥር | 14 | 15 | 1 | - | 29 | 1 |
| | በመቶኛ | 46.6% | 50% | 3.3% | - | 96.6% | 3.3% |
| 12 | በቁጥር | 15 | 9 | 4 | 2 | 24 | 6 |
| | በመቶኛ | 50% | 30% | 13.3% | 6.6% | 80% | 20% |
| 20 | በቁጥር | 11 | 9 | 6 | 4 | 20 | 10 |
| | በመቶኛ | 36.6% | 30% | 20% | 13.3% | 66.6% | 33.3% |
| አማካይ | በመቶኛ | 44.4% | 36.67% | 12.2% | 6.63% | 4.13% | 18.87% |

**ሠንጠረዥ 4.14 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 2 | በቁጥር | 13 | 15 | 2 | - | 28 | 2 |
| | በመቶኛ | 43.3% | 50% | 6.6% | - | 93.3% | 6.6% |
| 12 | በቁጥር | 5 | 15 | 9 | 1 | 20 | 10 |
| | በመቶኛ | 16.6% | 50% | 30% | 3.3% | 66.6% | 33.3% |
| 20 | በቁጥር | 8 | 14 | 2 | 6 | 22 | 8 |
| | በመቶኛ | 26.6% | 46.6% | 6.6% | 20% | 73.3% | 26.6% |
| አማካይ | በመቶኛ | 28.83% | 48.87% | 14.4% | 7.77% | 77.73% | 22.17% |

በሠንጠረዥ 4.13 እና 4.14፣ የቀረበው ጥያቄ 2 የሚገልፀው አጭር ልቦለድ ማንበብ ጠቃላት ዕውቀትን ከማሳደግ አንፃር ያለውን ጠቀሜታ/ሚና ተማሪዎች ምላሽ የሚሰጡበት ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግም በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት መልስ የሰጡ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 29 እና በመቶኛ 96.6% ሲሆኑ፤ አልስማማም (2) እና ፈፅሞ አልስማማም (1) ብለው የመለሱ ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 1 እና በመቶኛ 3.3% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.14፣ የቀረበው ጥያቄ 2ን፣ መሰረት በማድረግ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የሰጠው ምላሽ በጣም አስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 28 እና በመቶኛ 93.3% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የመለሱት ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 2 እና በመቶኛ 6.6% ነው፡፡

ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑም ሆነ የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ወቅት አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ዕውቀትን ያሳድጋል የሚለው ፅንሰ ሀሳብ ላይ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

በሰንጠረዥ 4.13 እና 4.14፣ የቀረበው ጥያቄ 12 የሚያመለክተው አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ትርጉም የማብራራት ችሎታን ከማሳደግ አኳያ የሚገልፁበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የተሰጠ ምላሽ የተማሪዎች ብዛት በቁጥር 24 እና በመቶኛ 80% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የመለሱት ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 6 እና በመቶኛ 20% ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4.14፣ የቀረበው የቀረበው ጥያቄ 12ን፣ መሰረት በማድረግ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የሰጠው ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የመለሱት ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 20 እና በመቶኛ 66.6% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት የመለሱት ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 10 እና በመቶኛ 33.3% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.14 ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው በጥያቄ ቁጥር 12 ላይ የቀረበው ፅንሰ ሀሳብ ላይ የቁጥጥር ቡድኑ ከሙከራ ቡድኑ የተሻለ ግንዛቤ እንዳለው ያመለክታል፡፡ ይሄውም የቁጥጥር ቡድኑ በቁጥር 4 እና በመቶኛ 10.4% በመቶ ከሙከራ ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ጊዜ የላቀ መረዳት እንዳለው ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.13 እና 4.14፣ የቀረበው ጥያቄ 20 የሚገልፀው አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ የመስራት ዕውቀታቸው እንዲጎለብት ከማስቻል አንፃር ምላሽ የሚሰጡበት ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግም በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት መልስ

የሰጡት ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 20 እና በመቶኛ 66.6% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የመለሱት ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 10 እና በመቶኛ 33.3% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.14 የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር 20ን መሰረት በማድግ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የሰጠው መላሽ በጣምም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 22 እና በመቶኛ 73.3% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት የመለሱት ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 8 እና በመቶኛ 26.6% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.13 እና 4.14 ላይ ጥያቄ ቁጥር 20ን መሰረት በማድረግ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ጊዜ የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው፡፡ ምክንያቱም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ አንፃር የተሰጠ ምላሽ ብዛት በቁጥር 2 እና በመቶኛ 6.6% አብላጫ ማሳየቱ ይህን ያመለክታል፡፡

## ሠንጠረዥ 4.15 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 2 | በቁጥር | 15 | 15 | | - | 30 | - |
| | በመቶኛ | 50% | 50% | - | - | 100% | |
| 12 | በቁጥር | 15 | 10 | 4 | 1 | 25 | 5 |
| | በመቶኛ | 50% | 33.3% | 13.3% | 3.3% | 83.3% | 16.6% |
| 20 | በቁጥር | 9 | 11 | 6 | 4 | 20 | 10 |
| | በመቶኛ | 30% | 36.6% | 20% | 13.3% | 66.6% | 33.3% |
| አማካይ | በመቶኛ | 43.33% | 39.97% | 11.1% | 5.53% | 83.3% | 16.63% |

**ሠንጠረዥ 4.16 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ መልስ በቁጥርና በመቶኛ**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 2 | በቁጥር | 14 | 16 | - | - | 30 | - |
| | በመቶኛ | 46.6% | 53.3% | | - | 100% | - |
| 12 | በቁጥር | 13 | 10 | 6 | 1 | 27 | 3 |
| | በመቶኛ | 16.6% | 50% | 30% | 3.3% | 90% | 10% |
| 20 | በቁጥር | 15 | 7 | 6 | 2 | 22 | 8 |
| | በመቶኛ | 50% | 23.3% | 20% | 6.6% | 73.3% | 26.6% |
| አማካይ | በመቶኛ | 37.73% | 42.2% | 16.67% | 3.3% | 87.78% | 12.2% |

በሠንጠረዥ 4.15 እና 4.16 ፣ የቀረበው ጥቄ 2 አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ዕውቀትን ከማጎልበት አንፃር ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት ተማሪዎች የሰጡት መልስ ብዛት በቁጥር 30 እና በመቶኛ 100% ሲሆን፣ አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት ደግሞ በቁጥር ምንም የለም፡፡ ይህን ውጤት በቅድመ ልምምድ ወቅት ከተሰጠው ምላሽ ጋር ስናነፃፅረው በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ጊዜ የተሰጠው መልስ ለጥያቄ ቁጥር 2፣ በቁጥር 28 እና በመቶኛ ደግሞ 93.3% ነው፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ጊዜ ለጥያቄ ቁጥር 2 የሰጠው መልስን ስንመለከት በጣምም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የገለፁት ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 29 እና በመቶኛ 96.6% ነው፡፡ ይሄም የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ጊዜ የሰጠው መልስ ከቅድመ ልምምድ ጊዜ በመቶኛ 6.6% እና ከቁጥጥር ቡድኑ ከቅድመ ልምምድ ጊዜ ደግሞ በመቶኛ 3.3% ብልጫ ማሳየቱን ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ወቅት አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ዕውቀት የማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው ተማሪዎች የተሻለ መረዳት እንዳገኙ ያመለክታል፡፡

በሠንጠረዥ 4.16፣ በጥያቄ ቁጥር 12 የቀረበውን ስንመለከት አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ትርጉም የማብራራት ችሎታን ሊያሳድግ ይችላል ለሚለው ሃሳብ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽየሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ የሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) የተማሪ ብዛት በቁጥር 27 እና በመቶኛ 90% ነው፡፡ በሌላበኩል ደግሞ የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ልምምድ የሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የተማሪ ብዛት በቁጥር 24 እና በመቶኛ 80% ሲሆን፣ በተጨማሪም የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የሰጠው መልስ በጣምም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የተማሪ ብዛት በቁጥር 20 እና በመቶኛ ደግሞ 66.6% ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ ምላሽ ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ምላሽ በመቶኛ 23.4% አብላጫ ያሳየ ሲሆን፣ ከቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ደግሞ 10% በመቶ ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ ማንበብ የተማሪዎችን የቃላት ትርጉም የማብራራት ችሎታ ሊያሳድግ የችላል ለሚለው ሃሳብ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስቻሉን ያስገነዝበናል፡፡

በሠንጠረዥ 4.16 በጥያቄ ቁጥር 20፣ የተገለፀውን ስንመለከት አጭር ልለድ ማንብብ ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ የመስራት ችሎታቸው እንዲጎለብት የስችላል ለሚለው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህም ጥያቄ የሙከራ ድኑ በድህረ ልምምድ የሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 22 እና በመቶኛ 73.3% ሲሆን፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት ደግሞ በቁጥር 8 እና በመቶኛ 26.6% ነው፡፡ ይሄ ውጤትም ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፤ ነገር ግን ከቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ምላሽ አንፃር ሲታይ በቁጥር 2 እና በመቶኛ 6.6% የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የተማሪዎች መልስ ብልጫ ያሳል፡፡

ከላይ ከቀረበው አስረጅ መረዳት የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ጊዜ ያገኘው ትምህርት አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ የመስራት ችሎታ እንዲጎለብት ያስችላል ለሚለው ሃሳብ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘታቸውን ያሳየናል፡፡

**ክፍል ሶስት ውስጥ የሚገኙ ጥያቄዎች**

3. አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ስራዎችን አንብቦ የማድነቅ ዕውቀትን ሊያዳብር የችላል::

8.አጭር ልቦለድ ማንበብ ግላዊ የራስ መተማመንን ይጨምራል::

.9. አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ ዐውድን ይፈጥራል::

**ሠንጠረዥ 4.17 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 3 | በቁጥር | 2 | 13 | 11 | 4 | 15 | 15 |
| | በመቶኛ | 6.6% | 43.3% | 36.6% | 13.3 | 50% | 50% |
| 8 | በቁጥር | 9 | 13 | 4 | 4 | 22 | 8 |
| | በመቶኛ | 30% | 43.3% | 13.3% | 13.3% | 73.3% | 26.6% |
| 9 | በቁጥር | 5 | 11 | 12 | 2 | 16 | 14 |
| | በመቶኛ | 16.6% | 36.6% | 40% | 6.6% | 53.3% | 46.6% |
| አማካይ | በመቶኛ | 17.73% | 41.07% | 29.97% | 11.07% | 58.87% | 41.07% |

**ሠንጠረዥ 4.18 የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ**

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 3 | በቁጥር | 3 | 17 | 9 | 1 | 20 | 10 |
| | በመቶኛ | 10% | 56.6% | 30% | 3.3% | 66.6% | 33.3% |
| 8 | በቁጥር | 8 | 9 | 13 | - | 17 | 13 |
| | በመቶኛ | 26.6% | 30% | 43.3% | - | 56.6% | 43.3% |
| 9 | በቁጥር | 4 | 14 | 9 | 3 | 18 | 12 |
| | በመቶኛ | 13.3% | 46.6% | 30% | 10% | 60% | 40% |
| አማካይ | በመቶኛ | 16.63% | 44.4% | 34.43% | 4.43% | 61.07% | 38.87% |

በሠንጠረዥ 4.17 እና 4.18 የቀረበው ጥያቄ 3፣ የያዘው ሃሳብ አጭር ልቦለድ ማንበብ

የፈጠር ስራዎችን አንብቦ የማድነቅ ዕውቀትን ከማሳደግ አንፃር ያለውን ሚና ተማሪዎች የሚገልፁበት ነው፡፡ ይንን መሰረት በማድረግ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት የመለሱ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር 15 እና በመቶኛ 50% ሲሆኑ፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም ብለው የመለሱ ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር 15 እና በመቶኛ 50% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.18 ለጥያቄ ቁጥር 3፣ ለቀረበው ጥያቄ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ወቅት የሰጠው ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 20 እና በመቶኛ 66.6% ሲሆን፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልስ የሰጡ ደግሞ በቁጥር 10 እና በመቶኛ 33.3% ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው መግለጫ መረዳት የሚቻለው የሙከራ ቡድኑም ሆኑ የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ስራዎችን አንብቦ የማድነቅ ዕውቀትን ያሳድጋል የሚለው ሃሳብ ላይ ግንዛቤ እንዳላቸው የሚያመለክት መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ መላሾች በቁጥር 5 እና በመቶኛ ደግሞ 16.6% ብልጫ እንዳለው ያመለክታል፡፡ ይሄ ደግሞ የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ጊዜ ከቁጥጥር ቡድኑ በተራ ቁጥር 3፣ ለቀረበው ጥያቄ የተሻለ ግንዛቤ እንዳለው ያስረዳል፡፡

ሠንጠረዥ 4.17 እና 4.18 መሰረት በማድረግ የቀረበውን ጥያቄ 8፣ ስንመለከት አጭር ልቦለድ ማንበብ ግላዊ የራስ መተማማንን ከማሳደግ አንፃር ያለውን አስተዋፅኦ/ጠቀሜታ ምላሽ የሚሰጡበት ነው፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግም በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት ተማሪዎች የሰጡት መልስ ብዛት በቁጥር 22 እና በመቶኛ 73.3% ሲሆን፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት መልስ የሰጡት ደግሞ በቁጥር 8 እና በመቶኛ 26.6% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.18 በጥያቄ ቁጥር 8፣ ለቀረበው ጥያቄ የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ወቅት የሰጠው መልስ ደግሞ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 17 እና በመቶኛ 56.6% ሲሆን፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት የመለሱት ደግሞ በቁጥር 13 እና በመቶኛ 23.3% ነው፡፡

ከዚህ ገለፃ መገንዘብ የሚቻለው በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ ማንበብ ግላዊ የራስ መተማማንን ለማሳደግ ጥቅም እንዳለው ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ቢሆንም፤ የቁጥጥር ቡድኑ ከሙከራ ቡድኑ የተሻለ መረዳት እንዳለው ነው መረጃው የሚያመለክተው፡፡

ሠንጠረዥ 4.17 እና 4.18 ላይ የቀረበው ጥያቄ 9፣ የሚያመለክተው አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ ዐውድን ከመፍጠር አኳያ ያለውን ሚና የሚገልፁበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ ምላሽ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት ተማሪዎች የሰጡት መልስ ብዛት በቁጥር 16 እና በመቶኛ 53.3% ሲሆን፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት የመለሱት ደግሞ በቁጥር 14 እና በመቶኛ 46.6% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.18 በጥያቄ 9፣ለቀረበው ጥያቄ የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ልምምድ ወቅት የሰጡት መልስ ደግሞ በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 18 እና በመቶኛ 60% ሲሆን ፣አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት ደግሞ የሰጡት መልስ በቁጥር 12 እና በመቶኛ 40% ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4.17 እና 4.18 ጥያቄ ቁጥር 9 መሰረት በማድረግ ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ ዐውድን ከመፍጠር አኳያ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ግንዛቤ እንዳለው ማመልከቱን ነው፡፡ ምክንያቱም የሙከራ ቡድኑ በቁጥር 2 እና በመቶኛ ደግሞ 6.6% ብልጫ ከቁጥጥር ቡድኑ እንዳለው መረጃው ያሳያል፡፡

## ሠንጠረዥ 4.19 የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 3 | በቁጥር | 2 | 14 | 10 | 4 | 16 | 14 |
| | በመቶኛ | 6.6% | 46.6% | 33.3% | 13.3% | 53.3% | 46.6% |
| 8 | በቁጥር | 9 | 11 | 5 | 5 | 20 | 10 |
| | በመቶኛ | 30% | 36.6% | 16.6% | 16.6% | 66.6% | 33.3% |
| 9 | በቁጥር | 3 | 14 | 12 | 4 | 17 | 13 |
| | በመቶኛ | 10% | 46.6% | 40% | 3.3% | 56.6% | 43.3% |
| አማካይ | በመቶኛ | 15.53% | 43.27% | 29.97% | 11.07% | 58.83% | 41.07% |

## ሠንጠረዥ 4.20 የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የፅሁፍ መጠይቅ በቁጥርና በመቶኛ

| የጥያቄ ተ/ቁ | የተማሪ መልስ | አማራጮች | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | 4እና3 | 2እና1 |
| 3 | በቁጥር | 7 | 18 | 2 | 3 | 25 | 5 |
| | በመቶኛ | 23.3% | 60% | 6.6% | 10% | 83.3% | 16.6% |
| 8 | በቁጥር | 11 | 12 | 5 | 2 | 23 | 7 |
| | በመቶኛ | 36.6% | 40% | 16.6% | 3.3 | 76.6% | 23.3% |
| 9 | በቁጥር | 10 | 11 | 7 | 2 | 21 | 9 |
| | በመቶኛ | 33.3% | 36.6% | 16.6% | 3.3% | 70% | 30% |
| አማካይ | በመቶኛ | 31.07% | 45.53% | 13.27% | 5.53% | 76.63% | 23.3% |

ከሠንጠረዥ 4.19 እና 4.20 ላይ የቀረበው ጥያቄ 3፣ አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ስራዎችን አንብቦ የማድነቅ ችሎታን ከማሳደግ አንፃር ያለውን ጥቅም ተማሪዎች የሚገልፁበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ጊዜ ተማሪዎች የሰጡትን መልስ ስንመለከት በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በማለት በቁጥር 25 እና በመቶኛ 83.3% ሲሆን፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በማለት ደግሞ

የተሰጠ መልስ በቁጥር 5 እና በመቶኛ 16.6% ነው፡፡ በቀረበው መረጃ መሰረት የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ ምላሽ ከቁጥጥር ቡድኑና ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የተሰጠ መልስ በቅደም ተከተል ስንመለከት የተማሪ ብዛት በቁጥር 15 እና በመቶኛ 50% የቁጥጥር ቡድኑ እና በቁጥር 20 እና በመቶኛ 66.6% የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ልምምድ ተማሪዎች የሰጡት መልስ ነው፡፡ በተጨማሪም የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ልምምድ ወቅት ተማሪዎች የሰጡት መልስ ብዛት በቁጥር 16 እና በመቶኛ 53.3% ነው፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ 4.19 እና 4.20 የቀረበውን ጥያቄ 3፣ መሰረት በማድረግ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው በሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ የተሰጠው መልስ በቅድመ ልምምድ በሁለቱም ምድቦች ከተሰጠው ምላሽና በድህረ ልምምድ ከቁጥጥር ቡድኑ ከተሰጠው መልስ በቁጥርም ሆነ በመቶኛ ብልጫ እንዳለው ያመለክታል፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች በድህረ ልምምድ ጊዜ አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ስራዎችን አንብቦ የማድነቅ ችሎታን እንደሚያጎለብት ግንዛቤ ማግኘታቸውን ያሳየናል፡፡

በሠንጠረዥ 4.19 እና 4.20 የቀረበው ጥያቄ 8፣ አጭር ልቦለድ ማንበብ ግላዊ የራስ መተማማንን ከማሳደግ አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ተማሪዎች መልስ የሚሰጡበት ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ ወቅት ተማሪዎች የሰጡት መልስን ስንመለከት በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት የመለሱ በቁጥር 23 እና በመቶኛ 76.6% ሲሆን አልስማማም(2) እና ፈፅሞ አልስማማም(1) በማለት ደግሞ የተሰጠ መልስ በቁጥር 7 እና በመቶኛ 23.3% ነው፡፡

በሌላ በኩል በሠንጠረዥ 4.17 እና 4.18 ጥያቄ 8ን መሰረት አድርጎ ለቀረበው ጥያቄ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 22 እና በመቶኛ 73.3%፣ እንዲሁም በሠንጠረዥ 4.19 ደግሞ የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ልምምድ ወቅት የሰጠው ምላሽ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 20 እና በመቶኛ 66.6% ሲሆን፣ በሠንጠረዥ 4.18 ለጥያቄ 8 የሙከራ ቡድኑ ቅድድ ልምምድ የሰጠው መልስ ደግሞ በጣም እስማማለሁ(4) እና እስማማለሁ(3) በማለት በቁጥር 18 እና በመቶኛ 60% ነው፡፡

በዚህም መረጃ መሰረት የሙከራ ቡድኑ በድህረ ልምምድ የሰጠው መልስ በቅደም

| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | ድምር |
| 01 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 61 |
| 02 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 4 | 59 |
| 03 | 4 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 1 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 52 |
| 04 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 58 |
| 05 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 65 |
| 06 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 57 |
| 07 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 62 |
| 08 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 63 |
| 09 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 68 |
| 10 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 2 | 60 |
| 11 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 57 |
| 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 57 |
| 13 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 75 |
| 14 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 65 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 65 |
| 16 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 75 |
| 17 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 60 |
| 18 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 67 |
| 19 | 4 | 1 | 1 | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 56 |
| 20 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 2 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 1 | 53 |
| 21 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 57 |
| 22 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 75 |
| 23 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 71 |
| 24 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 47 |
| 25 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 72 |
| 26 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 71 |
| 27 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 48 |
| 28 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 59 |
| 29 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 62 |
| 30 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 68 |

ገላጭ እስታትስቲክ

| | የተማሪዎች ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ | 30 | 47 | **75** | 62.1667 | 70.59802 |

Descriptive Statistics

| | N | Minimum | Maximum | Mean | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|---|
| exgpotqu | 30 | 47.00 | 75.00 | 62.1667 | 7.59802 |
| Valid N (listwise) | 30 | | | | |

## በአዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ 02 አፈሪካ አንድነት ቁጥር-2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም 7ኛ ክፍል እየተማሩ ባሉ ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ ዋና ዓላማ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ(አንብቦ መረዳት) ለማሻሻል ያለውን አስተዋፅኦ ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው፡፡

**መመሪያ**፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ከቀረቡት አማራጮች አንዱን መርጣችሁ በስሩ የ(×)ምልክት በማስቀመጥ መልስ ስጡ፡፡

በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

በጣም እስማማለሁ= 4 እስማማለሁ= 3 አልስማማም= 2 እና ፈፅሞ አልስማማም= 1

የተማሪው ክፍል ________ ጾታ ________ ፡ቡድን ______

| | ጥያቄ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | አጭር ልቦለድ የማንበብ ተነሳሽነት እንዲጎለብት ያስችላል፡፡ | | | | |
| 2 | አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላት ዕውቀትን ያሳድጋል፡፡ | | | | |
| 3 | አጭር ልቦለድ ማንበብ የፈጠራ ስራዎችን አንብቦ የማድነቅ ዕውቀትን ሊያዳብር ይችላል፡፡ | | | | |
| 4 | አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመገንዘብ አቅማቸው እንዲጎለብት ያስችላል፡፡ | | | | |
| 5 | አጭር ልቦለድ ቀጣይነት ያለው የአንባቢነት የህይወት ልምድ እንዲኖረን ያስችላል፡፡ | | | | |
| 6 | አጭር ልቦለድ ማንበብ በተማሪዎች መካከል የንባብ ፉክክር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 7 | በአጭር ልቦለድ መማር የአንብቦ መረዳት ክሂልን ያዳብራል፡፡ | | | | |
| 8 | አጭር ልቦለድ ማንበብ ግለዊ የራስ መተማመንን ይጨምራል፡፡ | | | | |
| 9 | አጭር ልቦለድ ለቋንቋ መማር ሂደት እውነተኛ ዐውድን ይፈጥራል፡፡ | | | | |
| 10 | በአጭር ልቦለድ መማር ንቁ ተሳታፊ እንድንሆን ያስችላል፡፡ | | | | |
| 11 | አጭር ልቦለድ ማንበብ አቀላጥፎ የማንበብ ችሎታን ያጎለብታል፡፡ | | | | |
| 12 | አጭር ልቦለድ ማንበብ የቃላትን ትርጉም የማብራራት ችሎታን ሊያሳድግ ይችላል፡፡ | | | | |
| 13 | አጭር ልቦለድ ተማሪዎች ስለሌሎች ባህል እንዲያውቁ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ | | | | |
| 14 | አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የምንባቡን የሀሳብ ፍሰት ጠብቀው የመረዳት አቅማቸው እንዲጎለብት ያስችላል፡፡ | | | | |
| 15 | አጭር ልቦለድ ማንበብ የመገመትና የመተንበይ አቅምን ይጨምራል፡፡ | | | | |
| 16 | አጭር ልቦለድ ማንበብ በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመግለፅ አቅምን ያዳብራል፡፡ | | | | |
| 17 | አጭር ልቦለድ ማንበብ የቡድን ተሳትፎን ያሳድጋል፡፡ | | | | |
| 18 | አጭር ልቦለድ የቋንቋ መማር ሂደትን ሳቢና ማራኪ ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 19 | አጭር ልቦለድ ማንበብ የማዳመጥ ክሂልን ያዳብራል፡፡ | | | | |
| 20 | አጭር ልቦለድ ማንበብ ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ የመስራት ዕውቀታቸው እንዲጎለብት ያስችላል፡፡ | | | | |

## አባሪ ሰባት፡- የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት የተዘጋጀ የትምህርት ይዘት

### የማስተማሪያ መፅሐፍ (ቴክስት)

የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጀ ፅሑፍ፡፡ ይህ ፅሑፍ የሙከራ ቡድኑን አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር የማንበብ ክሂልን ማሳደግ ላይ ያለውን አስተዋፅኦ/ሚና ለመመርመር የተዘጋጁ የማስተማሪያ ፅሁፎችን የያዘ ነው፡፡ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ከሚያዝያእስከ ግንቦትለአንድ ወር በሳምንት ሶስት ክፍለ ጊዜ ቅድመ ልምምድ ፈተና እና ድህረ ልምምድ ፈተናን ሳይጨምር ተሰጥቷል፡፡

### ትምህርት አንድ

### የትምርቱ ርዕስ፦ ክፍተት

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- የቅድመ ምንባብ እና የድህረ ምንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤
- የምንባቡን ሃሳብ አሳጥረው ይገልፃሉ፤
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ምክንያቱን ያብራራሉ፤
- ልዩልዩ የቃላት ፍቺ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤

### ክፍል አንድ፡- የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**ሀ.** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ርዕሱን አይታችሁ ምንባቡ ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. ክፍተት በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?
3. ክፍተት የሚለውን ቃል ታውቃላችሁ? ምን ማለት ይመስላችኋል?
4. ክፍተት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ምን አይነት ተፅኖ የሚፈጥር ይመስላችኋል?

**ለ.** ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ ፍቻቸውን በቃል ግለፁ፡፡

. ገርበብ . ብቅ . ጥላት

**ክፍተት**

ኳኳ…ኳኳ…ኳኳኳኳ፡፡

ያንኳኳው ሰው ገርበብ ያለውን በር ገፋ አድርጎት ወደ ውስጥ ዘለቀ፡፡ እትዬ ሻሾ ነበሩ፡፡

"ደህና አምሽተዋል?" አለች አራሷ ዘርፌ፣ ከመጋረጃው ራሷን ብቅ አድርጋ፡፡ በደብዛዛ ብርሃን ውስጥ እንደ ጥላት ትታያለች፡፡ ከእሷ ፊንጠር ብሎ አባወራው ተቀምጧል፣ እግሮቹን አነባብሮ፡፡

ቀዝቀዝ ያለ ቤት ነው፡፡ ግድግዳው ላይ የተለጠፉት የህፃናት ምስሎች ጎልተው ዐይን ውስጥ ይገባሉ፡፡ ክፍሏ ጠበብ ትላለች፡፡ ሳሎኑ ውስጥ የሚታዩት ቁሳቁሶች፣ ወንበርና ጠረጴዛዎች ባለቤቶቹ በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ እንደሚገኙ ያሳብቃሉ፡፡

ረዘም ካለ ለሰላምታ ልውውጥ በኋላ እትዬ ሻሾ የቤቱን ብርሃን ለመዱት፡፡ ቀጭን ናቸው፣ እትዬ ሻሾ፡፡ አዳፋ ነጠላ መልበስ የሚያዘወትሩ ረዥም አሮጊት፡፡

"ቁጭ ይበሉዋ እትዬ፡፡ ምነው ቆመው ቀሩሳ?!"

"ኧረ ተይኝ አንቺዬ! ምኑን ቁጭ አልኩት? ላንድአፍታ ደረስ ብዬ ልመለስ እንጂ ልቀመጥ መች መጣሁ?! " ሊናገሩት ያሰቡትን ከየትኛው ጫፍ እንደሚጀምሩት ሲያሰላስሉ ቆዩና፤ "ሆሆይ! እንዴት ያለ ጉድ ይታያል እናንተዬ?! በየቀኑ በጓዳችን ተፈልፍሎ የሚወጣው ጉድ እንዴት ለቁጥር ይበዛል?!..." አሉ፡፡

"ምነው?" አለ አባወራው፡፡

አራሷም "ምን ችግር ገጠሞት እተዬ?!" አለች፡፡

"ኧረ ለጆሮ የሚቀፍ ነው፡፡ ሰራተኞቻችንን ለምን አንቆጣጠርም? እርቃናችንን እስኪያስቀሩን ድረስ ነው እንዴ የምንጠብቀው? እርስ በእርሳችን ካልተጠባበቅን ምኑን ተረፍነው? እንዲህ ስክለፈለፍ የመጣሁትኮ…"

"ለምንድነው?" አለ አባወራው፤ ነገራቸውን እንዲያሳጥሩት በሚያዝዝ ቁጡ ድምፅ፡፡

"ቤታችንን አራቁተው ለድህነት የሚድሩን እነሱ አይደሉም እንዴ?! ገበናችንንና

ምስጢራችንን ከበረበሩ በኋላ ለሃሜት ሱሰኞች አሳልፈው የሚሰጡብንስ እነማን ሆነው?!"

ዘርፌ ንዴቷ መጣ፡፡ "ምን እንደተፈጠረ ለምን አሳጥረው አይነግሩንም? የምን ነገር ማስረዘም ነው?"

"አንቺማ ምኑን ታውቂው? የማሪያም አራስ! መንደርተኛው ሁሉ የሚፈተፍተው ስለማን መስሎሻል? ስላንቺው ጉድ እንጂ! ያው የኔ ነገር ታውቂዋለሽ፡፡ ጎረቤት ሲጠቃ አልወድም፡፡ ያየሁትንና የሰማሁትን ልንገርሽ ብዬ ነው አመጣጤ" አሉ እትዬ ሻሾ፡፡

"ምኑን ነው የሚነግሯት?"

"እርግቢቷ አስቤዛዋን በጭልፊት እያስመነተፈች ነው ይሉሻል"

"እርግብ?" አለች አራሷ፡፡

አባወራው ደግሞ "ጭልፊት?"

"ታዲያስ፣ ቤታችሁኮ ተራቁቷል፡፡ እስክትሸጣችሁ ድረስ ነው እንዴ የምትጠብቋት?... አንቺማ ከአስራ አምስት ቀን ወዲህ ጓዳሽን መች አየሽውና? እጠቅማትና እፀድቅባት ብለሽ ያሳደርሻት ሰራተኛ ተብዬ፣ ከንብረትሽ ከፍላና ካስቤዛሽ ቀንሳ ወዲያኛው ቀበሌ ላሉ ነዋሪዎች ስትቸረችር ስንቶቻችን መሰለሽ የደረስንባት?... "

አራስ ደነገጠች፡፡

ምን ማድረግ እንደሚገባት ግራ ገባት፡፡ ባለቤቷን አነበበችው፡፡ ሰፊ በሆነው የፊቱ ሰሌዳ ላይ የቁጣ ቃላት ተፅፈውበታል፡፡

"እንዴት ልመንዎት?" አለ አባወራው፡፡

ፈንጠር ቆንጠር አሉ እትዬ ሻሾ፡፡ "አትመነኝ! ጉዳዬ መስሎሃል? ደግሞ በምን ልመንዎት ብሎ አማርኛ?! ከመሬት ተነስቼ የምዘባርቅ መስሎሃል? ምን ይተርፈኝ በዬ ነው፣ ሁለት ጠጉር ካበቀልኩ በኋላ እመቤቲቱን ከገረድ የማጣላው… 'በምን ልመንዎት' ነው ያልከኝ?!"

“የሚሉትን ሰምተሻል?” አለ አባወራው የትኩረት ነጥቡን ወደ ባለቤቱ ልኮ

ዘርፌ ዝምታዋን እንደተከናነበች ስለ ትዳሯ ማሰላሰል ያዘች፡፡ ማትሪክ አልሆንልሽ ባላት ሰሞን ነው፤ የዛሬ የተዳር አጋሯን የተወዳጀችው፡፡ ጎረቤታቸው በሚገኘው ሰፌና ዘመናዊ ግቢ ውስጥ ተከራይቶ ይኖር ነበር፡፡ … እንደሚፈልጋት እየታወቃት መጣ፡፡

ተሽነፈችለት፡፡ ውለታ ውሎላቸው ነበርና እናቷ በልጃቸው መሸነፍ ተደሰቱ፡፡ “ቀደመኝ እንጂ፣ ለጄን አትወስድልኝም ወይ? ልለው ምንም አልቀረኝ ነበር” አሉ ተባለ፡፡ “ነፍሴ የተረፈችው በእሱ ደጋፊነት ነው እንጂ እኔ ቤት ንብረቴን ብሸጥ እንኳን ከያዘኝ ብርድ በሽታ መች እድን ነበር? ሲሉ ሰማሁዋቸው” የሚል በዛ፡፡

ዘርፌን እንዳቅሚቱ ደግሰው ዳርዋት፡፡

… ሆዷ መግፋት ያዘ፡፡ ዘጠኝ ወር እስኪሞላው ድረስ አጠገቡ እያለች ናፍቆት እንቅልፍ ነሳው፡፡ እንክብካቤ አበዛባት፡፡ ጥያቄዎቿን አሟላላት፡፡ ወሬያቸው ሁሉ በቅርቡ ስለሚያስተናግዱት አዲሱ እንግዳ ሆነ፡፡ ቀኑ እስኪደርስ ተቻኮሉ፡፡ ከልክ ያለፈ የመሰላት የባለቤቷ ደስታ ነፍሷን በሃሴት ወይን አሰከረው፡፡

አዲሱ “እንግዳ” መጣ፡፡ በቤታቸው ታላቅ የምስራች ሆነ፡፡ በዓልም ተደረገ፡፡ ውሎ ሲያድር ግን ልጇ ከሆዷ ሲወጣ አንድ ነገር አየች፡፡ በሷን አጣችው፡፡ አጠገቧ እያለ መንፈሱ ራቃት፡፡ ድምፁ ከበዳት፡፡ አጣችው፡፡ የእሷ የነበረ እንጂ አሁን የእሷ የሆነ አልመስልሽ አላት፡፡

እንዲወለድ የናፈቀችው ልጅ ባለቤቷ ይሰጣት የነበረውን ፍቅር ሰረቀባት፡፡ ቆይቶ ለ“ዘር” ተብሎ እንጂ ፍቅር ገዝቶት እንዳላገባት ገባት፡፡ ብቻ መሰላት፡፡ ለብዙ ጊዜ ጠበቀችው… ጠበቀችው፡፡ እንደነበረው ሊሆን አልቻለም፡፡

የሚያስፈልጋትን ነገር ስትጠይቀው የብስጭቱ መንስኤ ይሆን ጀመር፡፡ በቁጣ ይገረምማታል፤ ይደነፋባታልመ፤ህፃኑ ግን አልባሳት በዙለት፡፡ አሻንጉሊቶች በዙለት፡፡ ብዙ ነገሮች በዙለት፡፡

ዘርፌ ከፋት፡፡ መጠቃት አንደበቷን ቆለፈው፡፡ ካልጠየቋት የማትመልስ ሆነች፡፡ ብትመልስም መልሶቿ አጫጭር ሆኑ፡፡ ውስጧም እንደውጪ ተለወጠ፡፡ ልጇ ከባለቤቷ ጋር የሚያቀራርብ ድልድይ አልሆነላትም፡፡ ድልድዩን ሰብሮ ክፍተት የሚያበጅ እንጂ!

. እስካሁን ከቀረበው የአጭር ልቦለድ ታሪክ ምን ተረዳችሁ?
. የዚህ አጭር ልቦለድ ታሪክ መጨረሻው ምን የሚሆን ይመስላችኋል?
. ወ/ሮ ሻሾ የመጡበት ጉዳይ ምንድን ነው? በጥንድ ተወያይታችሁ በቃል ግለፁ!
. ዘርፌ ብዙ ጊዜ የጠበቀችው ማንን ነው? ለምን?

ይህን ሁሉ የምታጫውተው ወዳጅ ስላልነበራት ከሰራተኛዋ ጋር ነበር ወግ የምትሰልቀው፡፡

"… ሞቅ ብሎት በመጣ ቁጥር የምናምንቴዎችን ያህል እንኳን ክብር ሳይጠኝ ይተኛኝ ነበርና ሁለተኛ ልጄን ወለድኩለት" ትልና ለተነጫናጭ ልጇ ጡቷን ታጎርሰዋለች፡፡

ህፃኑ ሃያ ቀን አልሞላውም፤ የማህፀኗን በር ሾልኮ ከወጣ፡፡ "ምናለ ውሃ ሆነህ በቀረህ?" ትለዋለች፣ አንዳንዴ ምሬቷ ሲከፋ፡፡ "ይሄኔ አንተም እንደ አባትህ ለሚስትህ የማትመች ትሆን ይሆናል" ትላለች፣ ስለ አራስ ልጇ ስታስብ፡፡ ረዘም ላለ ሰዓት ስለጎጆዋ ስታሰላስል ራሷን ስለሚያማት "ተነሺ!" ትላታለች፣ ሰራተኛዋን፡፡ "ተነሺ! አብሲቱን ጣይው፡፡ ድስትም ትጥጂለሽ፡፡ ዘይት ባይኖርሽም ምንም አይደል፤ የዘይቱን ዕቃ አዘቅዝቀሽ ለድስቱ ካሳየሽው በቂ ነው፡፡ ደግሞ ለሽሮ! …" ትላትና ከአጠገቧ ታርቃታለች፡፡ ሰራተኛ ብቻ ሳትሆን ጓደኛም ጭምር ናት፡፡ አሁን ደግሞ ተከሳሽ! …

አባወራው እትዬ ሻሾ የሚሉትን በንዴት አዳምጦ ሲጨርስ እየተጣደፈ ወደ ጓዳ ገባ፡፡ ልብስ በማጠብ ላይ የነበረችውን ሰራተኛ አበሻቅጦ ጠራት፡፡ ሰራተኛዋ በእያንዳንዱ የሰውነቷ ክፍል ላይ ጉስቁልና ማህተሙን ያሳረፈባት አይነት ሴት ናት፡፡

በጥያቄ እያዋከበ፣ ከግድግዳው ጋር እያላጋ፣ ስቃይዋን ሲያበዛው ዘርፌ ከንፈሯን እየነከሰች ነበር፣ በኃይል! የመቀርጠፍን ያህል፡፡ "አምልጠሽ ውጪ ውጪ" አሰኛት፡፡ "ወጥተሽ ሩጪ-ሩጪ" አሰኛት፡፡

እትዬ ሻሾ ፊታቸውን አፍክተው በሰራተኛዋ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ቅጣት ይከታተላሉ፡፡ ጥፋቷን ስታስተባብል ባለመስማታቸው ተገርመዋል፡፡ በርግጥ የጥፋተኝነት ስሜት ጎልቶ እየተነበበባት ጥጓን ይዛ አቀርቅራለች፡፡

አባወራው “የበላሽበትን ወጭት የምትሰብሪ!” ሲላት፤ “እንዴት ገንዘቤን ከስክሼ ያመጣሁት በርበሬ ሱቅ ወስደሽ ትሽጪያለሽ?” ሲላት

እሷ ግን ዝም፡፡

እጁ እስኪዝል የቦክሱን አቅም አሳይቷታል፡፡ “ኧረ በእጅህ ሰበብ ሆና ጉድ እንዳታፈላብህ!” አሉና እትዬ ሻሾ አስጠነቀቁ፡፡

ዘርፌ የሌለች ያህል ሆናለች፡፡ ፀጥታ! አባወራው ግን ቁጣውን ቀጥሏል፡፡

“ከየት የማመጣው መስሎሽ ነው? ከአባትሽ ማሳ የዘረፍኩት? ወይስ ከአልፎ አግዳሚ የቀማሁት? ተናገሪ እንጂ! ምን ይዘጋሻል? ምን ያህል ብትንቂኝ ነው፤ንብረቴን እብድ የዘገነው በሶ ያስመሰልሽው?!” ርግጫውን ዳሌዋ ላይመረገው፡፡ “ኧረ ይብቃ አንተዬ!”

እጁን ያዝ አደረጉት እትዬ ሻሾ፡፡ “ሴት ልጅ እንዲህ አትመታም፡፡ እንዲህ?! አትመታም፡፡ ቦታ ይመረጣል!” አሉት፡፡

“የትም ተግማምተሽ ከምትቀሪ ብለን፣ ዱርዬ ጨፍሮብሽ ዲቃላ ከምትታቀፊ ብለን፣ ከመከራ ስንታደግሽ የሰፈርተኞቻችን መዘባበቻ ታረጊን?! … ስናዝንልሽ ትነክሺን!? ዳይ! ካሁን ደቂቃ ጀምሮ አንቺን ማየት አልፈልግም፡፡ ደሞ ሰበብ ሆነሽብኝ እስር ቤት ገለመሌ እያልኩ ካንቺ ጋር የምንከረፈፍበት ጊዜ የለኝም፡፡ … ኮተት ቅራቅንቦሽን ይዘሽ ውጪልኝ-ይይ!” እየተፈናጠረ ወጣ፡፡ቆይቶ የእትዬ ሻሾ ድምፅ ተደመጠ፡፡ “እኔ ምልሽ ዘርፌ! ታውቂ ነበር እንዴ ጉዱን?!” አሷት፤ ላደረጉት ጎረቤታዊ አስተዋፅኦ ከፍ ያለ የምስጋና ቃላት ስላልተቸራቸው ቅር ተሰኝተው፡፡

ዘርፌ አንዳች ነገር ልትናገር ስትል ሰራተኛዋ ጣልቃ ገብታ አቋረጠቻት፡፡ “ኧረ እትዬ አደብ ይግዙ፤ ሰው ጆሮ የሚገባም አይደል” አለች “ዝምታ ማንን ገደለ እትዬ?”

ዘርፌ ግን “እኔ ነኝ” አለች፡፡እትዬ

ሻሾም “አንቺ ምን?” ብለው ጠየቋት፡፡

“ባለቤቴ ለአብራኩ ክፋይ እንጂ ለእኔ ግድ የለውም፡፡ ትቶኛል፡፡ ረስቶኛል፡፡ እና እኔ ነኝ ለራሴ ሴት የሚያስፈልጋትን እንድታቀርብልኝ በርበሬውንም ዱቄቱንም ሽጠሽ ነይ የምላት፡፡ ሽጣ ባመጣችው ገንዘብ ነው የምፈልገውን የማስገዛት፡፡ እኔው ነበርኩ!” አለች

እንባዋ መጥቶ፡፡

“ውይ” አሉ እትዬ ሻሾ፤ ድንጋጤም ትካዜም እየታየባቸው፡፡ በራሳቸውም ላይ ተረቱ፡፡ “ፀጉሬን አሰራለሁ ብላ ሄዳ ተላጭታ ተመለሰች አሉ!”

(ምንጭ፣ ከጥቁር ሰማይ ስር፤ እንዳለጌታ ከበደ)

**ክፍል ሁለት፡- ደህረ ምንባብ ጥያቄ**

**ተግባር አንድ፡-** <u>**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ “እውነት” ስተት ከሆኑ ደግሞ “ሐሰት” በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በአጭሩ ግለፁ፡፡**</u>

1. ዘርፌ በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ነው የምትኖረው፡፡
2. ረዘም ካለ የሰላምታ ልውውጥ በኋላ ነው እትዬ ሻሾ የቤቱን ብርሃን የለመዱት፡፡
3. እትዬ ሻሾ ለዘርፌ ጥሩ ዜና ነበር ይዘው የመጡት፡፡
4. እትዬ ሻሾ የመጡበትን ጉዳይ በአጭሩ ለዘርፌ በመንገራቸው ዘርፌ ደስተኛ ሆነች፡፡
5. ሰራተኛዋ ለዘርፌ ሰራተኛዋ ብቻ ሳትሆን ጓደኛዋም ጭምር ናት፡፡

**ተግባር ሁለት፡-** <u>**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**</u>

1. ዘርፌ በርበሬውን የሸጠችው ለማን ነው?
   ሀ. ለወ/ሮ ሻሾ ለ. ለአባወራው
   ሐ. ለቤተሰቦቿ መ. ሌላ ቀበሌ ላሉ ነዋሪዎች
2. አባወራው ሰራተኛዋን በቁጣ የተናገራት ለምንድነው?
   ሀ.ሌብነቷን ሰምቶ. ለ.ስራ በአግባቡ አለመስራቷን ሰምቶ
   ሐ. ውጭ መዋሏን ሰምቶ መ. ለሚስቱ ባለመታዘዟ
3. እትዬ ሻሾ በዘርፌ ቅር የተሰኙት ለምንድን ነው?
   ሀ. ስለነቀፈቻቸው ለ. ስላላመሰገነቻቸው
   ሐ. ዝም ስላለቻቸው መ. ስለሰደበቻቸው

4. ዘርፌ ለምንድን ነው በርበሬውንም ዱቄቱንም በሰራተኛዋ የምታሸጠው?

ሀ. ዱቄትና በርበሬው ብዙ ስለሆነ

ለ. ለዕፃኑ ወተት ልትገዛበት

ሐ. አራስ ለራሷ የሚያስፈልጋትን ነገር ልታሟላበት

መ. ለሰራተኛዋ ደሞዝ ለመክፈል

5. "ምን ይትረፈኝ ብዬ ነው፤ **ሁለት ጠጉር** ካበቀልኩ በኋላ እመቤቲቱን ከገረድ የማጣላው፡፡" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. ሁለት ፍሬ ፀጉር ብቻ ያላቸው መሆኑን ለ. ያረጁ መሆናቸውን

ሐ. ወሬ ማመላለሳቸውን መ. ዘርፌን መውደዳቸውን

6. በንዴት እየተፈናጠረ የወጣው ማን ነው?

ሀ. ወ/ሮ ሻሾ ለ. አባወራው ሐ. ሰራተኛዋ መ. ዘርፌ

7. ዘርፌ "ቂጭ ይበሉ እትዬ፡፡ ምነው ቆመው ቀሩሳ?!" ያለችው ማንን ነው?

ሀ. ባለቤቷን ለ. ሰራተኛዋን ሐ. ጎረቤቶቿን መ. ወ/ሮ ሻሾን

8. አባወራው ዘርፌን የራቃት ለምንድን ነው?

ሀ. የሚፈልገውን ልጅ ስላገኘ ለ. ስላረጀችበት

ሐ. ስለማትወልድ መ. ገንዘብ ስለምታባክን

9. "እርግቢቷ አስቤዛዋን **በጭልፊቷ** እያስመነተፈች ነው ይሉሻል፡፡" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺ ማንን ይተካል?

ሀ. ሰራተኛዋን ለ. ዘርፌን ሐ. ወ/ሮ ሻሾን መ. አባወራውን

10. የዘርፌ እናት የተደሰቱት ለምንድን ነው?

ሀ. ዘርፌ በማትሪክ ጥሩ ውጤት በማምጣቷ ለ. ዘርፌ በማትሪክ መውደቋ

ሐ. ዘርፌ በባሏ በመሸነፏዋ መ. ዘርፌ በባሏ በለመሸነፏ

11. "በደበዘዘ ብርሃን ውስጥ እንደ **ጥላት** ትታያለች፡፡" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ------------- ነው፡፡

ሀ. ጥላሸት ለ. ጥለት ሐ. ጥላ መ. ጠቁራ

12. "በቁጣ **ይደነፋባታል**" ሲል ምን ለማለት ነው?

ሀ. በኃይል ይሰድባታልለ. ሞልቶ ይገነፍላል

ሐ. ያላትን ሁሉ ደፍቶ ያበላሽባታልመ. ይወዳታል

13. "ንብረቴን ዕብድ **<u>የዘገነው በሶ</u>** ያስመሰልሽው?!" በሚለው ውስጥ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. ምንም ሳይቀር መወሰዱን ለ. አስፈራርታ መውሰዱን

ሐ. በየቦታው እዛም እዚህም መዝራቷን/መሸጧን መ. በጥንቃቄ መሸጧን

14. "የበላሽበትን ወጭት የምትሰብሪ ባለጌ!" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ **<u>ወጭት</u>** የሚለው ቃል ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. ብርጭቆ ለ. ጀበና ሐ. እንስራ መ. ውለታ/ማዕድ

15. "የሰፈርተኞቻችን መዘባበቻ ታረጊን! …" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ **መዘባበቻ** የሚለው ቃልን በፍቺ ሊተካው የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. መቀለጃ ለ. መደራደሪያ ሐ. መፎካከሪያ መ. ባለሞያ

**ተግባር ሦስት፡- <u>ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ"ሀ" አምድ ላሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ"ለ" አምድ በመምረጥ አዛምዱ</u>፡፡**

| **<u>"ሀ"</u>** | **<u>"ለ"</u>** |
|---|---|
| 16. ገርበብ | ሀ. መቀለጃ |
| 17. ዘለቀ | ለ. ወሬ |
| 18. ጉድ | ሐ. መቆጣት |
| 19. አራስ | መ. መገላመጥ |
| 20. እርግብ | ሠ. ደስታ |
| 21. ሰሌዳ | ረ. ሰራተኛ |
| 22. ገረድ | ሰ. ግንባር |
| 23. ሃሴት | ሸ. ዘርፌ |
| 24. መገርመም | ቀ. የወለደች |
| 25. ወግ | በ. ችግር |
| | ተ. ገባ |
| | ቸ. መገረም |

**ተግባር አራት፦ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለተሰመረባቸው ቃላት በፍቺ አቻ የሆኑትን ከሰንጠረዡ በመምረጥ ተኩ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፈንጠር | ስታሰላስል | ላንጻፍታ | ታላቅ የምስራች | የቦክሱን |
| አደብ ይግዙ | ለአብራክ ክፋይ | ነሳው | መግፋት | አፍክተው |

26. ነፍሰ ጡሯ ሆዷ መጨመር ያዘ፡፡
27. ዘጠኝ ወር እስኪሞላው ድረስ አጠገቡ እያለች ናፍቆት እንቅልፍ ከለከለው፡፡
28. በቤታቸው ሃሴት ሆነ፡፡
29. ረዘም ላለ ሰዓት ስለጎጆዋ ስታስብ ራስዋን ስለሚያማት "ተነሺ!" ትላታለች፡፡
30. እትዬ ሻሾ ፊታቸውን ፈገግ አድርገው በሰራተኛዋ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ቅጣት ይከታተላሉ፡፡
31. እጁ እስኪዝል የቡጢውን አቅም አሳይቷታል፡፡
32. ኧረ እትዬ ዝም ይበሉ፡፡
33. ባለቤቴ ለልጁ እንጂ ለእኔ ግድ የለውም፡፡
34. ከሷ እራቅ ብሎ ባሏ ተቀምጧል፡፡
35. ቶሎ ደረስ ብዬ ልመለስ እንጂ ልቀመጥ መች መጣሁ?!

**ትምህርት ሁለት**

## የትምህርት ርእስ፡- ደብዳቤዎች

**የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦**

- በምንባቡ መሰረት የማንበብ ክሂል(መረዳት) ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቺዎችን ይሰጣሉ፤
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ምክንያቱን ያብራራሉ፤
- ቡድን በመወያየት የምንባቡን ሃሳብ ይገልፃሉ፤

## ክፍል አንድ፦ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**ሀ.** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ደብዳዴዎቹ ከሚለው የምንባብ ርዕስ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ?
2. ደብዳቤ ምንድነው? አንብባችሁ ታውቃላችሁ? ለምን ይጠቅማል?

**ለ.** ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ግለፁ

**. ደብዳቤ . ባዕድ . ጡር . እየኳተነ**

**ደብዳቤዎቹ**

*እሷ፡-*

*ውድ ናዖድ፡ …*

*በትላልቅ ፊደላትና በደማቅ ቀለማት በልቤ መዝግ ላይ የፃፍኩት ስምህን እንዳልነበረ አድርጌ የደለዝኩት መስሎኝ ነበር፡፡ አንተን ሊያስታውሰኝ ይችላል ብዬ የማምነውን ነገር ሁሉ ንፋስ እንደጎበኘው ዱቄት ከንቱ የሆነ መስሎኝ ነበር፡፡*

*ይኸው ዛሬ ከዓመታት በኋላ፣ ከስነትና ስንት ክረምት በኋላ፣ እያንዳንዱ ለሌት አንተን ሳላስብበት እንደማላነጋ እንድነግርህ፣ አፍካሪዋ ልቤ፣ አፅናኝ የተራበችው ነፍሴ፣ ግድ አለችኝ፡፡*

*በውብ ቃላት ከሽነህ ትፅፋቸው የነበሩ የፍቅር ደብባቤዎች በስሜት እንድታሰር ያደረጉኝ እንደነበር ትዝ ይልሃል ወይ? እኔ የምልህ ቃላት ከሚፈበረኩበት አገር ነበር ወይ የተወለድከው? … ይልቁንስ ያልገባኝ አንድ ነገር አለ፡፡ እኔን ስትጠራኝ በሙሉ ስሜ አልነበረም፡፡ በቁልምጫም አልነበረመረ፡፡ ባወጣህልኝ ቅፅል ስም ነበር የምትጠራኝ፡፡ ምን ማለት እንደሆነ ስጠይቅህ ጊዜው ሲደርስ እነግርሻለሁ ትለኝ ነበር፡፡ አሁን ትርጉሙን ጽፈህ ብትልክልኝ እንዴት እደሰት ነበር?!*

*እሷ፡-*

*አድራሻሽን እንጂ ስምሽን ያልፃፍሽው እንስት ሆይ፤ ማን ብዬ ነበር የምጠራሽ?*

*እሷ፡- ኒጺ ትለኝ ነበር፤ ኒጺኤል፡፡ ምን ማለት ነው?*

*እሱ፡- ኸሃ! ይሄ ስም ለካስ ከዚህ ቀደምም ውብ ኮረዳዎችን ለማቆለጳጳስ እጠቀምበት*

ነበር?! … ውድ የጥንት ነገር አታዋሺ? … ኒጂኤል የባዕድ ቃል ነው፣ "ዕብራይስጥኛ፡፡" እግዚአብሔር ለኔ መርጦ ያዘጋጃትና ያስቀመጣት ማለት ነው፡፡ እኔ የምለው ለምንድነው እኔን ሃሳብ ላይ መጣል የፈለግሽው? ፍቃድሽ ከሆነ ለሚቀጥት ጥያቄዉች መልስሽን ላኪልኝ፡፡

1.1 መልክሽምን ይመስል ነበር?

1.2 በየትኛው ዓመት ላይ ነው የኔ የነበርሽው?

1.3 እንዴት ባለ ሁኔታ ነው ያገኘሁሽ?

እሷ፦ደብዳቤህ እንደደረሰኝ ጻፍኩልህ፡፡ የቅፅል ስሜ ትርጉም እንዴት ደስ ይላል? በትርጉሙ መሰረት እየኖርነው መሆኑስ አጃኢብ አያሰኝም?! ጥያቄዎችህን ግን

ወደድኳቸው፡፡ መልሳቸውም የኸው፡፡ ጥቁር ነኝ፡፡ ረዥምና መካከለኛ ውፍረት ያለኝ፡፡

ከአምስት ዓመት በፊት ያንተ ነበርኩ፡፡ አዘውትሬ እምመላለስበት ከነበረ ካፌ ውስጥ ነበር፤ ባዶ ወንበር አግኝተህ፤ ከተቀመጥክበት በኋላ የተዋወቅከኝ፡፡ ይልቁንስ አንድ ቀልድ ልንገረህ፡፡ ሁለት ፍቅረኛሞች ነበሩ፤ ልክ አንተና እኔ እንደሆነው የሆኑ፡፡ በኋላ ተለያዩ፤ አንተና እኔ

በሁኔታዎች አለመመቻቸት ተቃቅረን እንደተራራቅነው ሁሉ! … እና - እሷ- ወታደር ለሆነው ፍቅረኛዋ ደብዳቤ ጻፈችለት፡፡ እንዲህ ብላ 'አንተን መጠበቁ ስለሰለቸኝ ሌላ አፍቅሬያለሁ፡፡ በቅርቡም ደግሰን ልንጋባ ነው እና ፎቶ ግራፌን ላክልኝ' ብላ ፃፈችለት፡፡ ታዲያ የተፃፈለት ሰውዬ በርካጻ ፎቶዎችን በፖስታ አሽጎ 'ያንቺ የሆነውን መርጠሽ ውሰጂ፡፡ ያንቺ ያልሆነውን ግን ላኪልኝ፡፡ አደራ' ብሎ ቆሽቷን አሳረረው፡፡ አንተም ልክ እንደዚህ ሰውዬ ሆንክብኝ፡፡

እሱ፦

ኧይ የጥንቷ! ቀልድሽ አሳቀኝ፡፡ አንቺው የፈጠርሻት መሆን አለባት፡፡ አንቺ ታፌዣለሽ፡፡ እኔ ግን የምሬን ነው፡፡ አሳስቦኛል፡፡ እባክሽን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ አንብቢና ከእኔ ጋር ባሳለፍሽው የፍቅር ህይወት መሰረት መልስ ስጪባቸው፡፡

2.1 ለመለያት ምክንያት የሆነን ምንድነው

2.2 አሁንስ በምን አይነት ሁኔታ ላይ ትገኚያለሽ

2.3 ወንድ ልጅ በቅናት ተጨብጦ ጡንቻውን ካልፈተሸብኝ የሚወደኝ አይመስለኝም የምትይዋ ነሽ? ወይስ ጎህ ሳይቀድ ለማኝ ከመፀዳዳቱ በፊት፤ ስልክ እየደወልሽ በህልምሽ ምን ስናደርግ እንዳየሽ የምታወጊኝና ከእንቅልፍ እያስቀሰቀሽ የምትተርቢኝ ነበርሽ? የትኛዋ ነሽ አንቺ? በውል ልለይሽ አልቻልኩም፡፡ ቀልዴን አይደለም፡፡

እሷ፦ ናዖድዬ! ጥያቄዎች ከዚህ በፊት ስለሆነው ነገር በጥልቀት እንዳስተውል ረድተውኛል፡፡ መልሶቻቸውም እነሆ!

ለመለያየት ምክንያት የሆነን ጉዳይ ትረሳዋለህ ብዬ አላስብም፡፡ ጓደኛዬ የፃፈችልኝን ደብዳቤ እለብሰው በነበረው በአንተ ጃኬት ውስጥ አገኘኸው፡፡ ደብዳቤው ላይ፣ ሱራፌል ከተባለ ልጅ ጋር አሳልፌው ስለነበረ ‘የፍቅር ህይወት’ በሰፊው ተፅፎ ነበር፡፡

ዝዋይ ሆና፣ እባክሽ ያላንዳች ምክንያት ፍቅረኛን መለየት ጡር ነው፤ በሰማይ በምድርም የተደላደለ ህይወት አይኖርሽም ብላ፤ የፃፈችልኝን ደብዳቤ ነው አንተ ያገኘኸው፡፡ ጓደኛዬ ስለሱራፌል እነግራት ነበር እንጂ እሱን በአካል አታውቀውም፡፡ እሷ የፃፈችውን ደብዳቤ አግኝተህ በማንበብህ፤ ካንተ ጋር ያለኝ ፍቅር አደጋ ላይ መውደቁን፣ እያነባሁ ስነግራት በጣም ነበር የደነገጠችው፡፡ ካንተ ጋር መወዳጀቴን ትቃወም ነበር፤ አይመጥንሽም ለማለት ሳይሆን “ሱራፌልን መተው የለብሽም” ብላ ነበር…እየህ ናዖድ፤ ጓደኞቼ ባገኙኝ ቁጥር አዋሳ በሚቆዩባቸው ጊዜያት ከፍቅረኞቻቸው ጋር ስለ ተዝናኑባቸው መናፈሻዎች፣ ስለተንፈላሰሱበት አልጋ፣ ስለተደሰቱባቸው ቴአትሮች፣ ስለጎበኟቸው ታላላቅ መዝናኛዎች እያወሩልኝ በሄዱ ቁጥር ቅናት ቤቱን ሰራብኝ፡፡ በዕድሜ ይበልጡኝ የለ?! በዕድሜ ብቻ አይደለም በብዙ ነገር አንሳቸዋለሁ፡፡ እና የማወራው ነገር አስፈለገኝ፡፡ ያልኖርኩትን ህይወት መተረክ ልማዴ ሆነ፡፡

ናዖድ! ወደ ሁለተኛው ጥያቄህ ስንሄድ፤ አሁን በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳለሁ ማወቅ ፈልገሃል፡፡ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነው ያለሁት፡፡ አዕናኝ የሌለው አልቃሻ ሆኛለሁ፡፡ እግዜር እኔን ረስቶኛል፡፡ ፍቅር ከልክሎኝ በብቸኝነት ነው የምኖረው፡፡ ግን ምን ዓይነት ሃጥያት ሰርቼ ነው እንዲህ የምቀጣው?! … ምን ወንጀል ሰርቼ ነው

*ሲኦሌን ምድር ላይ እንድጨርሰው የተፈረደብኝ?! … እንባዬን እንዲያብስ የተፈጠረው ወንድ በዚህ ሰዓት ምን እየሰራ ይሆን? ወይስ  እሱም የማያውቀኝን እኔን ፍለጋ እየኳተነ ይሆን?…*

*ናሆድ፤ ለሶስተኛው ጥያቄህ መልስ፣ በህልሜ ያየሁትን የምነግርህ ነበርኩ፡፡*

*እሱ፡-*

*አውቄሻለሁ፡፡ መጀመሪያውኑም ግልፅ አድርገሽ ብትነግሪኝ ኖሮ የሂን ሁሉ አላፋሽም ነበር፡፡ በምን እንደተጣላንና የፍቅር መንገዳችን በአጭሩ ሊቋጭ ስለቻለበት መንገድ ስትፅፊልኝ፤ ለምንድነው እንደተራ ነገር ጠቀስ አርሽ ብቻ ልታልፊው የምትሞክሪው? ወይስ እኔን በደለኛ የማድረግ ሃሳብ በውስጥሽ አለ? ጓደኛሽ የፃፈችው ደብዳቤ ስለቀድሞ ፍቅረኛሽ በቂውን ያህል እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ የዋለልሽን ውለታ መዘክዘክ*

*የማይታክትሽ ሴት እንደነበርሽኮ ከአስር ጊዜ በላይ ነው የጠቃቀሰችው፡፡ ታምመሽ ሆስፒታል ገብተሽ በነበረ ጊዜ አሳክሞሽ የለ? የእናትሽን ቤት ለማሳደስ ያወጣው ወጪ ቀላል እንዳልሆነ ከመናገር ቦዝነሽ የማታውቂ ሰው መሆንሽን በደብዳቤው ተፅፎ ነበርኮ! የሁለት እህቶችሽን የግል ኮሌጅ ወጪ ለመሸፈን ያደረገው አስተዋፅኦስ መች በቀላሉ የሚገመት ሆኖ? ሊያደርጋቸው እንደሚችል ተስፋ የምታደርጊያቸውን በርካታ ቃልኪዳኖች እያሉ፤ ድንገት "እንኳኋንም" በሚል በተዳፈነ ምክንያት ሱራፌልን ርቀሽ በቅጡ ካልተግባባሽኝ ከኔ ጋር መወዳጀትሽን ጠልታ ነበርኮ ጓደኛሽ በደብዳቤ ትወተውትሽ የነበረው?*

| |
|---|
| . እስካሁን ካነበባችሁት ታሪክ ምን ተረዳችሁ? |
| . በቀሪው የምንባብ ክፍልስ በደብዳቤዎቹ ውስጥ ምን የሚነሳ ይመስላችኋል? |

*ታዲያ ማሰብ የተሳነኝ ካልሆንኩ በቀር እንዴት ላምንሽና የራሴ ላደርግሽ እችላለሁ?! … የቀድሞ ፍቅረኛሽ ደብዳቤው ላይ የተዘረዘረውን ውለታ ውሎልሽ ጣል ጣል እንዳደረግሽው ሁሉ፣ እኔስ ላይ እንደዚህ አይነት ጭፍን እርምጃ ብትወስጅብኝስ? አዎ! ለጓደኛሽም የነገርኳት ይህን ነው፡፡ የማይመስል ነገር ተናግረሽ አሳምነሻት ልታሳምነኝ መጥታ ነበር፡፡ ይቅርታ እንዳደርግልሽ እግሬስር ወድቃ ተማፅናኝ ነበር፡፡ የዋህ ናት፡፡*

ማን ይሙት አንቺን "እሺ" ብዬ የኔ ባደርግሽ እግዜር አይስቅብኝም? የሱራፌል እንባ አይረብሸኝም? ጓደኞቼ አይሳለቁብኝም? የሚያውቁኝ አይዘባበቱብኝም?!

እ፦ ውድ ናያድ አሁንም አምነህ አልተቀበልከኝም ማለት ነው? በአንድ ወቅት አንድ ስመጥር የራሻ ደራሲ የፃፈውን ልብ የሚነካ አጭር ልቦለድ አነበብኩ፡፡ ምን አይነት አሳዛኝ ታሪክ ነው መሰለህ? አይገርምም! ለራሷ የፍቅር ደብዳቤ የምትፅፍ ሴት አለችበት እና እኔም የሚፅፍልኝ ሳይሆን የሚደውልልኝ ሰው አዘጋጀሁ፡፡

እሱ፦
የሚደውልልኝ ሰው አዘጋጀሁ ማለት ምን ማለት ነው? አንዳንዴ የምትፅፊው ነገር ግራ ያጋባል፡፡ የሆነው ሆኖ ውሸት የመፍጠር ብቃትሽን እንደማደንቀው ላሳውቅሽ እወዳለሁ፡፡

እ፦ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ ትምህርት ቤት አጠገብ ያለ -አንድ ነስሩ የሚባል- ባለ ሱቅ ተግባብቼ ነበር፡፡ አንድ ቀን ሱቅ ሄጄ፣ "ላስቸግርህ ነው" ብዬ፣ በሳምንት ሁለት

ሶስት ቀን "ሱራፌል ነኝ" ብሎ በጓደኛዬ ስልክ እንዲደውልልኝ ጠየኩት፡፡ እኔም ሱራፌል ፍቅረኛዬ እንደሆነ በማስመሰል መልስ እንደምሰጠውም ነገርኩት፡፡ የፍቅር ቃላት ባሰሰማ፣ ባንቆለጳጵሰው፣ አኩራፊና ተነጫናጭ ሆኜ ጆሮው ላይ ስልክ ብዘጋ እንኳን፣ ድራማ እየሰራን እንደሆነ ብቻ ልብ ማለት እንደሚገባው አበክሬ ገለፅኩለት ስልክ የደወለበትን የምከፍለው እኔ ነበርኩ፡፡ ባለሱቁ ደስ እያለው ነበር "አድርግ!" ያልኩትን ይታዘዘኝ የነበረው፡፡ ምን ያህል እንዲገባህ እንዳደረግሁ አላውቅም፡፡ እውነቱ ግን ይሄ ነው!

እሱ፦ምን እንደምልሽ አላውቅም፡፡ የምልሽ ነገር ቢኖር እንኳን ተረጋግቼ እንዳልፅፍልሽ ጊዜ አጥሮኛል፡፡ ልትገምቺ ከምትችይው በላይ የጊዜ አጥረት እያስጨነቀኝ ነው … ቻው! ከሶስት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ አቋርጦ የሚመጣው ደብዳቤሽን ለማንበብ እንኳን አልመቻች እያለኝ ነው፡፡

እ፦ ናያድዬ የኔ ውድ! የኋላ ታሪኬን አውግቼህ አላውቅም አይደል? ያለ ዕድሜዬ እንዳይድሩኝ ብዬ ከገጠር የሶስት ሰዓት እግር መንገድ ተጉዤ፣ ወልቂጤ ከተማ ገብቼ፣ ተምሬ፣ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቴን ለመጨረስ በቃሁ፡፡ ከተደጋጋሚ ሙከራ በኋላ ኮሌጅም ገባሁ፡፡ ወጣትነቴን በትምህርት ፈጀሁት፡፡ ተመልሼ ወደ ገጠር ሄጄ

ትዳር ብመሰርት  ምንኛ ደስ ባለኝ፣ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ ከሚኖቁት፣ ሸክላ በመስራት ከሚተዳደሩት የራሴ ጎሳ አባላት መሃል አንዱን እንዳላገባ እንኳን እነሱ አይፈልጉኝም… አርጅቻለኋ!

እሱ፦ ለምንድንነው የማይመለከተኝን ነገር እየፃፍሽልኝ በጊዜዬ ልትቀልጅበት የምትሞክሪው?! የጭውውታችን ገደብ እያለፈ አይመስልሽም?!

እሷ፦ እንደ አሮጊት ነዘነዝኩህ አይደል?! እናት የመሆን ናፍቆት እንዴት እየተፈታተነኝ እንደሆነ ልነግርህ አልችልም፡፡ ሳይሞሸሩ፣ የልጅ እናት ሳይሆኑ የማርጀትና የመጃጀት ፍርሃት እንዴት እንቅልፍ እንደሚነሳ ታውቅልኝ ይሆን?! ለኔ የተመረጠው ወንድ ጭራሽ ያልተወለደ ያልተፈጠረ ሲመስለኝ እረበሻለሁ፡፡ ሆድ ይብሰኛል፡፡ ማልቀስ እፈልጋለሁ፣ ስቅስቅ ብዬ ማልቀስ፣ ማንም አባባይ፣ እንባ አባሽ በሌለበት ክፍል ውስጥ ብቻዬን ሆኜ! … በስንት መከራ አንተን አገኘሁህ! እሰይ ስለቴ ሰመረን ዘምሬ ሳልጨርስ ተለየሁህ… አያስደነግጥም? ነገዋን በመፍራት በስጋት የምታዜም የብቸኛ ወፍ ድምፅ አትሰማም?!

እሱ፦ ከኔ ጥንት ፍቅረኛሽ ከነበርኩ ሰው አንዳች ነገር እንደምትፈልጊ ይገባኛል፡፡ ያ! የሚፈለግብኝን ነገር ግን አላወቅሁትም፡፡ በጠመዝማዛ የቃላት መንገድ ከምታስኳትኚኝ ለምን እጥር ምጥን ባለ ቃል ፍላጎትሽን አትገልጪልኝም? እንዴት ነው ነገሩ?!

እሷ፦ ውዴ! ፍላጎቴ ምን መሰለህ?! ፍርሃቴን መጎዳቴንና መሰቀየቴን የምታስወግድ መኩሪያዬ እንድትሆነኝ ነው፡፡ ወደ ውስጤ ገብተህ ብቸኝነቴን እንድትገድለው ብቻ አይደለም፡፡ ናፆድዬ ላስቸግርህ ነው፡፡ ሶስት ታናናሽ እህቶች አሉኝ፣ ሶስቱም ባለትዳሮች ናቸው፣ ሁል ጊዜ ስለኔ ያስባሉ፡፡ ብቸኝነቴና ቆሞ ቀር መባሌ ያሳስባቸዋል፡፡ እንደሚረብሸኝ ያውቃሉ፡፡ በዓል በመጣ ቁጥር ጓዝ ጉዝጓዜን ይገፍ ከወላጆቼ ጋር ጊዜዬን አሳልፋለሁ! እህቶቼ ሁለት ሶስት ልጆቻቸውን ይዘው ሲሄዱ እኔ ግን "እማዬ" የሚለኝ ህፃን የለም፡፡

የኔ ጌታ ላስቸግርህ! "አግባኝ" እያልኩህ አይደለም፣ ግን "እጮኛዬ ነው" ብዬ አንተን የገፍ ገጠር ከሚኖሩት ወላጆቼ ጋር ላስተዋውቅህ?! ጥያቄዬ ፈታኝ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ግን አንድ ሐሙስ የቀራቸው የሚመስሉ ወላጆቼ አስደስቼያቸው እንዲሞቱ አድርግ! እንወዳጅ ስልህ በሩካቤ ስጋ አይደለም፡፡ ምን እነደሆነ ታውቃለህ? የኔ ውሃ

አጣጪያቸው እንድሆን ጠይቀውኝ የነበሩ የትላንት ጎረምሶች ዛሬ ወደ ጎልማሳነት እየተጠጉ ነው፤ ዘንድሮም ሲያዩኝ እንደ አምና ካቻምናው እንዳያሽሟጥጡኝ አንተ አግዘኝ፡፡ ደጋግሜ እልሃለሁ፡፡ ናያድዬ! የምቀርበው ወዳጅ ከጎኔ እንዳለ እንዲሰማኝ አድርግ፤ ነፍሴን ከመረበሽ ታደጋት፡፡

እሱ፡- ድሮ "ጊጂ" ብለህ ትጠራኝ ነበር ያልሽዋ! በውስጥሽ የተፀነሰው እኩይ ስሜት አልተዋጠልኝም፡፡ እንዲህ ያለ ሃሳብ ጉድ ሳያፈላ በእንጭጩ መቀጨት አለበት፡፡ እንዲህ ያለ ጨርቁን የጣለ ሃሳብ በህሊናሽ ጓዳ እየተንጎራደደ እንዲመላለስ አትፍቀጂለት፡፡ ምን እየሆንሽ ነው?! ነካ አድርጎሻል ልበል?!

እሷ፡- ለሁለት ቀናት ብቻ እኮ ነው፣ "የውሸት ባል" የምትሆነኝ? በትውልድ ቀዬዬ ተመላልሰንበት ስድቤን አስፍቄ እንመለሳለን እኮ ነው የምልህ፡፡

እሱ፡- ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይህንን ደብዳቤ ፅፌልሻለሁ! አንቺ የድሮዋ ጓደኛዬ! የምንመላለሳቸው የፅሁፍ መልዕክቶች ሰላሜን ከማደፍረስ ውጭ አንዳችም ነገር አልፈየዱልኝም፡፡ እሎኘኛዬ እጅ ቢገቡ ሊያንቸብብብኝ የሚችለውን አደጋ መገመት

እንዴት ይሳንሻል?! ... እኔን የሌለሁ ያህል እርሺኝ፡፡ እወደዋለሁ ባልሺው ልቤ ስም ደጅ እጠናሻለሁ፡፡ እርሺኝ!

ስለኔ ለማንም ምንም አትበይ፡፡ አንተዋወቅም፤ አብረን የቆረስነው የፍቅር እንጎቻ የለም፡፡ ቢኖርም የሻገተ ነበር ብለሽ በንቀት እለፊው፡፡ ምንም ይምጣ ምን እርሺኝ፡፡ በትክክል የምትወጂኝ ከሆነ ይህቺን ውለታ ብቻ ዋይልኝ፣ እሺ?

እሷ፡- እሺ

**ክፍል ሁለት፡- ድኅረ ምንባብ ጥያቄ**

**ተግባር አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በአጭሩ ግለፁ፡፡**

1. ደብዳቤዎቹ የሚያወሩት ስለተጋቡ ባልና ሊስት ነው፡፡
2. እሷ ናያድን ለማግባት አጥብቃ ምትፈልገው ሀብታም ስለሆነ ነው፡፡

3. ለፍቅረኛሞቹ መለያየት ምክንያቱ እሱ በኪሱ ውስጥ ያገኘው ደብዳቤ ነው፡፡
4. እሷ ናየድን ገጠር ይዛ መሄድ የፈለገችው ያረጁ ቤተሰቦቿን ለማስደሰት ብቻ ነው፡፡
5. እሷ ከሱራፌል ጋር የምትፃፃፈው ደብዳቤ የውሸት ነበር፡፡

**ተግባር ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይህን ደብዳቤ ፅፌያለሁ ያለው ማን ነበር?

   ሀ. እሷ ለ. ናየድ ሐ. ሱራፌል መ. ጓደኛዋ
2. ባለታሪኳ የውሸት የፍቅረኛ ድራማ ለመስራት የተስማማችው ከማን ጋር ነበር?

   ሀ. ከሱራፌል ጋር ለ. ከናየድ ጋር ሀ. ከሽምሱ ጋር መ. ከነስሩ ጋር
3. "በደማቅ ቀለማት በልቤ መዝገብ ላይ የፃፍኩት ስምህን እንዳልነበር አድርጌ <u>**የደለዝኩት**</u> መስሎኝ ነበር" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ ምንድነው?

   ሀ. ያጠፋሁት ለ. የወቀጥኩት ሐ. ያኖርኩት መ. የቸከቸኩበት
4. የባለታሪኳ ቅፅል ስም ማን ነበር?

   ሀ. ኒቆሪያ ለ. ሰላማዊት ሐ. ኒጺኤል መ. ሳራ
5. ፳. የቅፅል ስሟ ትርጉም ምን ነበር?

   ሀ. ቆንጆ ማለት ነው

   ለ. እግዚአብሐር ለኔ መርጦ ያዘጋጃትና ያስቀመጣት ማለት ነው

   ሐ. እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ነው

   መ. የእኔ ዘውድ ነሽ ማለት ነው
6. "እኔና አንተ በሁኔታዎች አለመመቻቸት <u>**ተቃቅረን**</u> እንደተራራቅነው ሁሉ! …" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፍቺ -----------------ነው፡፡

   ሀ. ተጣልተን ለ. ተዋደን ሐ. አቀርሽቶን መ. ተስማምተን
7. በሁለተኛው አንቀፅ የተገልፀው ሃሳብ ምንድን ነው?

   ሀ. ያለፈ ታሪክ ለ. ለዓመታት በፍቅር መሰቃየትን

   ሐ. ባማረ ቃል ስለሚፃፉት ደብዳቤዎች መ. ስለትዳር
8. እሱ በመጀመሪያ ጊዜ ካቀረባቸው ጥያቄዎች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

   ሀ. መልክሽ ምን ይመስል ነበር

ለ. እንዴት ባለሁኔታ ነው ያገኘሁሽ

ሐ. አሁንስ በምን አይነት ሁኔታ ላይ ትገኛለሽ

መ. በየትኛው ዓመት ላይ ነው የኔ የነበርሽው

9. "አብረን የቆረስነው **የፍቅር እንጎቻ** የለም፡፡" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺ ምንድነው?

ሀ. ለልጅ የሚጋገር ትንሽዬ እንጀራ ለ. በማር የሚጋገር እንጀራ

ሐ. የህፃን ልጅ ማዘያ መ. በፍቅር ያሳለፍነው ትንሽጊዜ የለም

10. እሷ ሃገሯ ብቻዋን መሄድ ምትፈራው ለምንድነው?

ሀ. ቆሞ ቀር ስለምትባል ለ. ያረጁ ወላጆቿ ባለማግባቷ ስለሚያዝኑ

ሐ. ሊያገቧት ጠይቀው ያላገኟት ጎልማሶች ስለሚሰድቧት መ. ሁሉም መልስ ነው

11. "የኋላ ታሪኬን **አውግቼህ** አላውቅም አይደል?" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ -------------- ነው፡፡

ሀ. አውርቼህ ለ. ወግቼህ ሐ. ፅፌልህ መ. አሳይቼህ

12. በምንባቡ መሰረት የናየድ አቋም/ ሃሳብ ምን ዓይነት ነበር?

ሀ. የሚራራ ለ. ተቀያያሪ ሐ. ፅኑ መ. ወሽካታ

13. ጓደኛዋ ሱራፌልን እንድታገባ የምትፈልገው ለምንድን ነው?

ሀ. ናየድን ስለምትጠላው ለ. ናየድ ስለማይነጥናት

ሐ. ሱራፌልን መተው ጡር ይሆንብሻል ብላ መ. ሱራፌል ገንዘብ ስለማይሰጣት

14. ናየድ የሚፅፈውን ደብዳቤ የወደደችው በምኑ ነው?

ሀ. በቃላት አመራረጡና አገላለፁ ለ. በተለያዩ ደማቅ ቀለማት ስለተፃፈ

ሐ. መዝገብ ላይ በመፃፉ መ. ብዙ ደብዳቤ በመሆኑ

15. ሁለቱ ባለታሪኮች የት ነው የተዋወቁት?

ሀ. ትምህርት ቤት ለ. ካፌ ውስጥ ሐ. ሀገር ቤት መ. ታክሲ ውስጥ

**ተግባር ሶስት፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ**

| **"ሀ"** | **"ለ"** |
|---|---|
| 16. ለማንቆለጳጰስ | ሀ. የትውልድ ሰፈር |

17. ታፈግፍለሽ
18. ጎህ ሳይቀድ
19. መዘባበቻ
20. ገደብ
21. ቆሞ ቀር
22. በእንጭጩ
23. ቀዬ
24. መማፀን
25. አዘውትሬ

ለ. ደጋግሜ
ሐ. ለማወደስ
መ. ትቀልጃለሽ
ሠ. መለመን
ረ. ሳይነጋ
ሰ. ልክ
ሸ. ያላገባ
ቀ. በጅምሩ
ተ. መቀለጃ
ቸ. ጠርዝ
ኀ. ጋብቻ

**ተግባር አራት፦ <u>ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ከቀረቡት ቃላት መካከል አውድን መሰረት አድርጋችሁ በመምረጥና ባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ፃፉ</u>፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ደፋ | ሳይቀድ | ሀጥያት | ሐኬተኛ | ወላፈን |
| ጭፍን | የመፍጠር | በቅጡ | ጎረምሶች | አውግቶኝ |

1. የደብዳቤው---------------- ለሷመለያየት ምክንያት ሆነ፡፡
2. የፍቅር------------------- ዘወትር ይገርፋታል፡፡
3. ነፃድ እሷ የምታደርገውን ድርጊትና ሃሳብ እንደ--------------- እንዲቆጥራት አድር አድርጓል፡
4. ጎህ------------------ ሳይቀድ በፊት ትደውልለት ነበር፡፡
5. እንደዚህ ዓይነት ------------------- እርምጃ እንዳትወስጂ፡፡
6. ውሸት ------------------- ብቃት አለሽ፡፡
7. ሱራፌልን እርቀሽ ------------------- ካልተግባባሽኝ ከኔ ጋር መወዳጀትሽን ጠላሁት፡፡

8. ታሪኩን ---------------- አያውቅም፡፡

9. የትላንት ---------------- የዛሬ ጎልማሶች ናቸው፡፡

10. ምን አይነት -------------------- ሰርቼ ነው የምቀጣው፡፡

## ትምህርት ሶስት

### የትምህርቱ ርእስ፡- እትዬ አልታዬ

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- ቅድመ ምንባብ እና ድህረ ምንባብ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፤
- የምንባቡን ሃሳብ አሳጥረው ይገልፃሉ፤
- ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፤

### ክፍል አንድ፡- ቅድመ ምንባብ ጥያቄ

ርዕሱን በማየት ምንባቡ ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

### እትዬ አልታዬ

እንዳጋጣሚ ቀኑ የተሟላ ዕለት ጊዜና ገንዘብ እኩል የፈቀዱ ዕለት፣ ብርሃኑና ጥላዬ ከወደ ውሃው ለማለት፣ እና ተዝናንተውም ለማውጋት ለመጫወት፤ ጠያይዘው ወደ እትዬ አልታዬ ቤት፡፡

እትዬ አልታዬ ቤት የኩላሊት ሰፈር መገናኛ መደሰቻ ነው፡፡ ትሰሜ እቺ በክራር የምትዘፍነው፤ "እንጦጦ ላይ ሆኖ ይታያል ኩላሊት፤ የትያልታዬ ቤት የሁከት መድኃኒት" ያለችውም ሳቅና ጨዋታ ስለሚበዛበትና ሰው ውስጣዊውን ሁከትና ብቸኝነት ለመሸሽ ስለሚጎበኘው ነው፡፡

የትዬ አልታዬ የቀኝ ጎረቤት "ዕድሜ ቀጥል ጣፋጭ ክትፎ ቤት" የሚል በቢክ እስክሪብቶ የተጣፈባት ካርቶን ወረቀት፡፡

የትዬ አልታዬ የግራ ጎረቤት "ልዩ ልዩ በያይነቱ ጠቅላላ የሬሳ ሳጥን መሸጫ መደብር ቤት አስተያየት እናደርጋለን" የሚል በቀይ የተጻፈበት ቆርቆሮ ከበሩ በላይ ተሰቅሎ፤ አንድ ጥቁር የሬሳ ሳጥን ግድግዳውን ተደግፎ ዘብ ቆሞአል፡፡

ብርሃኑ በግማሽ ስካር፣ "እዚች ክትፎ በልተን፣ ዕድሜያችንን መርጠን አዘን፤ ካረቄ የተረፈውን ገንዘብ ቀብድ አስይዘን ስናበቃ ወደቤታችን" አለ፡፡

"ጥላዬ 'ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት' እንዲሉ አባቶች" አለ፡፡

"ምጣድ አይቶ ጠሃይ፣ እንጎቻ አይቶ ጨረቃ እንዲሉ እናቶች"

"አይ የስካር ሞቅታ፤የጠላ ጠብታ እንዲሉ ፈረንጆች"

ሁለቱ ጎረምሶች በዚህ እየሳቁ እትዬ አልታዬ ቤት ጥልቅ፡፡ እትዬ አልታዬ ፈገግ ብለው ወርቅ ጥርሳቸውን ብቅ፡፡

እትዬ አልታዬ የእትየነቱን ዘመን የትና የት ጥለው ሄደው፣ የእማማነቱንም ዘመን እንደ ወዶ ማለፉ ብለው፣ ሊያከትሙ ሲኒያቸውን ሊደፉ አንድ ሐሙስ ቀርቷቸው፣ እንዲሁ በዘልማዱ እትዬ እየተባሉ፤ ወርቅ ጥርሳቸውን ብልጭ ድርግም እያደረጉ፤ ጠላ እየጠመቁ አረቄ እየሸጡ፣ ገንዘብና ጊዜ እየቆጠሩ … ምናባቷንስ ይቺ ኑሮ፣ ሞት ይህ ክፉ ተንኮለኛ ድመት፤ አይጥ ሆነው ቢጠሩት ቢጠሩት አይል አቤት … እትዬ አልታዬ ሞትን "ውርርርር" እስኪሉትና "ሚያው" እስኪላቸው እኛ ስለወርቅ ጥርሳቸውና

እንዲሁም ስለፈገግታቸው እንናገርላቸው… እግረ መንገዳችንን ሌሎችንም እናንነሳ እናወሳ ይሆናል፡፡

እትዬ አልታዬ ፈገግ ሲሉ ሲታዩ፣ ጊዜ በስውር እጅ ይዞ በጭካኔ ሳይሆን እየሳቀ በዝግታ እንደወረቀት ጭርምትምት ያደረጋቸው ይመስላል፡፡ ፊታቸው የሚስቅ መዳፍ የመስላል፡፡ (መዳፍ እንደማይስቅማ የታወቀ ነው፡፡ ግን አንድ ቀን ሳት ብሎት ቢስቅስ?) ታዲያ የትዬ አልታዬ ፈገግታቸው ሲታይ ልብ ይሰውራል፡፡ በተለይማ ከብርሃኑና ከጥላዬ ጋር ሲቃለዱ የሚታየው ፈገግታቸው የሺ አመት ደግነትና ፍቅር የተከማቸበት ይመስላል፡፡

እንግድያማ ብርሃኑና ጥላዬ ወይ አንዳቸው ወይ ሁለታቸውም ልጆቻቸው ናቸውን? ቢባል፣ "ሊሆንም ይችላል ላይሆንም ይችላል" ይሏል ባዲሳባ አነጋገር፡፡

. እስካሁን ካነበባችሁት ምን ተገነዘባችሁ? ከዚህ ቀጥሎስምን ሊነሳ እንደሚችል ገምቱ?
. እትዬ አልታዬ በምንድን ነው የሚተዳደሩት?
. የትዬ አልታዬ ቤት የት ሰፈር ነው የሚገኘው?
. ጥላዬና ብርሃኑ ግንኙነታቸው ምንድን ነው?

ሁለቱ ገብተው እንደተቀመጡ እትዬ አልታዬ በገዛ እጃቸው እናትና ልጅ ቀዱላቸውና ጠርሙሱን ይዘው ቆመው የዩዋቸው ጀመር፡፡ እናት ለልጁ አንድ አንድ መለኪያ ደስታ ለክታ የምታጠጣቸው ይመስላሉ፡፡ ብርሃኑ እንደመነሳት ብሎ እጅ ነስቶ በሁለት እጅ ተቀብሎ ሲያበቃ የመለኪያዋን ከንፈር በፍቅር የሚስም ይመስል በዝግታ በጥቂቱ ሳበ፣ አይኑን ጨፍኖ ሲከተላት አረቄዋ አፉን ሙቀት ሞላች፤ በጉሮሮው ዘመተች፣ ወደ ቆላ ወረደች፡፡

"እሰይ! እዚህ ደረሰች" አለ ሆዱን በመዳፉ እያሻሸ፡፡ ቀና ብሎ አያቸው ሳቅ ሳቅ በሚለው ፊቱ፡፡

"ሙቀት! ሙቀት! ሙቀት!" አሉት እትዬ አልታዬ፡፡ ወርቅ ጥርሳቸው ያረቄውን ነበልባል መልሶ የሚወረውር ይመስል አንፀባረቀ፡፡

"ያረቄና ያንቱ ፍቅር ሙቀት!" አላቸው፡፡ ሁለቱ ሁሌ እንደተቃለዱ፡፡

"አይ አንተ! የዛሬ ሰላሳ ዓመት ተገኝተህ በሆነ" አሉት፡፡

"ያኔማ አይመችም ነበር፡፡ የለሁም ነበር" አላቸው፡፡

"እሱ ላይ ነው ጉዱ የኸውልህ፡፡ እኔ ደሞ አሁን የለሁም፡፡" ፊገግታቸው ላይ መሸ፡፡ ወርቅ ጥርሳቸው እንደ ማታ ጸሐይ ተደበቀ፡፡ እርጅናቸው ሲጨልምባቸው ታየ፡፡

ኀረምሳው ብድግ ብሎ ትከሻቸው እያቀፈ ካንገት በላይ እየቀለደ "ሰማህ ልጅ ጥላዬ፣ እትዬ አልታዬ እዚህ የሉም፡፡ ፖሊስ የጠየቀህ እንደሆነ እትዬ አልታዬን አላየንም በል፡፡"

አግድሙ ወንበር ላይ አጠገቡ እያስቀመጣቸው፣ መለኪያውን አንስቶ ፉት እያስደረጋቸው፣ "መለኪያዬን ከማጋራት በላይ ምን የፍቅር ምልክት አለ?" አላቸው፡፡

እትዬ አልታዬ ሊናገሩ ሲሉ ባለሬሳ ሳጥኑ የግራ ጎረቤታቸው ከተፍ፡፡ ሰካራም፡፡ ትልልቅ ዓይኖቹ በስካር ልማድ ቀይ ሆነው ቀርተዋል፡፡ ስሙ ገላጋይ ተስፋዬ ሲሆን የኩላሊት ሰፈር ሰዎች ገላጋይ በርበሬ ይሉታል፡፡ "ና ዚህ ገላጋይ" አሉት እትዬ አልታዬ "ኧረ ስምህን ለውጥ፡፡ የሬሳ ሳጥን እየሸጥክ ገላጋይ መባል ደሞ ምን ፈሊጥ ነው? እኛ መገላገል ፈልገናል አልንህንዴ፡፡ ኧረዲያ"

አዛለች ወዝዋዜ እንደ ዘንባባ እየተወዛወዘች ሄዳ እየተወዛወዘች ተመልሳ ሳትወዛወዝ አረቂውን ስትሰጠው በፈዛዛ በርበሬዎቹ ሲከተላት ቆይቶ በስማብ ለማለት እንኳ ያህል ጊዜ ሳይወስድ ኸው አድርጎ ወዳፉ ወረወራት አረቂዋን፡፡ ጉሮሮውን አቃጥላ ስትወርድ አይኑን ጨፈነ፡፡ ፊቱን አኮማተረ፡፡

"ቀስ ብለህ ጠጣ ትሰክራለህ፡፡ ሬሳ መሰለው?" አሉት እትዬ አልታዬ፡፡

አዛለች ሁለተኛውን ስትቀዳለት፣ ጥላዬ፣ "ታዲያስ ገበያ እንዴት ነው?" አለው ገላጋይን፡፡

"ይህን ሰሞንማ ስምንተኛው ሺ መድረሱ ነው መሰለኝ ሰው መሞት እየተወ ሄዷል፡፡"

"ምናባህ ታየኛለህ?" አሉት እትዬ አልታዬ፣ "እኔ እንደሆንኩ አልሞትልህ፡፡ ደሞ ብሞትም በሳጥን አልቀበር፡፡ እኔ አልታዬወርቅ አፈር ፈርቼ ነው ወይስ ተጠይፌ ነው ሳጥን ውስጥ እምታፈን? አልታዬ ማን እንደሆነች ባታውቅ ነው ልጄ፡፡ ሰሌኔን ለብሼ ነው ምተኛው ልንገርህ"

"እኔማ ሰሌንም መሸጥ ልጀምር ወይ እያልኩ አስባለሁ፡፡" ከት ብለው ሳቁ እትዬ አልታዬ፤ ወርቅ ጥርሳቸው ቦግ ብሎ ታየ፡፡ … እንግዲህስ ያ ወርቅ ጥርሳቸው ሊያሸንፋቸው ምንም አልቀረው፡፡ ድሮ ድሮ የበሰሉ የሞሉ ጋለሞታ ሳሉ ነበር ይህን ወርቅ ከጥርሳቸው መሃል ያስተከሉ፡፡ እንዲያጌጣቸው ነበር ሐሳባቸውማ፡፡ አሁን ግን ይበልጣቸው ይከልላቸው ጀመረ፣ ከውበታቸው ቀድሞ ጎልቶ እየታየ፡፡ ምናባቱንሳና፤ ይህን ወርቅ አውጥተው ወዲያ ቢጥሉት፡፡ ከጣሉትማ ተረታሁ ታነፍኩ ማለት ይሆንባቸዋል፡፡ አላወልቀውም ይሁን፤ እኔ አልታዬ ነኝ በወርቅ ምሸነፍ?

አልታዬ ሳሉም በወርቅ አልተሸነፉ በፍቅር ነው እንጂ፡፡ እትዬ አልታዬ ሳሉም ለወርቅ ብለው አልተወሰዱ ለአምሮታቸው ብለው ነው አንጂ፡፡ እና አሁን ካረጁ በኋላ ለወርቅ

ሊሸነፉለት? ለዚህ ለብጫ ድንጋይ? ባይሆን ለዚህ ለወጣት ይሸነፉለታል እንጂ፡፡ ውስጡን ሳቅ አሉ፡፡ ቢወልዱ ኖሮ እንደሱ ያለ ሳቅ ሳቅ የሚለውን ነበር የሚወልዱ፡፡ ትዝ አላቸው ቅድም ገላጋይ ሳይመጣ አዝኖላቸው ተነስቶ ሲያቅፋቸው፡፡

ወደሱ ዘወር እያሉ ያስለመዱትን ቀልድ እየጀመሩ፣

"ብርሽ ብሪትሽ!" አሉት፡፡

"የስ ላቭ" አላቸው፡፡

"ይኸ ገላጋይ ሰው እንዳይመስልህ"

"ምን አረግኩ?" አለ በርበሬው፣ አዛለች እየተወዛወዘች ስትሄድ በርበሬዎቹ እተከተለ፡፡

"ምን አረግኩ? አሁንስ የሌባ አይነ ደረቅ ሆንክብኝ፡፡ አላውቅብህ መሰለህ? በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች ደህና ለብሰው ሲያልፉ ስታይ በዓይንህ ስትከተላቸው ስትጎመጃቸው አላይህ መሰለህ?"

"አንተ ሟርተኛ! ደሞ እንደሱ አትየኝ ብዬሃለሁ፣ ዋ!" የስካርም የጨዋታም ሲስቁ ብርሃኑ ፊት ላይ ፍርሃት ብቅ ሲል አይተው አዘኑለትና ወደሱ ዘወር ብለው በዚያ በርህሩህ ገፃቸው አይዞህ እያሉት፣

"ብርሽ ብርዬ ብርጭቆ ብርሌ!" አሉት፡፡

"ወይዬ አልታይዬ!" አላቸው፣ ብቅ ብሎ የነበረው ፍርሃት ተመልሶ ሲሰጥም እየተሰማው፡፡

"እርጅና ምን እንደሆነ ልንገርህ?"

"ምንድን ነው?"

"አይን መክፈት ነው፡፡ ያ በልጅነት ችኮላ ነፉስና በጉርምስና ፍላት ትኩሳት ይሰማን የነበረው ፍርሃት ስጋት ብስጭት ኀዘን፣ ያ ሁሉ ብድግ ፍረጥ፤ ያ ሁሉ ተስፋ ያስቆርጥ አንጀት የበላ ደም እንባ ያስለቅስ የነበረው ጭንቀት ለካስ ያልነበረ ኖሯል፡፡ ያ ሁሉ መረበሽ መሸበር ከንቱ ሁከት ኖሯል፡፡ ትንሽ ልጅ በጭለማ የሚሰማው የጅብ ጩኸት

ኖሯል፡፡ ከንቱ ጋጋታ፡፡ ከንቱ!" አሉና መለኪያቸውን ብድግ አርገው ግልብጥ አደረጉት፡

(አምስት ስድስት ሰባት እና ሌሎች፣ ስብአት ገ/እግዚአብሔር)

## ክፍል ሁለት፡- ድህረ ትምህርት ጥያቄ

**ተግባር አንድ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆኑ"እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. ብርሃኑና ጥላዬ ጓደኛሞች ናቸው፡፡
2. የእትዬ አልታዬ ቤት የኩላሊት በሽተኞች መገናኛ ነው፡፡
3. የእትዬ አልታዬ ቤት ሳቅና ጨዋታ ይበዛዋል፡፡
4. ገላጋይ የእትዬ አልታዬ የቀኝ ጎረቤት ነው፡፡
5. አዛለች ጥርሷ ላይ ወርቅ ያስተከለችው በወጣትነቷነው፡፡

**ተግባር ሁለት፡-ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. "ከንቱ ጋጋታ፡፡ ከንቱ!" በማለት መለኪያቸውን ብድግ አድርገው የገለበጡት ማን ናቸው?
   ሀ. ብርሃኑ ለ. ጥላዬ ሐ. እትዬ አልታዬ መ. አቶ ገላጋይ
2. "ዓይን መክፈት ነው፡፡" የተባለው ምንድን ነው?
   ሀ. እርጅና ለ. ወጣትነት ሐ. ጎልማሳነት መ. ሲነጋ
3. "አንተ ሟርተኛ!" የተባለው ማን ነው?
   ሀ. ጥላዬ ለ. ገላጋይ ሐ. ብርሃኑ መ. አዛለች
4. እትዬ አልታዬ የተሸነፉት በ ---------------------- ነው፡፡
   ሀ. ወርቅ ለ. ገንዘብ ሐ. መጠጥ መ. ፍቅር
5. "እትዬ አልታዬ እኔ እንደው አልሞትልህ" ያሉት ለምንድን ነው?
   ሀ. ወጣት ስለሆኑ ለ. ጤነኛ ስለሆኑ
   ሐ. ገላጋይ ስላያቸው መ. ሀብታም ስለሆኑ
6. "ይህን ሰሞን ስምንተኛው ሺ መድረሱ ነው መሰለኝ" ያለው ለምንድን ነው?
   ሀ. ሰው ባለመሞቱ ለ. ሰው በመሞቱ

ሐ. ሀጥያት በመብዛቱ     መ. ግፍ በመብዛቱ

7. ጉሮሮውን አቃጥሎ ያለፈው ምንድን ነው?

ሀ. በርበሬ     ለ. ሚጥሚጣ     ሐ. አረቄ     መ. ትንታ

8. የገላጋይ ዓይኖች ቀልተው የቀሩት በምን ምክንያት ነው?

ሀ. በንዴት     ለ. በስካር     ሐ. በቅናት     መ. በህመም

9. የእትዬ አልታዬ የግራ ጎረቤት ላይ የተፃፈው አስተያየት ምንድን ነው?

ሀ. እድሜ ቀጥል ጣፋጭ ክትፎ ቤት     ለ. ስለ ቢክ እስኪርብቶ

ሐ. ስለ ጥቁር የሬሳ ሳጥን     መ. አስተያየት አናደርጋለን

10. እትዬ አልታዬ የእትዬነቱን ዘመን የትና የት ጥለውት ሄደዋል፡፡ የሚለውን ዓረፍተ ነገር በፍቺ ሊተካው የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. እትዬ አልታዬ ዘመኑን በአስተሳሰብ በልጠውታል፡፡

ለ. እትዬ አልታዬ አርጅተዋል

ሐ. ክብራቸውን አጥተዋል

መ. ሞተዋል

**ተግባር ሶስት፦ ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ"ሀ"ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ መምረጥ አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 11. ከንቱ ጋጋታ | ሀ. ጭልጥ |
| 12. መሸበር | ለ. ሞት ጠሪ |
| 13. ሲሰጥም | ሐ. አዛኝ |
| 14. ሟርተኛ | መ. ረብሻ |
| 15. ርህሩህ | ሠ. ስትመኛቸው |
| 16. ስትጎመጃቸው | ረ. ከዘንባባ የሚሰራ ምንጣፍ መሰል |
| 17. አንጀት ይበላል | ሰ. ማለያየት |
| 18. ሰሌን | ሸ. ሲጠፋ |
| 19. ማጋራት | ቀ. ማመስገን |
| 20. መገላገል | በ. ማካፈል |
| 21. እጅ መንሳት | ተ. ያሳዝናል |

22. ሁከት ቸ. መረበሽ

23. ግልብጥ ኀ. የማይጠቅም አጀብ

**ተግባር አራት፦ ምንባቡን መሰረት ማድረግ ከዚህ በታች በንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በመምረጥ ባዶ ቦታውን ሙሉት፡፡**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አሳጥረን | ከመሬት | ፈገግታቸው | የሁከት | ኸው | የተሟላ ዕለት |
| ጎረምሶች | በዘልማድ | ውሃው | ተንከለኛ | ወዲያ | በመጻፍ |

1. ብርሃኑና ጥላዬ ከወደ------------------ ለማለትና ለመዝናናት ወደ እትዬ አልታዬ ቤት ሄዱ
2. "እንጠጦ ላይ ሆኖ ይታያል ኩላሊት የትዬ አልታዬ ቤት------------------- መድኃኒት፡፡"
3. "እዚች ክትፎ በልተን፣ ዕድሜያችንን-----------------ወደዚያ መደብር ገብተን የሬሳ ሳጥናችንን መርጠን አዘን፣…"
4. ጥላዬ "ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ----------------እንዳሉ አባቶች" አለ፡፡
5. ሁለቱ --------------- በዚህ እየሳቁ እትዬ አልታዬ ቤት ገቡ፡፡
6. እንዲሁ ----------------- እትዬ እየተባሉ
7. ሞት ይህ ክፉ ---------------- ድመት፣ አይጥ ሆነው ቢጠሩት ቢጠሩት አይል አቤት…
8. የእትዬ አልታዬ ----------------- ሲታይ ልብ ይሰውራል፡፡
9. "እሰይ! እዚህ ደረሰች" አለ ሆዱን -------------------- እያሻሸ፡፡
10. በስማብ ለማለት እንኳ ያህል ጊዜ ሳይወስድ -------------- አድርጎ ወዳፉ ወረወራት አረቄዋን፡፡
11. እንዳጋጣሚ ቀኑ ------------------ ጊዜና ገንዘብ ዕኩል የተገኘ ዕለት፡፡ የፈቀዱ ዕለት ለመጫወት መጠጥ ቤት ሄዱ፡፡
12. ይህን ወርቅ አውጥተው ------------------- ቢጥሉት፡፡

አባሪ ስምንት

በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ 0-2 አፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽኦ/ሚና ለመፈተሽ ለሚደረግ ጥናታዊ ፅሁፍ ለሰባተኛ ክፍል ለቁጥጥር እና ለሙከራ ቡደን የቀረበ ቅድመ ልምምድ ፈተና፡፡

## አምስት ስድስት ሰባት

የዛሬን አያድርገዉና፣ አቶ በርሱፍቃድ በጉርምስናቸዉ ዘመን የሶስት ሰዉ ምሳ አይመልሳቸዉም ነበር፡፡ ሲያርሱም ያንኑ ያህል ነበር፡፡ ግዙፍ ደንደሳም በመሆናቸዉ ሁለት ሰዉ ታግሎ አይጥላቸዉም ነበር፡፡

ጎጆ ከወጡ በኋላ ፈጣሪ ድህነትና ፍሬን አጣምሮ ሰጣቸዉ፤ አምስት ልጅ ወለዱ፡፡ ሚስታቸዉ በተፈጥሮ ለስላሳ ደካማ በመሆናቸዉ፤ አምስተኛዋን ልጅ ከወለዱ በኋላ በሽታ አደረባቸዉ፤ ለጉልጓሎ ለአረም ለአጨዳ መዉጣት አቃታቸዉ፤ ዉሃ መቅዳትና ወፍጮም እያሸነፋቸዉ ስለሄደ የመጀመሪያዋ ልጃቸዉ ፋናዬ በስምንት አመትዋ በገንቦ ዉሀ መቅዳት፤ በልጅ አቅምዋ እህል መፍጨት ግድ ሆነባት፡፡ በናትዋ የወጣች ልስልስ ነገር፤ ከእንዝርትና ከወስፌ የከበደ ማንሳት የማትችል ሰንበሌጥ መሳይ ነ፤ በዚያ ላይ እስክትጠግብ አትበላም፡፡ በምን ጉልበትዋ ትቻለዉ ዉሃዉን ወፍጮዉን እንጨት ለቀማዉን ?

በእህል እጦትም በሴት ጉልበት እጦትም ቤተሰቡ አብዛኛዉን ጊዜ ቆሎ ወይም ንፍሮ ብቻ ይበላል፡፡ ቢቸግራቸዉ አቶ በርሱፍቃድ ወንድ ልጅ የማይሰራዉን ሰሩ፤ ሌሊት እየተነሱ እህል መፍጨት ጀመሩ፡፡ ሲያስቡት፣ እጄም ወገቤም ሞፈር ለምዷልና ከእፍረቱ በስተቀር ወፍጮ ምንም አያስቸግርም መስሏቸዉ ነበር፡፡ አልሆነም፤ እንዳሰቡት አልሆነም፡፡ መዳፋቸዉም ወገባቸዉም ስላልቻለ ጥቂት ፈጭተዉ ተመልሰዉ ተኙ፡፡ ግን የማይለመድ የለም፤ ወፍጮዉን ለመዱት፡፡ በበአል ቀን እየወጡ እንጨት ለቅመዉ በማታ ጨለማ እያመጡ ፋናዬን ከእንጨት ለቀማዉም አሳረፉዋት እንጂ እስካሁን ሞታ ነበር፡፡

አርብ እለት ማለዳ ተነስተዉ ሞፈር ቀምበራቸዉን ተሸክመዉ የቀራቸዉን አንድ በሬና የጎረቤታቸዉን የወይዘሮ ሹምነሽን በሬ እየነዱ ወደ ወይዘሮ ሹምነሽ እርሻ

ሄደዉ ጠመዱ፡፡ አንድ ቀን የወይዘሮ ሹምነሽን መሬት፣ ሁለት ቀን የራሳቸዉን መሬት ነዉ የሚያርሱት፡፡ ይህን በሚዋዋሉበት ጊዜ አቶ በርሱፍቃድ፡

‹‹አንዱ በሬ የኔ፣ ጉልበቱ የኔ፣ ሞፈር ቀምበሩ የኔ፣ ታዲያ አልተጎዳሁም?›› ቢሉዋቸዉ፣ ወ/ሮ ሹምነሽ መልሰዉ እንዲህ አሉ፣

‹‹አዬ! እንዲህ ከብት ባለቀበት ጊዜ ይህን አግኝተዉ ተጎዳሁ ይላሉ? አሁን ለልጆችዎና ለጉርብትናዎ ብዬ ነዉ እንጂ አንድ ቀን ለኔ አንድ ቀን ለራሱ የሚያርስ አጣለሁ? እንግዲያዉስ ሁለት ቀን ለኔ አንድ ቀን ላንተ ብለዉ እጅ ነስቶ የሚቀበለኝ አጣለሁ? ለዚህ ነዉ እንጂ እርስዎ ከሚመጡብኝ እኔ እመጣብዎት አልነበረም?››

አቶ በርሱፍቃድ አንገታቸዉን ደፉ፣

‹‹እሱስ ነዉ›› አሉ፣ ‹‹እርስዎ አራት ጥማድ በሬ እያሳረሱ እንደኔ አልተቸገሩምና ማለቴ ነዉ እንጂ፡፡››

‹‹አዬ አያ በርሱፍቃድ! እርስዎም እንዲህ ይላሉ? ባሌ ከሞተ ወዲህ ልጅ የለኝ ምን የለኝ፡፡ ብቻዬን ባዶ ቤት ዉስጥ ጥቅልል ብዬ እየተኛሁ፣አልተቸገርሽም ይሉኛል? አሁን እትዬ ዝማም እርስዎ ቢኖሩዋቸዉ ፋናዬ ብትኖራቸዉ ቤት ይዉላሉ እንጂ እንደኔ ብቻቸዉን ቢሆኑ ምን ይዉጣቸዉ ኖሯል? ብታመም እንኳ ዉሀ የሚያጠጣን የለኝ፡፡››

‹‹ምነዉ እኔ አምስት ልጅ አለኝ፡፡ አንዱን አይወስዱም? ››

‹‹እዚያ ቆላ ያለዉ ያጎቴ ልጅ ከፍቶት ልጄን እንድታሳድጊያት ልልክልሽ ነዉ ብሎ ልኮብኛል እንጂ ቀደም ብለዉ ቢነግሩኝማ ይሆን ነበር፡፡››

አይ እፍረት! አይ ኩምታ! አቶ በርሱፍቃድ አሁንም አንገታቸዉን ደፉ፡፡ …

ያቺን ሰዓት እያስታወሱ ‹‹ወይዘሮ ሹምነሽ በሬዬን አልሰጥም ቢሉ ኖሮ ወይም አስቀድመዉ ከሌላ ሰዉ ተዋዉለዉ ቢሆን ኖሮ ምን እሆን ነበር? እጄን አጣምሬ ቁጭ? ሞት መጥቶ ልጆቼን ሚስቴንም እኔንም አንድ በአንድ እስኪበላን ቁጭ? በስመአብ ወወልድ!›› ይህን እያሰቡ ሲያርሱ፣ በባዶ ሆድ ላይ ሀሳብ ስራቸዉን አስረስቷቸዉ እርፉን በቅጡ ሳይጨብጡ ቀርተዉ ኖሮ ማረሻዉ የበሬዉን ሰኮና

ወጋባቸዉ፡፡ ደሙን ሲያዩ አዘኑለት፡ አቅፈዉ ሊያባብሉት አሰኛቸዉ በሬዉን-በንዴት ገረፉት በጅራፋቸዉ - የባሰዉን አሳዘናቸዉ ያ የሚወዱት በሬያቸዉ የስራ ጓደኛቸዉ የፀሐይ ቃጠሎን የሚጋሩቸዉ አርሶ የሚያበላቸዉ የመጨረሻ ተስፋቸዉ ጅራፍ ሲያወርዱበት ትዕግስቱ እማያልቅበት፡፡

‹‹ሆድ ብሶኝ ነዉ ጨንቆኝ ነዉ ርቦኝ ነዉ አትቀየመኝ ሲሳይ ወዳጄ፣ የመጨረሻ ወዳጄ›› ባሉት፣ የበሬ ቋንቋ ባወቁና የልባቸዉን በነገሩት፡፡ ይኸ የስሜትና የሀሳብ ጎርፍ የጤና ስላልመሰላቸዉ ሌላ ፍርሀት ያዛቸዉ፡፡ ‹‹ያበድኩ እንደሆነ ወይ የታመምኩ እንደሆነ ልጆቼን ምን ይዉጣቸዋል? ልጆቼን፡ ኮሳሳ ልጆቼን፡ ፍሬዎቼን አጥንቶቼን፡ አጥንት ሆነዉ ቀሩ ልጆቼን! እግዚኦ መሀረነ

ክርስቶስ! አዉጣኝ፡፡ ከዚህ ጭንቅ ሰዉረኝ፡፡ ከልጆቼ መማቀቅ እግዚኦ ሞቴን ስጠኝና ልጆቼን አብላልኝ አንተ ፈጣሪ!››

ይኸ ሁሉ ነብሳቸዉን እያስጨነቀ እሳቸዉ የሲሳይን ሰኮና አንስተዉ አዩ፡፡ ክፉኛ ተወግቷል፡፡ ምናልባት ሳምንት ሙሉ ሊያርስ አይችልም ይሆናል፡፡ በሬዎቹን ፈቱ፣ እርፍና ሞፈሩን ተሸክመዉ ወደ ቤት ሄዱ፡፡

ከቤታቸዉ ኋላ ያለዉ ዋንዛ ስር ሁለተኛዉ ልጃቸዉ ወርቁ ቁጭ ብሏል፡፡ ከአምስት ዓመት በፊት ሶስት ጥማድ በሬ በነበራቸዉ ዘመን በጥጋብ ዓመት ሲወለድ ድቡልቡል ዱባ ልጅ ነበር፡፡ እሱማ እንዳባቱ ወፍራም ጉልበታም ብርቱ ሊሆን ነበር የተወለደዉ - ድህነት ቤታቸዉ ገብታ፣ ከስድስት አምስቱን በሬ ጨርሳ፣ አስራ ስድስቱንም በጎቻቸዉን አንድ ባንድ አስሸጣ፣ ቀስ በቀስ ሁሉን ነገር ዉጣ፣ ይኸዉ ወርቁን ልጃቸዉን ሳይቀር ዉፍረቱን ደሙን ምጥጥ አድርጋ አጥንትና ዓይን ብቻ አስቀርታ ጉድ ሰራቻቸዉ እንጂ፡፡

ወርቁ መሬቱን በእንጨት እየጫረ በዝግታ ያለቅሳል፡፡

‹‹ምን ሆንክ?›› አሉት፡፡

‹‹እማማ ሹምነሽ ናቸዉ›› አለ፡፡

‹‹ምን አረጉህ ወይዘሮ ሹምነሽ?›› አሉት፡፡

‹‹ልላክህ፣ ከእማማ ወለተ ሃይማኖት ቤት ሰፌድ አምጣልኝ አሉኝ፡፡ እቺ ምራቅ

ሳትደርቅ ሮጠህ ያመጣህልኝ እንደሆነ እንጀራ በጨዉ እሰጥሀለሁ አሉኝ፡፡ ሮጬ አመጣሁላቸዉ ምራቋ ሳትደርቅ፡፡ ደርቃለች አሉና ከለከሉኝ፡፡ አልደረቀችም! ዉሸታቸዉን ነዉ አባብዬ፤ አልደረቀችም! እንጀራዬን ከለከሉኝ፡፡››

አቶ በርሱፍቃድ ከማዘናቸዉ የተነሳ ቆመዉ ቀሩ፡፡ በሆዳቸዉ ለፈጣሪ አቤት አሉ፡፡ ልጃቸዉ እንባቸዉን እንዳያይ ‹‹በል ተነስ ቤት ግባ›› አሉት፡፡ ተነስቶ ገባ፡፡

የተሸከሙትን አዉርደዉ በልጃቸዉ ቦታ ተተክተዉ ቁጭ ብለዉ አለቀሱ፡፡

‹‹የማበላቸዉን ከልክለህ ልጆች የሰጠኸኝ ምነዉ?›› አሉት ፈጣሪን፡፡

ህማማት፡-

አባ ወልደማርያም ንስሀ ሲሰሙ ዉለዉ ዘጠኝ ሰዓት አልፎ ህዝበ-ክርስቲያን ወደ የቤቱ ሲሄድ ወደ ኋላ ቀርተዉ ለብቻቸዉ ሲፀልዩ ሲሰግዱ ቆይተዉ ወደ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ቆሎ ለመቅመስ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተዉ በመቃብሩ በኩል ሲያልፉ አዩት ራቁቱን ባርኔጣ አድርጎ መቃብር ድንጋይ ላይ ወጥቶ ሲቆም፡፡ ፊቱ ወደዚያ ነዉ፡፡ ረዥም አርባ ቅልጥም ቀጭን እንደ ጅማት፡፡ እንደሚሰብክ መምህር እጆቹን ዘርግቶ በልዝብ ድምፅ እንዲህ አለ፤

‹‹አምስት ስድስት ሰባት! ስሙኝ፡፡ ስሙኝ እላንት ሙታን፤ ልንገራችሁ የማይነገር ለህያዋን፡፡ ከወዲያኛዉ አገር ሰይጣንን አይታችሁታል? አላያችሁትም፡፡ እዚህ ትታችሁት ሄዳችሁ እዚያ እንዴት ታገኙታላችሁ? እዚሁ ነዉ ከኛ ጋር ይኖራል፡፡ አምስት ስድስት ሰባት! ሰይጣን ማለት ጎተራ ነዉ፤ ስልቻ ነዉ፡፡ የማይሞላ ጉድ ነዉ፡፡ ሰይጣን ማለት ሆድ ነዉ፡፡

‹‹አምሰት ስድስት ሰባት፤ አምስት ልጅ ሁለት እናት አባት፡፡ ሰይጣን ከእባብ ተዋህዶ ሄዋንን አሳሳተ፤ አሳተ፡፡ ከእፀበለስ ተዋህዶ፤ ሄዋን ሆድ ገባ፡፡ ከሆድዋ ተዋህዶ ለልጆችዋ ተረፈ፡፡ ሰይጣን ሲኦል ወረደ ማለት ወደ ሆድ ወረደ ማለት ነዉ፡፡ ከዚያስ? ከዚያማ ጭለማ ዉስጥ ቁጭ ብሎ ይገዛን ያስሰግደን ጀመር አምስት ስድስት ሰባት! ቀኑን ሙሉ ስንስራ ስንለፋ ስንዋሽ ስናስመስል- ለምን? ለእንጀራ፡፡ ለማን? ለሰይጣን ሆድ፡፡ ሆድ ይኸ ሆድ ይኸ ጎተራ፤ ይኸ ጭለማ የሰይጣን ቤት መኖሪያ፡፡

ሰዉ ከተወለደ እስኪሞት ተራራ ያህል እህል ይበላ፡፡ አይሞላ ታዲያ ያ ሆዱ ያ ጉዱ፡፡ አይሞላም ሰይጣን ነዉ፡፡ ሆድ!ሆድ!ሆድ! ብሎ እየጮኽ ሆዱን በእጁ ደጋግሞ ሲፀፋዉ ተሰማቸዉ አባወልደማሪያም፡፡

‹‹አምስት ስድስት ሰባት! አምስት ልጅ፤ ስድስት እናት፤ ሰባት አባት፡፡ እንግዲህ ሰሞኑን ስለ ክርስቶስ ስቅለት ትሰማላችሁ፡፡ ግን ማን ነዉ ሰዉ ሆኖ ያልተሰቀለ? ማነዉ በልጁ ለቅሶ ያልተቸነከረ? ማነዉ በሚስቱ ሞት ያልተቀበረ? ደጋግሞ ሊነሳ ደጋግሞ ያልተቀበረ ማነዉ? አምስት ስድስት ሰባት! እሳት፡፡ ገሀነም ትገባላችሁ ብለዉ ያስፈራሩናል፡፡ የት ነዉ ያለነዉና ነዉ? ገሀነምአይደለም?!‰ረተዉኤድያ! ›› ብሎ ዞረ፡፡ዓይኖቹ በእብደት ደንግጠዉ እንደደነገጡ ቀርተዋል፡፡ ያስደነግጣሉ፡፡ እብዱ አባ ወልደማሪያምን አያቸዉና ከድንጋዩ ወርዶ ወደሳቸዉ መጣ፡፡ ቀጭን አጥንታም ረኽርም ነዉ፡፡ ለሁለት ቢታጠፍ እሳቸዉን ያህላል፡፡

‹‹ሰላም ለከ፡፡ ህማማት ነዉና የይሁዳን ታሪክ ልንገርህ›› አላቸዉ ‹‹አምስት ስድስት ሰባት!

‹‹ሰማይን አንጋጠዉ ቢያዩት ደመና አጥቶ ራቁቱን ቀረና፤ በፀሎት ቢጨምቁት ጠብ አልል አለና፤ ምድር ጓጉታ ተነቃቅታ ደርቃ ቀረችና፤ የይሁዳም በሬዎች አንድ በአንድ ከዱትና፤ ታማኙ አልሞት ባዩ ጀግናዉ ሲሳይ ብቻ ቀረ፡፡ ቀንበር ሊሸከም ሞፈር ሊጎትት አብሮት ሊሰራ እስከመጨረሻ፡፡ አምስት ስድስት ሰባት! ይሁዳ ግን ሰዉ ነዉና፤ ከሀዲ ነዉና፤ በሬዉን ሊሸጠዉ ተነሳ፡፡ ገገር ታጣ፡፡ እንግዲያዉ ና ሲሳይ የመጨረሻ ወዳጄ ዘመዴ፤ ወደ ጓሮ እንሂድ ልንገርህ ለብቻህ አለና ወሰደዉ፡፡ አምስት ስድስት ሰባት! በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! አለና የመጨረሻይቱን ምስጢር በስለት ነገረዉ፡፡ እርድ! በሬዉ ከማዘኑ የተነሳ ምንም አላለ፡፡ በዝምታ ነብሱን ሰጠ፡፡ ፀሀይ ይህን አይታ በእፍረት ፊትዋን ልትሸሽግ ዘወር ብትል ደመና አጣች፤ ደም አለቀሰች፡፡

‹‹አረድኩት፤ ገፈፍኩት፤ ብልቱን አወጣሁት፡፡ ጠብሰን ቀቅለን በላነዉ ሲሳይን የመጨረሻ ወዳጃችንን፡፡ ወጥ እንዳይሆን እንጀራ የለን፤ ቋንጣ እንዳይሆን ቶሎ ጨረስነዉ፡፡ በላሁት ሲሳይን ዘመዴን፡፡ ለሆድ ለሰይጣን ሰዋሁት፡፡

‹‹ታዲያ ይሁዳ ከዳተኛ ነዉ ይላሉ፡፡ የኔን ታሪክ ያላወቁ፡፡ ይሁዳ እንኳ ተፀፀተ

ዕዳዉን ከፈለ፡፡ እኔ ግን! እኔ ግን!›› ብሎ ራሱን ይዞ ጮኸ፡፡ ‹‹ወየዉ ወየዉ ወየዉ! ወይኔ ዘመዴን ወይኔ ወዳጄን ወይኔ ሲሳዬን ወይኔ ወይኔ!›› እያለ እየተወዛወዘ የመርዶ የቀብር ለቅሶ አለቀሰ፡፡ ከዚያ ለቅሶዉን ድንገት አቋርጦ ካጠገባቸዉ ትልቅ ድንጋይ አነሳ፡፡ ተንበረከከ፡፡ ድንጋዩን ትከሻዉ ላይ አኖረ፡፡

‹‹ማረኝ አንተ የዳዊት ልጅ፣ ይቅር በለኝ አባ›› አላቸዉ

‹‹እግዚአብሄር ይቅር ይበልህ፡፡››

‹‹ አልፈልግም የሱን ይቅርታ!›› ብሎ ተነስቶ በንዴት ድንጋዩን ወደዛ ወረወረዉ፡፡ ‹‹የተበደለ ምን ይቅርታ ያስፈልገዋል? ሰዉ በመሆንዎ ይቅርታ ለመንኩ እንጂ ፈጣሪን ይቅርታ እለምናለሁ? እሱማ ሊከሰስ ይገባዋል›› ብሎ እጆቹን አንስቶ ለሙታን መናገር ጀመረ እብዱ ሰዉዬ፡፡

‹‹አምስት ስድስት ሰባት ! ንገሩልኝ ታገኙት እንደሆን፡፡ አበላቸዉ እህል ከልክለህ አምስት ልጆች የሰጠኸኝ ምነዉ? ብሎሃል በሉት፡፡ አምስት ልጅ ተሰብስቦ አብሮ ሲዉል አንዲት ሳቅ ብቅ ሳትል ቀኑ መምሸቱ ምነዉ? ብሎሃል በሉት፡፡ ልጆቼ አንዲት ቀን እንኳ ኩኩሉ ሳይጫወቱ ማለቃቸዉ ምነዉ? ሚስቴንም ልጆቼንም አንድ በአንድ ስቀብር ዝም ብለህ ማየትህ ምነዉ? ብሎሃል በሉት፡፡ የፍርድ ቀን ቢመጣ የሚፈረድበት ማነዉ? ብሎሃል በርሱፍቃድ በሉት፡፡ አምስት ስድስት ሰባት! የፍርድ ቀን ቢመጣ ››

ልስልስ ባለ ሩኅሩኅ ድምፅ ‹‹ምነዉ አለቀሱ አባ?›› ሲላቸዉ ዓይናቸዉን ከፈቱ፡፡ በነገሩ ምሬት በስቃዩ ብዛት ዓይናቸዉን ዘግተዉ ሲያዝኑ ቆይተዋል፡፡ ሲያዩት ጊዜ ላዩ የነበረዉ የእብደት ድንጋጤ የለም፡፡ ስቃይ ሀዘን ነዉ መላ ፊቱ ሲያዩት፡፡ አንጀት የሚበላ ስቃይ ሀዘን፡፡

‹‹ምን ሆኑ አባ?›› አላቸዉ አዝኖላቸዉ፡፡ ፊቱ ላይ የሰፈረዉ ሀዘን ፊታቸዉ ላይም ታይቶት ይሆን?

‹‹ምንም አልሆንኩም ልጄ፣ ምንም አልሆንኩም፡፡ ደህና ነኝ›› እያሉ እንባቸዉን ጠረጉ፡፡ ማልቀሳቸዉን አላወቁም ነበር፡፡

‹‹ለኔ ነዉ ያለቀሱልኝ?››

‹‹ አዎን ልጄ፤ እዉነትም ተሰቅለሃል፡፡ ግን አብሮት የተሰቀለ በቀኙ ይቀመጣል፤አይዞህ፡፡››

ድንገት ቁጭ አለና ጉልበቱን አቅፎ ራሱን ደፋ፡፡ ተንበረከኩ አጠገቡ፡፡ ‹‹ምን ሆንክ ልጄ?››

‹‹እርቃነ ስጋዬን፡፡ አጠገብዎ ቆሜ፡፡ ይቅርታ አባ፡፡ ይለፉ ይሂዱ፡፡››

አባ ተነሱ፡፡ አርባ ጊዜ የተጣፈ ቡትቶ ካባቸዉን አዉልቀዉ አለበሱት፡፡

አይዞህ ልጄ፡፡ ከልብሱ ስር ሁላችንም እርቃነ ስጋችንን ነን፡፡ በል ተነስ እንሂድ››

ጥቂት እርምጃ እንደሄዱ ‹‹ትንሽ አረፍ እንበል፤አባ? የፀሐይዋ ሙቀት ደስ ይላል›› አላቸዉ፡፡ ስፍራዉ ግን የምሽት ጥላ ሰፍኖበታል፡፡

‹‹እስቲ እዚች አጋድሙኝ፡፡ እንደሱ! አይ አባ! እንዴት ደግ ነዎት! ለመሆኑ ሰዉ ነዎት? ዓይኑን ዘጋ፡፡ ‹‹….. ይግቡ እንጂ፡፡ ‰ረ ይግቡ! ቤት ለንግዳ›› አለ ዐይኑን እንደዘጋ ‹‹ፋናዬ፡ ንሺ ዉሀ ለእግር አምጪ፡፡ አባ ደክሟቸዋል ከሩቅ ነዉ የመጣነዉ፡፡›› ዓይኑን ከፈተ፡፡ ‹‹ወርቁ! ‰ረ ወርቁ!! ሲጠሩህ አትሰማም? ከብቶቹ ሁሉ ገብተዋል? ለነሲሳይ ጭድ ሰጠሃቸዉ? ጎሽ የኔ አንበሳ፡፡ ና በል ያባን ጉልበት ሳም፡፡ መርቁኝ በላቸዉ፡፡ እናትህን ጠላ መሳይ አምጪልን በላት … ወርቁ! በቃ ጫጫታ፣ ግቡ ጨልሟል በላቸዉ ልጆቹን … ህልም ይፈታሉ አባ? ‰ረ የገብርኤል ያለህ! ምንኛ ክፉ ህልም አሳየኝ!? ረሀብ ገብቶ ያለኝን ጨርሼ፤ ሁሉ ሞቶ ብቻዬን ቀርቼ… ረሀብ መቸስ ጥጋብ ማለት ነዉ፡፡ ሰዉ ሲሞት ደስ ይለዋል ማለት ነዉ… ግን እርስዎ ምን ይመስልዎታል እንዲህ ዓይነት ህልም…ህልም… ህልም…›› ሰዉየዉ በዚያዉ ቀረ፡፡

በርሱፍቃድ አለፈለት፤ አለፈ፡፡

*መመሪያ አንድ፡-* <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በአጭሩ ግለፁ</u>፡፡

፩. የአቶ በርሱ ፍቃድ ባለቤት ጠንካራና ጤነኛ ናቸው፡፡

----------------------------------------------------------------------------

፪. ፋናዬ በስምንት አመቷ በገንቦ ውሃ ትቀዳ፤ በልጅ አቅሟ እህል የግዱን ትፈጭ ነበር፡፡

----------------------------------------------------------------------------

፫. አቶ በርሱ ፍቃድ አንድ ቀን የራሳቸውን ሁለት ቀን የወ/ሮ ሹምነሽን መሬት ነው የሚያርሱት፡፡

----------------------------------------------------------------------------

፬. አቶ ወልደ ማሪያም በርሱፍቃድን መቃብር ቦታ ያገኙት ቅዳሴ አለቀ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ሲወጡ ነው፡፡ -----------------------------------------------------------------

፭. የሲሳይን ሰኮና ማረሻው የወጋው አቶ በርሱፍቃድ ማረሻውን ከአፈሩ ለማላቀቅ ሲታገሉ ነው፡፡

----------------------------------------------------------------------------

<u>***መመሪያ ሁለት***</u>፦<u>*ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ*</u>፡፡

፩. በርሱፍቃድ ሲሳይን ወደ ጓሮ እንሂድ ልንገርህ ያለው ለምንድንነው?

ሀ. ሚስጥሩን ሊያጫውተው ለ. ችገሩን ለብቻው ሊነግረው

ሐ. የመጨረሻ ወዳጁን ሊያርደውመ. ሳር ሊያበላው

፪. የአባን ጉልበት እንዲስም የታዘዘው ማን ነው?

ሀ. ወርቄ ለ. ፋናዬ ሐ. ወ/ሮ ሹምነሽ መ. ሚስታቸው

፫. አቶ በርሱፍቃድ <u>**በጉርምስናቸው**</u> ዘመን የሶስት ሰው ምሳ አይመልሳቸውም ነበር፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍች_______ ነው፡፡

ሀ. በጉልምስና ለ. በህፃንነት ሐ. በሽምግልና መ. በወጣትነት

፬. "እንጨት ለቅመው በማታ ጨለማ እያመጡ ፋናዬን ከእንጨት ለቀማው አሳረፏት እነጂ እስካሁን ሞታ ነበር፡፡" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ "**ፋናዬ**" የሚለውቃል ፍቺ----- ነው፡፡

ሀ. ብርሃኔ ለ. የሴት ልጃቸው ስም ሐ. የወንድ ልጃቸው ስም መ. መሪዬን

፭. "አይ እፍረት! አይ ኩምታ! አቶ በርሱፍቃድ አሁንም አንገታቸውን ደፉ፡፡ ..." በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ "**ኩምታ**" የሚለው ቃል አገባባዊ ፍቺ ምንድነው?

ሀ. ጩኸት ለ. ሀዘን ለ. ድንጋጤ መ. ደስታ

፯. የአቶ በርሱፍቃድ ቤተሰብ አብዛኛውን ጊዜ ቆሎ ወይም ንፍሮ በልቶ የሚያድረው ለምንድነው?

ሀ. እህል ስለሌላቸው ለ. ለጤና ተስማሚ ስለሆነ

ሐ. ደሞዛቸው ትንሽ ስለሆነ መ. ምግብ መስራት ስለጠሉ

፰. የሲሳይ ጉዳት ለምን ያህል ቀን ከእርሻ ሊያስቀረው ይችላል?

ሀ. ለሁለት ቀን ለ. ለሁለት ሳምንት ሐ. ለወር መ. ለአንድ ሳምንት

፱. ወ/ሮ ሹምነሽ ወርቁ ምን እንዲያመጣላቸው ነው የላኩት?

ሀ. መሶብ ለ. ሰፌድ ሐ. አክንባሎ መ. ትሪ

፲. "ጭለማ ውስጥ ቁጭ ብሎ ይገዛን ያስገድደን ጀመር" የተባለው ማነው?

ሀ.ችግር ለ. ሰይጣን ሐ. ሆድ መ. ስራ

፲፩. "አምስት ስድስት ሰባት" የሚለው ርዕስ ማንን ይወክላል?

ሀ. ልጆችን ለ. ሚስትን ሐ. አባትን መ. ሁሉም መልስ ነው

፲፪. በርሱፍቃድ እንዳለፈለት የሚገልፀው ስንተኛው አንቀጽ ነው?

ሀ. የመጨረሻው ለ. የመጀመሪው ሐ. አስረኛው መ. ስደስተኛው

፲፫. <u>ግዙፍና ደንደሳም</u> በመሆናቸው ሁለት ሰው ታግሎ አይጥላቸውም ነበር፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍች፡፡

ሀ. ትልቅ ለ. በጣም ወፍራምና ረጅም ሐ. አጭር ወፍራም መ. ቦርጫም

፲፬. ቢቸግራቸው አቶ በርሱፍቃድ ወንድልጅ የማይሰራውን ሰሩ፡፡"**ቢቸግራቸው**" የሚለው ቃልን

ሊተካው የሚችለው የቱ አማራጭ ነው?

ሀ. ቢደኸዩ ለ. ምንም ባይኖራቸው ሐ. ግራ ቢገባቸው መ. ቢተርፋቸው

፲፭. <u>ጎጆ</u> ከወጡ በኋላ ፈጣሪ ድህነትና ፍሬን አጣምሮ ሰጣቸው፡፡ ለተሰመረበት ቃል አቻ ፍችው ምንድነው?

ሀ. ትዳር ለ. ከሳር የሚሰራ ቤት ሐ. መኖሪያ መ. ኑሮ

፲፫. "ውሃ መቅዳትና ወፍጮም እያሸነፋቸው ሄደ፡፡" የሚለውን ሀሳብ የሚገለፀው ምንድነው?

ሀ. እየደበደባቸው ለ. እየመራቸው ሐ. እየበለጣቸው መ. መስራት እያቃታቸው መሆኑን

መመሪ ሶስት፡-ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ"ሀ" አምድ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ"ለ" አምድ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ጠመዱ | ሀ. ንጋት |
| ፪. በሚዋዋሉበት | ለ. በሽታ አደረባቸው |
| ፫. ባለቀበት | ሐ. ደኸዩ |
| ፬. እጅ ነስቶ | መ. ማዘን፣ ማፈር |
| ፫. አንገት መድፋት | ሠ. እመጣቦት |
| ፮. ተቸገሩ | ረ. አመስግነው |
| ፯. ማለዳ | ሰ. በሞተበት |
| ፰. ታመሙ | ሸ. በሚስማሙበት |
| ፱. እጠይቆት | ቀ. አቀናጁ፣ አጣመሩ |
| ፲. አሺ አለ | ተ. ተቀበለ |
| | ቸ. ምሽት |
| | ኀ. ቆርጠ |

መመሪያ አራት፡-ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለተሰመረባቸው ቃላት አቻ ፍቺ የሚሆኑትን ከሰንጠረዡ በመምረጥ ተኩ፡፡

| ዘግተው | ተፀፀተ | ቢጨቀጭቁት | አጋድሙኝ | ለህያዋን |
|---|---|---|---|---|
| ያልተቸነከረ | ይቺ ምራቅ ሳትደርቅ | ጠላ መሳይ | ወፍጮ | ክፉ |

፩. ህልም ይፈታሉ አባ? ኧረ የገብረኤል ያለህ? ምንኛ መጥፎ ህልም አሳየኝ!

፪. እናትህን ቅራሬ አምጪልን በላት ወርቁ!

፫. እስቲ እዚች **አስተኙኝ**፡፡

፬. በነገሩ ምሬት በስቃዩ ብዛት ዓይናቸውን **ጨፍነው** ሲያዝኑ ቆይተዋል፡፡

፭. ይሁዳ እንኳን **ንስሀ ገባ** ዕዳውን ከፈለ፡፡

፮. በፀሎት **ቢነዘንዙት** ጠብ አልል አለ፡፡

፯. ማነው በልጁ ለቅሶ **ያልተሰቀለ**? ብሎ ጠየቀ፡፡

፰. **በቶሎ** ሮጠህ ያመጣህልኝ እንደሆነ እንጀራ በጨው እሰጥሃለሁ፡፡

፱. ስሙኝ እላንት ሙታን፤ ልንገራችሁ የማይነገር **በህይወት ላሉት**፡፡

፲. ከእፍረቱ በቀር **መጅ** ምንም አያስቸግርም መስሏቸው ነበር፡፡

**አባሪ ዘጠኝ**

ለቁጥጥር ቡድኑና ለሙከራ ቡድኑ የቀረበ ድህረ- ልምምድ ፈተና

## ሲጨልም

ወደ ሰባዎቹ የሚጠጉ የሚመስሉ አንድ አረጋዊ “ልጄ” አሉ አስተናጋጁን፤ “የገዛሁትን መድኃኒት ይገፍብህ መጣሁ፤ እባክህን የሰጠኸኝን ወስደህ…” አላስጨረሳቸውም፡፡

ግድግዳው ላይ ወደተለጠፈው ጽሑፍ አመለከታቸው

የተሸጠ መድኃኒት አይመለስም

አረጋዊው በለሰለሱ ቃላት መማፀን ያዙ፡፡ “ሰውዬ ዞር በል! ስራ ልስራበት! ለእንቶ ፈንቶ ጉዳይ የማባክነው ጊዜ የለኝም…” አለ ቁጣው እየተወለደ! “ዛሬ በዚህ ሰውዬ እንድጨቀጨቅ ተፈርዶብኛል ልበል?” “እባክህን ልጄአሳፋሪ ነገር ደርሶብኝ ነው፡፡ … ዘመድና ዕድር የሌለኝ ከርታታ ሽማግሌ ስለሆንኩ እንጂ…” አሉት ትሁት በሆነች ፈገግታ ሊያባብሉት እየሞከሩ፤ “ቅናሽ ዋጋ ብትከፍለኝም…” “ይሄ ሰውዬ ነካ ያደርገዋል ልበል?” አለና ሌሎች መድኃኒት ገዥዎችን ያስተናግድ ገባ፡፡ “ከያዙ አይለቁ” “ድህነት ቢፈትነኝ ነው ልጄ” አሉ፤ ያደፈና የነተበ ነጠላቸውን እያሳዩት፡፡ ነጠላው ከሰውነታቸው በከፋ ሁኔታ ያረጀ ኮታቸውን ደብቆላቸዋል፤ “አቅሜ የደከመ ባይሆን ኖሮ…” አሉት፤ ጫማ ካገኘ የከረመ እግራቸውን እያዩ፡፡አንዲት ተስተናጋጅ “አልመልስም ካለ አልመልስም ነው፡፡ ለምንድን ነው የሚነዘንዙት?” አለች በሚነጫነጭ ድምጽ፤ “ይሄኮ ፋርማሲ እንጂ አዛውንቶች የሚጦሩበት የድኩማን መርጃ ድርጅት

አይደለም" አነጋገሯን ያልወደደው የሚመስል ሌላኛው ጎልማሳ ደግሞ፤ "መድኃኒቱን ሙሉ በሙሉ የገዙት ከዚሁ መደብር ነው?" የሚል ጥያቄ አመጣ፡፡ "አዎ፤ ዶክተሩ ዕፎ በሰጠኝ መሠረት" ብለው መለሱለት፡፡ "ምን ያህል ፈጀብዎ?" "ሰባ ሁለት ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም፡፡ መድኃኒቱን ወስዶ ግማሹን እንኳን ቢሰጠኝ ምን አለበት?" አሉ በሃዘኔታ፤ "የሁለታችንንም የጋብቻ ቀለበት አስይዤ ነው ከማምነው ሰው የተበደርኩት" "መድኃኒቱን ለምን መመለስ ፈለጉ?" አሉ፤ ዘንቢል ያንጠለጠሉ አንዲት አሮጊት፡፡ በዚህ ጊዜ አስተናጋጁ ጣልቃ ገባ፤ "ባህላዊ ህክምና ብትከታተል ኪስ እንደማታራቁት ገብቷቸው ይሆናላ! ወይም ፀበል ሊያጠምቋት! ወይ…" "ኧረ ልጄ! ጉዳዩን ብታውቀው ኖሮ ያፌዝክበት ምላስህን ታፍርበት ነበር…" አሉ እንባ እየተናነቃቸው፡፡ "መድኃኒቱን ምን ላድርገው? ልዋጠው ወይስ ሽንት ቤት ልጨምረው?" "ለባለቤቴ ነው የምገዛላት ብለው አልነበር?...በጠና

ታማብኛለች፤ የዕድሜዬ ጀንበር አየጠለቀ ባለበት ሰዓት ለእህል ያላነሱና ለትምህርት ያልደረሱ ሦስት ልጆች በትናብኝ እንዳትሄድ ፀልይልኝ፤ ብለውኝ አልነበር?" "ማለቱንስ ብዬህ ነበር ልጄ!...ብዬህ ነበር" "እና ሩብ ሰዓት ያህል እንኳን ሳይቆዩ ሃሳብዎን አስሰርዞ፤ የገዙትን መድኃኒት የሚያስመልስ ምን ተአምር ተፈጠረ?! ቅድም የማይመለከተኝን ነገር ሲዘላብዱልኝ ነበር እኮ" አረጋዊው አንገታቸውን ደፉ፡፡ "እኮ ምን ቢፈጠር ነው…?" "ቤቴ ሳልደርስ ነው አንተ ዘንድ የመጣሁት" "ለምን?" አሉ ሌሎቹ፡፡ "ሰፈርተኞቼ ደጄ ላይ ሲጯጯሁ አየሁ፡፡ ባለቤቴን በህይወቷ ልደርስላት አልቻልኩም!" አሉ አረጋዊው ድምፃቸው እየሻከረ፤ እንባቸው እየወረደ፡፡ በመድኃኒት ሻጩ ፊት ላይ ፀፀትና ድንጋጤ እየታየ ድፍን መቶ ብር አውጥቶ በሻካራ እጆቻቸው ላይ አኖረ፡፡ ሌሎቹም ኪሶቻቸውን ይፈትሹ ጀመር፡፡
"ይባርካችሁ ልጆቼ! ከፈን መግዣ ስላልነበረኝ እንጂ…" እንባ ተናነቃቸው፡፡ መንሰቅሰቃቸውን እየቀጠሉ ወጡ፡፡ ፀጥታ!

<u>መመሪያ አንድ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምርንያታችሁን በአጭሩ ግለፁ</u>፡፡

፩. አዛውንቱ ሰውዬ ወደ መድኃኒት ቤቱ ተመልው የመጡት የተሳሳተ መድኃኒት ስለሰጣቸው ለመቀየር ነበር፡፡

------------------------------------------------------------

፪. ለአዛውንቱ የተሸጠ መድኃኒት እንደማይመለስ ማስታወቂያውን ያሳያቸው ጎልማሳው ገገር ነበር፡፡ ----------------------------------------------------------------

፫. አዛውንቱ ወደ መድኃኒት ቤት የተመለሱት ቤታቸው ሳይደርሱ ነው፡፡

----------------------------------------------------------------

፬. ዋና ባለታሪኮቹ አራት ልጆች ነበሯቸው፡፡ --------------------------------------------

፭. መድኃኒቱን የገዙት በሰባ ሁለት ብር ነው፡፡ --------------------------------------------

***<u>መመሪያ ሁለት፦ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ የተሸለውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡</u>***

፩.አረጋዊው ዕድሜያቸው ስንት ነበር?

. ሀ. ወደ ስልሳዎቹ የሚጠጋ ለ. ወደ ሰባዎቹ የሚጠጋ

. ሐ. ወደ ሰማኒያዎቹ የሚጠጋ መ. ወደ ዘጠናዎቹ የሚጠጋ

፪. መድኃኒት የሚሸጡት ስንት ናቸው?

ሀ. አምስት ለ. አራት ሐ. ሶስት መ. አንድ

፫. ዛሬ በዚህ ሰውዬ እንድጨቀጨቅ ተፈርዶብኛል ልበል? ብሎ የተናገረው ማን ነው?

ሀ. አዛውንቱ ለ. ጎልማሳው ሐ. መድኃኒት ሻጩ መ. ተስተናጋጁ

፬. ጎልማሳው የጠላው የማንን ንግግር ነበር?

ሀ. የተስተናጋጁን ለ. የአሮጊቷን ሐ. የመድኃኒት ሻጩን መ. የአረጋዊውን

፭. አዛውንቱ ወዴት ነበር ተመልሰው የመጡት?

ሀ. መርጃ ድርጅት ለ. ፋርማሲ ሐ. የድኩማን መኖሪያ መ. ወደ ቤታቸው

፯. "እባክህን **<u>የሰጠኸኝን</u>** ወስደህ..." በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ምንን ይገልፃል

ሀ. መድኃኒቱን ለ. ብሩን ሐ. አረጋዊውን መ. ወጣቷን

፯. የአረጋዊው የኑሮ ሁኔታ ---------- ነበር፡፡

ሀ. የተደላደለ ለ. የተመቻቸ ሐ. ጤናማ መ. የተጎሳቆለ

፰. ያደፈና የነተበ ነጠላ የለበሰው ---------------- ነው፡፡

. ሀ. ዘንቢል ያንጠለጠሉት አሮጊት ለ. አረጋዊው .

. ሐ. ወጣቷ ተስተናጋጅ መ. ለቀስተኛው

፱. የጋብቻ ቀለበታቸውን ያስያዙት ለማን ነበር?

ሀ. ለሚያምኑት ሰው ለ. ለልጃቸው ሐ. ለጎረቤታቸው መ. ለመድኃኒት ሻጩ

፲. መድኃኒቱን ለምንድነው መመለስ የፈለጉት?

ሀ. ፀበል ሊወስዱ ቸው ለ. ባህላዊ ህክምና ሊወስዱ ቸው

ሐ. ከፈን ለመግዛት መ. ወርቁን ለማስመለስ

፲፩. "ቅናሽ ዋጋ ብትከፍለኝም..." የሚለው ሃሳብ ምንን ይገልፃል?

ሀ. የከፈሉትን ሙሉ ዋጋ ብትከፍለኝም ለ. የከፈልኩትን ዋጋ አብልጠህ

ሐ. ከከፈልኩት ዋጋ እጥፍ አድርገህ መ. ከከፈልኩት ዋጋ ቀንሰህ

፲፪. የአዛውንቱ ሰፈርተኞች የሚጯጯሁት ለምንድን ነው?

ሀ. ባለቤታቸው በመሞታቸው ለ. ባለቤታቸው በጣም ስላመማቸው

. ሐ. ባለቤታቸው መድኃኒት ባለማግኘታቸው መ. ልጆቻቸው ስለተራቡ

፲፫. አረጋዊው በለሰለሱ ቃላት መማፀን ያዙ፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ **"መማፀን"** የሚለው ቃል ፍቺ ----------------------ነው፡፡

ሀ. ማፅናናት ለ. መቆጣት ሐ. መለመን መ. መናገር

፲፬. ሌሎች መድኃኒት ገዥዎችን ያስተናግድ ገባ፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ "ያስተናግድ" የሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. መጠጥ የሸጥላቸው ለ. መድኃኒት ይሸጥላቸው

ሐ. ምግብ ይሸጥላቸው መ. ሀዘንተኞችን ያፅናናቸው

፲፭. ነጠላው ከሰውነታቸው በከፋ ሁኔታ ያረጀ ኮታቸውን **<u>ደብቆላቸዋል</u>**፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. ሸፍኖላቸው ለ. ማንም በማያየው ቦታ አስቀምጦላቸው

ሐ. ለማንም ሳይነግርባቸው መ. ሁሉም እንዲያየው አድርጎታል

**<u>መመሪያ ሶስት፡-ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ"ሀ" ረድፍ ስር ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ</u>**፡፡

| **<u>"ሀ"</u>** | **<u>"ለ"</u>** |
|---|---|
| ፩. እንቶ ፈንቶ | ሀ. ለፍቶ ኗሪ |
| ፪. ለስላሳ ቃላት | ለ. አዛውንት |
| ፫. መጨቅጨቅ | ሐ. እየጣሩ |
| ፬. ከርታታ | መ. መወትወት |
| ፭. ሽማግሌ | ሠ. በባሰ |
| ፮. ሊያባብላት | ረ. ሊያግባቡት |
| ፯. እየሞከሩ | ሰ. አሳዛኝ |
| ፰. በከፋ ሁኔታ | ሸ. ያለቀ/የነተበ |
| ፱. ያረጀ | ቀ. የማይረባ |
| ፲. የከረመ | በ. የቆየ |

ተ. መሸጥ

ቸ. አልኮል የሌለው መጠጥ

<u>መመሪያ አራት</u>፡-<u>ምንባቡን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የቀረቡትን ቃላት በመምረጥ ባዶ ቦታውን ሙሉ</u>፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የከረመ | ጀንበር | ያፌዝክበትን | ሲዘላብዱልኝ | በህይወቷ |
| መንሰቅሰቃቸው | ፀፀት | ጎልማሳ | ትሁት | ነካ |

፩. "ሽማግሌ ስለሆንኩ እንጂ…" አሉት ------------------- በሆነች ፈገግታ ሊያባብሉት እየሞከሩ

፪. "ይሄ ሰውዬ ----------------- ያደርገዋል ልበል?" አለ፡፡

፫. "አቅሜ የደከመ ባይሆን ኖሮ…" አሉት፤ ጫማ ካገኙ ----------------- እግራቸውን እያዩ

፬. አነጋገሯን ያልወደደው የሚመስል ሌላኛው ------------------- ደግሞ፣ "መድኃኒቱን ሁሉ የገዙት ከሂሁ ነው" አለ፡፡

፭. "አይ ልጄ! ጉዳዩን ብታውቀው ኖሮ ----------------- ምላስን ታፍርበት ነበር…" አሉ፡፡

፮. የዕድሜዬ ------------------ እየጠለቀ ባለበት ሰዓት ልጆች በትና እንዳትሞት ፀልይልኝ ብለውኝ ነበር፡፡

፯. ቅድም የማይመለከተኝን ነገር --------------------- ነበር እኮ

፰. ባለቤቴን -------------------- ልደርስላት አልቻልኩም

፱. በመድኃኒት ሻጩ፡ ፊት ላይ ---------------------- እየታየ ድፍን መቶ ብር አውጥቶ በሻካራ እጃቸው ላይ አኖረ፡፡

፲. እንባ ተናነቃቸው፡፡ ---------------- እየቀጠሉ ወጡ፡